«ማኅበረ ቅዱሳን»
እግዚአብሔር ያከበራቸው
የነቢያት፣ የሐዋርያት፣
የጻድቃን፣ የሰማዕታት
በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣
ትሩፋትና አማላጅነት
የሚዘከርበት በመሆኑ ይህን
ስያሜ አግኝቷል።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ
ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በሰ/ት/ቤቶች ማ/መ
ማኅበረ ቅዱሳን ኅትመት
ሚዲያ መምሪያ የሚታተም
ትምህርታዊ መጽሔት

# ሐመር

## ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ
ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣
ሥርዓት እምነትና
ክርስቲያናዊ ትውፊት
ጠብቆ የሚወጣ

፳፱ኛ ዓመት ቁጥር ፮
መጋቢት ፳፻፲፬ ዓ.ም.

ም/ዋና አዘጋጅ፡-
*ዲያቆን አሻግሬ አምጤ*
አድራሻ፡- የካ ክፍለ ከተማ
*ወረዳ 01/02 የቤት ቍጥር 521/522*
*+251- 911361580*
ከፍተኛ ሪፖርተር፡-
*ቀሲስ ዐቢይ ሙሉቀን*
*ኮፒ አርታዒ፡-*
*ቀሲስ ልዑል ታመነ*
የገጽ መልክአ ባለሞያና ጸሐፊ፡-
*ገነት ታደሰ*
አሳታሚበማኅበረ ቅዱሳን ልማት ተቋማት አስተዳደር
*አ.አ አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06*
የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ፡-
*+251-118-124222*
*ፖ. ሣ. ቍ.80078*
*magazine@eotcmk.org*
የማኅበረ ቅዱሳን ሕዝብ ግንኙነት
*+251-962 17 17 17*
የልማት ተቋማት ሽያጭና ስርጭት መምሪያ
*0111 54 04 84/24 61 84/944 25 90 14*
የገበያ ጥናት ልማት መምሪያ
*0111 26 65 49*
*የማስታወቂያና የገበያ ጥናት ባለሞያ*
*ጌዴዎን አክሊሉ*
*09 44 25 90 26*

# ማውጫ

መልእክት ዘማኅበረ ቅዱሳን
አጀንዳ ተቀባይ ላለመሆን ኀላፊነትን አስቀድሞ
መወጣት ........................................................ ፪

ዐውደ ስብከት
"ያስታቸው ዘንድ ይተጋል" .................................. ፬

ትምህርተ ሃይማኖት
"ጻድቃንም መላእክትም በአንድ ዓለም ይኖራሉ" .......... ፮

ዐቢይ ጉዳይ
የቤተ ክርስቲያን የዘመን ክሥተቶች ............................ ፲

ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ
መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባልንጀነት........................................ ፲፬

እናስተዋውቃችሁ
ገነተ ቅዱሳን ፈንድቃ መድኃኔዓለም አንድነት ገዳም......... ፲፮

የነገዋ ቤተ ክርስቲያን
የኢንተርኔት ዘመን ስብከተ ወንጌል ............................ ፳

ኪነ ጥበብ
ካሳ............................................................ ፳፫

የጥያቄዎቻችሁ መልስ
ለሰው ይናገርብኛል ብዬ ስለምሰጋ ኃጢአቴን
ለካህን ባልናገርስ?................................................ ፳፮

*በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ።*

# አጀንዳ ተቀባይ ላለመሆን ኀላፊነትን አስቀድሞ መወጣት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በየዘመናቱ ልዩ ልዩ ፈተናዎች ቢገጠሟትም በጽናትና በመንፈሳዊ ጥበብ ስታሳልፈው መኖሯ የሚታወቅ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ከየአቅጣጫው የሚገጥማትን ፈተና ስትቋቋመው የኖረችው በመንፈስ ቅዱስ ስትጠበቅ የምትኖር በመሆኗና መከራውን ሳይሳቀቁ በጽናት የሚያሸንፉ ልጆችን ስትወልድ በመኖሯ ነው፡፡ ልጇቿ በየዘመኑ ቤተ ክርስቲያንን የሚገጥሟትን ፈተናዎች ተቋቁመው ዘመኑን ዋጅተው ትውልዱን ማሻገር ብቻ ሳይሆን የተከሠተውን መከራ የቤተ ክርስቲያንን ብርሃንነት ሲገልጡበት በመኖራቸው ነው፡፡

ጥንት የተፈጸመው በታሪክ ተመዝግቦ በመቀመጡ አንብበን ብንረዳውም በዘመናችንም አባቶቻችን ቤተ ክርስቲያን የገጠሟትን ችግሮች ለመፍታት እየሄዱበት ያለው መንፈሳዊ ጥበብ ለልጆቻቸው መንፈሳዊ ጽንዓት የሚሰጥ ነው፡፡ በተለይ ባለፉት ሁለት ሦስት ዓመታት በቤተ ክርስቲያን ላይ ያልደረሰ መከራ ባይኖርም አባቶቻችን በአንድ በኩል ችግሩ እንዲወገድ መንግሥትን ከማሳሰብ አልፎ በጽንዓት መጠየቅ በሌላ በኩል ደግሞ ለችግር የተጋለጡትን መደገፍ ያከናውኗቸው ተግባራት ናቸው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ሁል ጊዜ አጀንዳ ተቀባይ ከመሆን አልፋ አስተዳደራዊ መርሆዎቿንና ሀገራዊ አበርክቶዋን በሚገባ ማሳወቅ ካልቻለች ምንም ዓይነት ሀገራዊ አበርክቶ እንደ ሌላት፣ ብትኖር እንደማትጠቅም፣ ባትኖርም እንደማትጎዳ ተደርጋ ስለምትታይ የችግሩ ውስብስብነት የከፋ ጥፋት ያደርሳል፡፡

አባቶቻችን በልዩ ልዩ መንገድ መከራው የሚቆምበትን፣ ሕዝበ ክርስቲያኑ ከአምላካቸው በረከት የሚያገኙበትን ተግባር ሲፈጽሙ መቆየታቸው የሚያስመሰግን ቢሆንም ገና ብዙ እንደሚቀርም መታወቅ ይኖርበታል፡፡ በየደረጃው በመንግሥት መዋቅር ተሰግስገው ሊያራምዱት ለፈለጉት የግል ዓላማቸው እንቅፋት ትሆንብናለች በሚል ስጋት የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን አማኞች የሚያስጨፈጭፉ፣ ቀን ለአገር አሳቢ መስለው ንግግር እያደረጉ ሌሊት ከጥፋት ፈጻሚዎች ጋር የሚመሣጠሩ አካላት ቢኖሩም አባቶቻችን ጉዳዩን የያዙት በፈሊጥ በመሆኑ እንጂ አገር በነውጠኞች ትጠፋ ነበር፡፡ ለጥፋት የተሰለፉ ወገኖች በሄዱበት መንገድ እንድንጓዝና እነርሱ የሚሰጡንን አጀንዳ ብቻ ይዘን እሳት የማጥፋት ተግባር እንድንፈጽም፣ ሕዝብም ለነውጥ እንዲነሣሣ ስሜቱን የሚጎዱ ተግባራትን ቢፈጽሙም ምላሹ እነርሱ ባልጠበቁት መንገድ እንዲሆን፣ አገርም በአመጽ እንዳትፈርስ ሲያደርጉ የኖሩት አባቶቻችን ናቸው፡፡ የአባቶቻችን ሚና አገር ስትወረርና ሕዝብ ለመከራ ሲጋለጥ አብረው እየኖሩ መከራ በመቀበል ሕዝብ የበለጠ መከራ እንዳይደርስበት በማጽናናት ጭምር የሚገለጥ መሆኑን በደቡብ ወሎ፣ በሰሜን ወሎና በዋግ ኽምራ አህጉረ ስብከት የሚገኙ አባቶችን አይተናል፡፡ በልዩ ልዩ አካባቢዎች በክርስቲያኖች ላይ ጀምላ ችፍጨፋ ቢፈጸምም አባቶቻችን የመረጡት ሰላማዊውንና ሕጋዊውን መንገድ ተከትሎ መሥራትን ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ተግባር ብዙ ዋጋ ማስከፈሉ የታወቀ ቢሆንም አጥፊዎች በሄዱበት መንገድ መጓዝ አገርን ያለ ሕዝብ ማስቀረት በመሆኑ አባቶቻችን ይህን መንገድ አለመምረጣቸው የሚያስደንቅ ነው፡፡ አንዳንድ የመንግሥት ባለሥልጣናት ሲያደርጉት የከረሙት ግን ሕዝብን አስተዳድራለሁ ከሚል አካል የማይጠበቅ እኩይ ድርጊት ነው፡፡ ድርጊታቸውም እነዚህ አካላት ለምን ሥልጣን እንደ ያዙ ያውቁታልን? የሚል ጥያቄ ያስነሣል፡፡

ከቤተ ክርስቲያን የሚጠበቀው ሕጋዊውንና ሰላማዊውን መንገድ ይዞ ቀጥ ብሎ በመጓዝ ለዘለቄታው አሸናፊ መሆን እንጂ ለጊዜው በሚገኝ ድል አገር ማሸበር አለመሆኑ መታወቅ አለበት፡፡ በየጊዜው ከቤተ ክርስቲያን አባቶች የሚጎድል ነገር ባይኖርም ራሳቸው ገርፈው ራሳቸው የሚጮኹትን አንዳንድ ባለሥልጣናት እኩይ ድርጊት መንግሥት ተከታትሎ ማስተካከል ካልቻለ አገር ከዚህ ወደሚከፋ ማኅበራዊ ቀውስ ልትገባ ትችላለች፡፡ አባት መስለው የቤተ ክርስቲያንን መዋቅር ይዘው አባቶችንና ሕዝበ ክርስቲያኑን ለመከፋፈል የሚሞክሩ፣ አንዱን አቅርበው ሌላውን በማራቅ ልዩነት የሚፈጥሩ፣ የተሳሳተ መረጃ ሰጥተው በብዙኃን መገናኛ ካስነገሩ በኋላ ሐሰት መሆኑ የሚረጋገጥባቸው፣ እናደርጋለን ብለው ቃል ከገቡ በኋላ ቃላቸውን የሚያብሉት ሥልጣን ላይ የተቀመጡ አንዳንድ የመንግሥት አካላት እንጂ ቤተ ክርስቲያን አለመሆኗን መረዳት ከስሕተት ያድናል፡፡ በቤተ ክርስቲያን ላይ እየደረሰ ላለው ፈተና ምክንያት የሚሆኑ የራሳችን የመሰሉ፣ መልካቸው ከእኛ ግብራቸውና ተልኳቸው ከሌላ የሆኑ አካላት መኖራቸውም መታወቅ ይኖርበታል፡፡ እንዲህ የሚያደርጉትንም ቢሆን ቀስ በቀስ ጊዜ ስለሚገልጣቸው መጽናት ያስፈልጋል፡፡

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የማይታለፍ የመሰለ ፈተና ቢገጥማትም ባሸናፊነት መወጣቷ የተረጋገጠው አምላኳ ስለማይለያት ነው፡፡ ባለፈው ዓመት በሆሣዕና ከተማ ጥምቀተ ባሕርን በተመለከተ የተፈጸመው በአንድ የመንግሥት አካል ይቅርና በአንድ ግለሰብ እንኳ የሚፈጸም አልነበረም፡፡ ማኅተም የሌለው፣ ማን እንደ ሠራው የማይታወቅ፣ አድራሻ የሌለው፣ ባለሥልጣናት ይሁንታ ያልሰጡት፣ ሠርቶ ያጸደቀው ባለሞያ ያልፈረመበት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ለቤተ ክርስቲያን ሰጠን ብለው በደቂቃ ውስጥ የባህል ምኒስቴር ጭምር በማኅበራዊ ትሥሥር ገጹ ለዓለም አሳውቆ ሲያበቃ ታሽጎ የተሰጠውን ሀገረ ስብከቱ ሲከፍት የሚያሳፍር ሆኖ አግኝቶታል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ተግባር ሕዝብ መንግሥትን እንዳያምን ከማድረግ ውጭ ዘለቂታዊ ጠቀሜታ የለውም፡፡ የሀገረ

ስብከቱን ሊቀ ጳጳስና አገልጋዮች ከፊት አድርጎ ሕጋዊውን መንገድ ብቻ ተከትሎ በጽንዓት የታገለው የከተማው ሕዝበ ክርስቲያን በዚህ ዓመት ሕጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታውን አግኝቷል።

ቤተ ክርስቲያን ሕጋዊውን መንገድ ብቻ በመምረጧም ቤተ ክርስቲያን እንጂ መንግሥት አለማትረፉን መረዳት ያስፈልጋል። በአዲስ አበባ ከተማና በሌሎች ከተሞች እየተፈጸመ ያለውም ሕጋዊውንና ሰላማዊውን መንገድ የተከተለ ነው። አዲስ አበባ ሀገረ ስብከት የሄደበት መንገድ ሕግና ሥርዓትን ብቻ የተከተለ ቢሆንም ሕጋዊውን መንገድ ትቶ ኃይል እንዲጠቀም የሚገፋፉ እኩይ ተግባራት ነበሩ። ከተማ አስተዳደሩ ይፈጽመውና ያስፈጽመው የነበረው ሕዝበ ክርስቲያኑን ስሜታዊ በማድረግ በመንግሥት ላይ “ሆ” ብሎ እንዲነሣ የሚያደርግ ቢሆንም አባቶች ሕዝቡን እያረጋጉ በሌላ በኩል ደግሞ አስተዳደሩን በሰላማዊ መንገድ በመያዝ ጉዳዩን ዓለም እንዲያውቀው ማድረጋቸው የቤተ ክርስቲያንን አሸናፊነት ገሀድ ያወጣ በመሆኑ ለክርስያኖች ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ተቋማት መንግሥትንም ጨምሮ ትምህርት የሚያገኙበት ነው ብለን እናምናለን።

አዲስ አበባ ሀገረ ስብከት በሕዝበ ክርስቲያኑ ላይ ተደጋጋሚ በደል ሲፈጸምበት አባቶች የመረጡት ሰላማዊውንና ሕጋዊውን መንገድ እንጂ አስተዳደሩ የሄደበትን ነውጠኝነትና አድሏዊነት አልነበረም። ሳይታክቱ በየመድረኩ የሚገኙት የከተማዋ ከንቲባ በቤተ ክርስቲያን ይዞታ ላይ ያላቸውን አቋም ቀርበው እንዲያስረዱ ቅዱስ ሲኖዶስ ለጻፈላቸው ደብዳቤ ምላሻቸው “ጠቅላይ ቤተ ክህነት ለደኅንነቴ ስለሚያሰጋኝ በሆቴል እንሰብሰብ” በማለት መልስ ሰጥተው የነበረ ቢሆንም አባቶቻችን “የቤተ ክርስቲያንን ክብር በማይመጥን ቦታ አንገኝም” በሚለው አቋማቸው ጸንተው “ቅዱስ ሲኖዶስ መንበሩን ለቆ ሆቴል ውስጥ አይሰበሰብም” ማለታቸው ከተማ አስተዳደሩ ጉዳዩን እንደ ገና በትኩረት በማየት ወደ ቅዱስ ሲኖዶስ ጽሕፈት ቤት ሄዶ በጉዳዩ ላይ እንዲወያይ አድርጎታል። ከመናገር ይልቅ ዝምታ፣ በስሜት ከመነዳት ይልቅ ርጋታ፣ ነውጥ ከመፍጠር ይልቅ መገፋት አሸናፊ መሆኑን አባቶቻችን ያሳዩት ትዕግሥት የሚደነቅ ነው። ከተማ አስተዳደሩ በሄደበት መንገድ መንዝ አዋጭ አለመሆኑን መንግሥትም፣ ተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎችም ትምህርት የሚያገኙበት ነው ብለን እናምናለን። አባቶቻችን በማስተዋል የፈጸሙት ተግባር ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ሁል ጊዜ አጀንዳ ተቀባይ ከመሆን ይታደጋታል።

የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ይዞታ ነጠቃን በተመከለተ ከተማ አስተዳደሩ ያለውን አቋም ለማስረዳት ከቅዱስ ሲኖዶስ ፊት ቀርቦ የነበረው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ውጤታማ ውይይት ማድረጉ ተገልጧል። የተፈጸመው የአባቶቻችንን ጥንካሬ የሚያሳይና የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ክብር የሚያስጠብቅ ነው። የተደረገው መልካም ቢሆንም በቂ ባለመሆኑ ጉዳዩን ከዳር ማድረስ ያልፈልጋል። ወደ ፊትም ችግር እንዳይፈጠር መሥራት ይገባል። ቤተ ክርስቲያንም ሁል ጊዜ አጀንዳ ከመቀበል ወጥታ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በጥናት እያስደገፈች ለሚመለከተው አካል አስቀድማ ማሳወቅ ይጠበቅባታል። ይህን ማድረግ የሚቻለው መጭውን ዘመን ከግምት ውስጥ ያስገባ ተግባር ለማከናወን የሚያግዝ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ነው። ዘመኑን የዋጀ ተግባር ለማከናወን ምን መሥራት፣ እንዴት ማከናወን እንደሚገባ አስቀድሞ መለየት ተገቢ ነው። ይህም ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥትም ሆነ ከሌሎች ተቋማት ምን እንደምትጠብቅ፣ ከእርሷም ምን እንደሚጠበቅ ለመለየት ያስችላታል። እንዲህ ዓይነቱ ተግባር በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ላይ ችግር ሲከሠት ለማስወገድ ከመድከም አስቀድሞ ለመከላከል፣ ከደረሰም በኋላ ለመቀነስ ያግዛል ብለን እናምናለን። ✣

# “ያስታቸው ዘንድ ይተጋል”

(መጽሐፈ ምሥጢር ፲፥፬)

ቀሲስ ዐቢይ ሙሉቀን

የሰው ልጅ ከፍጥረታት ሁሉ ልቆና ከብሮ በአርአያ እግዚአብሔር የተፈጠረ ልዩ ፍጥረት ነው (ዘፍ.፩፥፳፯)። ይሁን እንጂ ክቡር የሆነውን ነገር የሚፈልገው ብዙ በመሆኑ ቅዱሳን መላእክት “ዘያፈትዎሙ ለመላእክት ከመ የሐውጽዎ ለዘእምቅድመ ዓለም፤ ከዓለም በፊት የነበረውን ይጎበኙት ዘንድ ያስመኛቸዋል” (መጽሐፈ ኪዳን) እንደተባለ ያዩት ዘንድ በተጋት የሚሹትን አምላክ ያዩበት በመሆኑ ቢደሰቱበትም ዲያብሎስ ግን በሰይጣናዊ ቅናት ተነሣሥቶ፣ ከፈጣሪው አጣልቶ የተሰጠውን ጸጋ ሊያስወስድበት ያላሰበበት ጊዜ አልነበረም። በክፉ ምክሩም አታልሎ አታድርግ የተባለውን እንዲያደርግና ከፈጣሪው እንዲጣላ፣ ከጸጋ እንዲራቆት፣ ልጅነቱን እንዲያጣ፣ ገነትን ተነጥቆ ወደ ምድረ ፋይድ እንዲወድቅ አድርጎታል። በክፉ ምክሩ ገነትን ያህል ቦታ እግዚአብሔርን ያህል ጌታ ያሳጣው ጥንተ ጠላት ዲያብሎስ ምንም እንኳን ኃይሉ እንደ ብሉይ ኪዳኑ ባይሆንም በሐዲስ ኪዳንም ያለ ዕረፍት ይዋጋዋል፣ ከሃይማኖቱ አሥቶ፣ ከፈጣሪው አጣልቶ በሲኦል ያኖረው ዘንድም ይተጋል።

አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ “በዕለተ ምጽአት ለፍርድ የሚመጣው እግዚአብሔር ወልድ ብቻ እንጂ እግዚአብሔር አብ ለፍርድ አይመጣም” በማለት ኑፋቄ ያስተምር ለነበረው ለቢቱ መልስ የሰጠው “የሰው ልጅ እንደምን በመለኮት ላይ ይህን ያህል ስድብ ይህን ያህልም መከፋፈልን በወልድና በወለደው ላይ ይናገራል? ቢቱ የነቢያትና የሐዋርያትን መጽሐፍ የማያውቅ ይመስላችኋልን? ፈጽሞ ያውቃል። ነገር ግን ሰይጣንን ደስ በሚያሰኘው ገንዘብ። ሰይጣንም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የማያውቅ አይደለም እኮን፤ በልቡ ትዕቢት የጎሊናውን ራስ ቀና ቀና በማድረግ ትእዛዝን ይቃወማል እንጂ። ሰይጣን እግዚአብሔር የሰውን ልጅ እንደሚወደው ስለሚያውቅ የሰው ልጆችን ያስታቸው ዘንድ ይተጋል። ቢቱም አባቱ ሰይጣንን ይመስላል። ምእመናንንም ያስታቸው ዘንድ ይተጋል። ” በማለት አስረድቷል” (መጽሐፈ ምሥጢር ምዕ.፲ ቍ.፬)።

በዚህ ጽሑፍ ያስታቸው ዘንድ የሚተጋው ማን ነው? የሚያስታቸውስ እነማንን ነው? ለምንስ ሊያስታቸው ይተጋል? የሚሉ ነጥቦችን በአጭሩ እናቀርባለን።

### ያስታቸው ዘንድ የሚተጋ የተባለው ማን ነው?

አባ ጊዮርጊስ በዋናነት ሊገልጸው የፈለገው የሥላሴን አንድነት ሦስትነት፣ የአብ፣ የወልድና የመንፈስ ቅዱስን ህልውና በመጠራጠር የካደውን የቢቱን ጉዳይ ሲሆን መነሻ ያደረገው ቢቱ ከገለጸው የክሕደት መጀመሪያ፣ የሐሰት አባት ተብሎ ከተጠራው ሳጥናኤልን ነው። ሳጥናኤል፣ ዲያብሎስ፣ ሰይጣን፣ ጋኔን፣ ቢል አንድ ነው። ትርጒሙ ውዱቅ (የተጣለ)፣ የተጣላ፣ የሚያጣላ መስተቃርን ማለት ነው። አዳም አትብላ የተባለውን ሳይበላና ከፈጣሪው ሳይጣላ፣ ከልጅነት ሳይራቆት፣ ከገነት ሳይባረር፣ በክብር እያለ ሰይጣን ቅንዓተኛ፣ ከሳሽ፣ የሚያጣላ ነበር። ጥንተ ጠላት የሚባለውም በዚህ ምክንያት ነው። ቅዱስ ቀለሚንጦስ ዘርዎም “ሰይጣን ለአዳም ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ሀብተ ጸጋ ባየ ጊዜ ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ቅንዓት አደረበት፤ በአዳም ላይም ቀናበት፤ እርሱንም አንሥቶ ከእግዚአብሔር የሚያርቅበትንና የእርሱም ታዛዥ የሚያደርግበትን ተንኮል በማሰብ ከጸጋ እግዚአብሔር አዳምን ለማውጣት ተነሣ” በማለት የገለጠው ለዚህ ነው (ቀሌ.፩፥፵፮)።

አዳምን በክፉ ምክሩ ያሳተው ጥንተ ጠላት ዲያብሎስ ከአዳም የተወለደውን ቃኤልንም እንዲሁ አሳስቶ ወንድሙን እንዲገድል አደረገው። በብሉይ ኪዳን አንድምታ ትርጓሜ ተጽፎ እንደ ምናነበው ሰይጣን መልከ መልካም የሆነች እኅቱን ሉድን በማጣቱ ያዘነውን ቃየልን ወደ ክፉ አሳብ አስገባው። ክፉ ምክሩን እንዲቀበል ያደረገውና እንዲፈጽመው የገፋፋው አንዱ ሰይጣን በሰው፣ ሌላኛው ሰይጣን ደግሞ በቍራ ተመስለው ሰውየው ቍራውን ሲገድለው በማሳየት እንዲህም አለን ብሎ ወንድሙን እንዲገድለው በማድረግ ነው(ዘፍ.፬፥፰ አንድምታ)።

አዳምን በክፉ ምክሩ አስቶና ከፈጣሪው አጣልቶ ጸጋውን ሁሉ ያስገፈፈው፣ ቃየልን የወንድሙ ገዳይ ያደረገው ጥንተ ጠላት ዲያብሎስ በየዘመናቱ የእግዚአብሔር ወዳጅ በነበሩት ሰዎች ሁሉ ልዩ ልዩ መከራዎችን ሲያመጣባቸው ኖሯል። አባታችን አብርሃምን ከአምላኩ ለማጣላት ልጅህን ሠዋልኝ ብትለው አያደርገውም በማለት ክፋተት ለማግኘት ቢሞክርም አልተሳካለትም (ዘፍ.፳፪፥፱-፲፫ አንድምታ) በኢዮብ ላይ ተነሣሥቶ ልጆቹን በሞት እንዲነጠቅ፣ ሀብት ንብረቱን እንዲያጣ፣ እርሱም በክፉ ደዌ እንዲሠቃይ አድርጓል። “ሰይጣንም በእግዚአብሔር ፊት እንዲህ ብሎ መለሰ፤ በውኑ ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚያመልከው በከንቱ ነውን? አንተ ቤቱን በውስጥም በውጭም በዙሪያው ያለውንም ሁሉ አልሞላህለትምን? የእጁንም ሥራ ባርከህለታል፣ ከብቱንም በምድር ላይ አብዝተህለታል። ነገር ግን እጅህን ዘርግተህ ያለውን ሁሉ ዳስስ፤ በእውነት በፊትህ ይሰድብሃል” በማለት ቢፈትነውም አልተሳካለትም። ይህም ሰይጣን የሰውን ልጅ ከመክሰስ፣ ክፉ ምክር ከመምከር፣ በልዩ ልዩ ፈተና እንዲወድቅ ከማድረግ ዐርፎ የማያውቅ ለመሆኑ ማሳያ ነው (ኢዮ.፩፥፱-፲፩)።

ከአዳም መፈጠር ጀምሮ ቅንዓት፣ ተንኮል፣ ሐሰት፣ በአጠቃላይ ክፉ ተግባር መገለጫው የሆነውን ጥንተ ጠላት ዲያብሎስን ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ እንዲህ ሲል ይገልጸዋል። “እንግዲህ አዋቂዎች ሁኑ ጽኑም፤ ትጉም፤ ጠላታችሁ ጋኔን የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞራልና። እርሱንም በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት፤ እንዲህም ያለ መከራ በዓለም በአሉ ወንድሞቻችሁ ሁሉ እንደሚፈጸም ዕወቁ፤ ፍቅርንም አጽንታችሁ ያዟት”(፩ጴጥ.፭፥፰-፱)። ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ “ጠላታችሁ ጋኔን” በማለት ጠላት ሊያጠፋው የፈለገውን

እስካላጠፋ ድረስ እንደማያርፍ ዲያብሎስም የሰውን ልጅ ሊያጠፋ እጅግ እንደሚተጋ በሚገባ አስረድቶናል፡፡ ዲያብሎስ ጠላት ብቻ ተብሎ አልበቃውም፡፡ ነፍሰ ገዳይም ተብሏል፡፡ "እርሱ ከጥንት ጀምሮ ነፍሰ ገዳይ ነው፤ በእውነትም አይቆምም"(ዮሐ.፰፥፵፬) የተባለው ሰውን ከአምላኩ ለመለየት ሲተጋ በመኖሩ ነው፡፡

**መላእክትና የሰው ልጅ ስሙን ቀድሰው ክብሩን ወርሰው ይኖሩ ዘንድ የተፈጠሩ ፍጥረታት ናቸው፡፡ ዘለዓለማውያን፣ ሕያዋን፣ ከሕያወ ባሕርይ ከእግዚአብሔር ሕያውነትን በጸጋ ገንዘብ አድርገው ይኖሩ ዘንድ የተፈጠሩ ናቸው፡፡ ሌሎቹ ፍጥረታት ትንሣኤ ሙታን የላቸውም፤ ስሙን ቀድሰው ክብሩን ወርሰው በመንግሥተ ሰማያት የሚኖሩበት ተፈጥሯዊ ማንነት የላቸውም**

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በመዋዕለ ስብከቱ በዘሪውና በዘር መስሎ ባስተማረበት ትምህርቱ ሰይጣንን ጠላት በማለት፣ በሰው ልቡና ውስጥ እንክርዳድ የተባለ ክፋትን፣ኑፋቄን፣ ሐሰትን በአጠቃላይ ክፉ ሥራን እንደሚዘራ ያስተማረው "መልካም ዘርን የዘራ የሰው ልጅ ነው፤ እርሻውም ዓለም ነው፤ መልካሙ ዘር የመንግሥት ልጆች ናቸው፤ እንክርዳዱም የክፉ ልጆች ናቸው፡፡ የዘራውም ጠላት ዲያብሎስ ነው፤ መከሩም የዓለም ፍጻሜ ነው፤ አጫጆችም መላእክት ናቸው "(ማቴ.፲፫፥፴፯-፴፱) በማለት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም"አምነውም እንዳይድኑ ሰይጣን መጥቶ ቃሉን ከልባቸው ይወስድባቸዋል" ተብሎ ተጽፏል(ሉቃ.፰፥፲፪)፡፡

ቅዱስ ዮሐንስ በፍጥሞ ደሴት ተግዞ ሳለ በተመለከተው ራእይ "ዓለሙን ሁሉ የሚያስተው ዲያብሎስና ሰይጣን የተባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፤ ወደ ምድርም ተጣለ፤ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ" በማለት ጥንተ ጠላት እንደሆነ፣ እርሱም አዳምን ከማሳት ጀምሮ በመጨረሻው ዘመን እስኪወድቅ ድረስ የሰውን ልጅ ለማሳት እንደማያርፍ "ታላቁ ዘንዶ፣ እርሱም የቀደመው እባብ" እያለ በጥንተ ግብሩና በመገለጫው ይጠራዋል (ራእ.፲፪፥፱)፡፡

### ሰይጣን ሊያስት የሚተጋው ማንን ነው?

ለዚህ ጥያቄ ብዙም ሳንደክም የሰውን ልጅ ነው በማለት በአጭሩ መመለስ ይቻላል፡፡ በእርግጥ በዓለመ መላእክትም አስቀድሞ መላእክትን ሊያስት ሞክሮ ነበር፡፡ ፈጠሪ ሳይሆን እኔ ፈጠርኋችሁ ባለ ጊዜ እርሱን ተከትለው የሳቱ ነበሩ፡፡ ይሁን እንጂ እርሱን ተከትለው ከሳቱት በቀር ሌሎቹን ግን ማሳት አልተቻለውም ነበር፡፡ ምክንያቱም ሌሎቹ መላእክት "ንቁም በበህላዌነ እስከ ንረክቦ ለአምላክነ፤አምላካችንን እስክናገኘው ድረስ በያለንበት ጸንተን እንቁም" በሚለው የቅዱስ ገብርኤል ቃል ጸንተው ቆመው ነበርና(መጽሐፈ አክሲማሮስ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ገጽ ፴፰)፡፡ በዓለመ መላእክት ካደረገው የማሳት ተግባር በኋላ ግን ኃይሉን ሙሉ በሙሉ ያደረገው በሰው ልጅ ላይ ነው፡፡ የሰው ልጅ መንግሥተ ሰማያት የተዘጋጀችለት፣ በአርአያ እግዚአብሔር የተፈጠረ፣ መላእክትን ያስደነቀ ልዩ ፍጥረት ነው፡፡ "በአዳም ላይ ታላቅ ምስጋና ባዩ ጊዜ መላእክት ከግርማው የተነሣ ፈሩ፤ የመለኮት ብርሃን በአዳም ፊት ይበራ ነበር፡፡ የአዳም ፊት ብርሃን ከፀሐይ ይበልጥ ነበር ሥጋውም እንደ ንጋት ኮከብ ይበራ ነበር "(ቀሌ.፩፥፴፰) ተብሎለታልና፡፡ በእንደዚህ ያለ ክብርና ሞገስ የተፈጠተረውን የሰውን ልጅ ዲያብሎስ ክብሩን ሊያሳጣው እጅግ ይተጋል፡፡

መላእክትና የሰው ልጅ ስሙን ቀድሰው ክብሩን ወርሰው ይኖሩ ዘንድ የተፈጠሩ ፍጥረታት ናቸው፡፡ ዘለዓለማውያን፣ ሕያዋን፣ ከሕያወ ባሕርይ ከእግዚአብሔር ሕያውነትን በጸጋ ገንዘብ አድርገው ይኖሩ ዘንድ የተፈጠሩ ናቸው፡፡ ሌሎቹ ፍጥረታት

ትንሣኤ ሙታን የላቸውም፤ ስሙን ቀድሰው ክብሩን ወርሰው በመንግሥተ ሰማያት የሚኖሩበት ተፈጥሯዊ ማንነት የላቸውም፡፡ ስለዚህ ይህን ክብር ያጣው ሳጥናኤል "እኔ ከሞትሁ ሰርዶ አይብቀል" አለች ተብሎ እንደሚነገርላት ፍጡር በክፉ ቅንዓት ተነሣሥቶ ከተፈጠረለት ስሙን ቀድሶ ክብሩን ወርሶ የመኖር ዓላማ ያወጣው ዘንድ የሰውን ልጅ ለማሳት አብዝቶ ይተጋል፡፡

አዳም አትብላ የተባለውን ዕፀ በለስ ከበላ በኋላ በአዳምና በዲያብሎስ መካከል የተላለፈው እርግማንም "በአንተና በሴቲቱ መካከል፣ በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፤ አንተም ሰኮናውን ትነድፋለህ" (ዘፍ.፫፥፲፭) የሚል ነበር፡፡ በሕያው እግዚአብሔር የተላለፈው በአባቡ አንጻር በዲያብሎስና በሰው ልጅ መካከል ጠላትነት ያለ መሆኑን የሚያስረዳ ነው፡፡ ስለዚህ ማንን ነው ሊያስት የሚተጋው ለሚለው የሰውን ልጅ በሙሉ ነው ብለን እንረዳዋለን፡፡

## ለምን ሊያስታቸው ይተጋል?

ለዚህ ጥያቄ ሊቁ አባ ጊዮርጊስ "እግዚአብሔር የሰውን ልጅ እንደሚወደው ስለሚያውቅ" በማለት የዲያብሎስን የጥላቻውን ምክንያት፣ ሊያስተው የሚተጋበትን መሠረታዊ ቁም ነገር ያስረዳል፡፡ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ እንዴት ይወደዋል የሚለውን ደግሞ ዘርዘር አድርገን እንመልከት፡፡ ፍቅር የሚባለው እስከ መጨረሻው የሚዘልቅ፣ መሞት የሚገባም ቢሆን እንኳን በሞት የሚገለጥ ሲሆን በትክክልም ፍቅር ተብሎ ይጠራል፡፡ በአባቶች ብሂል "የቀን ዘመድ ከገበያም አይገድ" ይባላል፡፡ በአፍ ብቻ እወድሃለሁ፤ አከብርሃለሁ የሚሉትን ነቢዩ ዳዊት "በአፉሆሙ ይድኅሩ ወበልቦሙ ይረግሙ፤ በአፋቸው ይባርካሉ፤ በልባቸው ግን ይረግማሉ" በማለት ይወቅሳቸዋል (መዝ.፷፩፥፬)፡፡ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ የሚወድበት ፍቅር በፍጥረት አንደበት ሊነገር ከሚችለው በላይ ነው፡፡

የእግዚአብሔር ፍቅር የተገለጠው ወንጌላዊው ዮሐንስ "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወትን እንዲያገኝ እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ቤዛ አድርጎ እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲህ ወዶታልና" በማለት እንደገለጸው የእግዚአብሔር ፍቅር የተገለጠው አስቀድሞ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለውን አንድያ ልጁን "ውረድ፤ ተወለድ፤ ተሰቀል፤ ሙት፤" ብሎ ለዓለም ያለ ዋጋ በመስጠት ነው(ዮሐ.፫፥፲፮)፡፡ አባ ሕርያቆስ በቅዳሴው "ፍቅር ሰሀቦ ለወልድ ኀያል እመንበሩ ወአብጽሖ እስከ ለሞት፤ ኀያል ወልድን ፍቅር ሳበው እስከ ሞትም አደረሰው" (ቅዳሴ ማርያም) በማለት እንደ ገለጸው አብ ቢሉ ልጁን፣ ወልድ ቢሉ ሥጋውንና ደሙን በመስጠት በመስቀል ላይ በተከፈለ ዋጋ ነው፡፡

መድኃኔዓለም ክርስቶስ ለሰው ልጅ ያለውን ፍቅር እንዴት እንደገለጸው በመጽሐፈ ቅዳሴ "በሰርክ ጊዜ ሥጋውን የሚሠዋና ፈጽሞ ምግብ የሚሆን ሙሽራን ያየ ማነው? ወልደ እግዚአብሔር ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ከእርሱ በቀር እንደ እርሱ ያደረገው የሌለ እንግዳ ሥርዓትን በዚህ ዓለም ሠራ፡፡ በሰርክ ጊዜ በሐዋርያት ፊት ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ማዕድ አድርጎ ሠራ፡፡ ከእርሱ ይበሉ ዘንድ ያመነበትም ለዘለዓለም ይድን ዘንድ፡፡ በሰርክ ጊዜ መብል መጠጥ የሆነውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን የሰጠን አምላካችን ቡሩክ ነው፡፡ የኃጢአት ማስተሥረያ ሊሆን ለዘለዓለም እንድንበት ዘንድ" ይላል (መጽሐፈ ቅዳሴ፣ ፳፻፫፣ ገጽ ፲፪) ፡፡

እግዚአብሔር የሚወደውን ሰይጣን ሊያስተው ይፈልጋል፡፡ አስቀድሞ እንደተመለከትነው የእግዚአብሔርን ወዳጅ አብርሃምን፣ኢዮብን ሰይጣን ከፈጣሪያቸው ሊያጣላቸው ታግሏል፡፡ ሌሎችንም እንዲሁ፡፡ ይሁን እንጂ እውነተኛ የእግዚአብሔር ወዳጆች ስለነበሩ ድል አድርገውታል፡፡ ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ሊያስረዳን የፈለገውም በአጠቃላይ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ እጅግ አብዝቶ ይወደዋል፡፡ ይሁን እንጂ ሰይጣን ሊያስተው ይተጋል፡፡ ትጋቱ ለበጎ ነገር በሆነ መልካም ነበር፡፡ ግን ሰውን ከፈጣሪ ለማጣላት፣ አስቀድሞ በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል የተፈጠረውን በኋላም የደም ዋጋ የተከፈለለትን በሐዲስ ተፈጥሮ በልጅነት የከበረውን የሰውን ልጅ ከዚህ ልዩና እጅግ የከበረ ጸጋ ሊለየው አብዝቶ ይተጋል፡፡

በጥንት አባቶቻችን በእነ አብርሃም፣ በእነኢዮብ፣ በነቢያት፣ በሐዋርያት፣ በሊቃውንት፣ በመነኰሳት፣ በሰማዕታት ሁሉ እጅግ አብዝቶ ፈተና ያመጣባቸው እንደ ነበር፣ ነገር ግን ድል እንዳደረጉት ዛሬም እግዚአብሔር ስለሚወደን ሰይጣን እኛን ሊያስት እንድሚተጋ ተረድተን ከእርሱ ይልቅ ልንተጋ፣ አብዝተን ልንቃወመው ይገባል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ "እንግዲህ እግዚአብሔርን እሺ በሉት፤ ሰይጣንን ግን እንቢ በሉት፤ ከእናንተም ይሸሻል፡፡ እግዚአብሔርን ቅረቡት ይቀርባችሁማል" (ያዕ.፬፥፯-፰) በማለት እንዳስተማረን መቅረብ ያለብንን እየቀረብን መራቅ ያለብንን ልንርቅ፣ መታዘዝ ላለብን እየታዘዝን እንቢ ልንለው የሚገባንን እንቢ ልንለው ይገባል፡፡

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈጽመን የዲያብሎስን ፈቃድ በመተው የእግዚአብሔር ወዳጆች ለመሆን ደግሞ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "የእግዚአብሔርን ጋሻ ልበሱ፣ ...የሰላምን ወንጌል ኃይልም ተጫምታችሁ ቁሙ፤...የመዳንንም ራስ ቁር በራሳችሁ ላይ ጫኑ... የመንፈስ ቅዱስንም ሰይፍ ያዙ፤ ይኸውም የእግዚአብሔር ቃል ነው" (ኤፌ.፮፥፲፩-፲፯) በማለት ይመክረናልና ጠላት ዲያብሎስን ድል የምንነሣበትን ሃይማኖትን የማጽናትን፣ በጎ ምግባርን የመሥራትን፣ ማለትም የጾም፣ የጸሎት፣ የምጽዋትና የስግደትን ሕይወትና ዕለት ዕለት ቃለ እግዚአብሔርን የመስማት ልምድን ገንዘብ ልናደርግ ይገባል፡፡ ለዚህ ሁሉ አምላከ ቅዱሳን እግዚአብሔር ይርዳን አሜን፡፡✥

# “ጻድቃንም መላእክትም በአንድ ዓለም ይኖራሉ”

## (አረጋዊ መንፈሳዊ ድርሳን ፲፱)

**ቀሲስ ዐቢይ ሙሉቀን**

ከሥነ ፍጥረት የምንረዳው ሕያወ ባሕርይ እግዚአብሔር ሕያዋን ሆነው፣ ስሙን ቀድሰው፣ ክብሩን ወርሰው እንዲኖሩ የፈጠራቸው ፍጥረታት መኖራቸውን ነው፡፡ ከፍጥረታት መካከል ለምግበ ሥጋ፣ ለምግበ ነፍስ የተፈጠሩ አሉ፤ ለአንክሮ ለተዘክሮ የተፈጠሩም አሉ፡፡ ነቢዩ ዳዊት “ጥቀ ዐቢይ ግብርከ እግዚኦ፤ ወኵሎ በጥበብ ገበርከ፤ መልአ ምድረ ዘፈጠርከ፡- አቤቱ ሥራህ እጅግ ታላቅ ነው፤ ሁሉን በጥበብ አደረግህ፤ የፈጠርኸውም ፍጥረት ምድርን ሞላ” (መዝ.፻፫፥፳፬) በማለት እንደ ገለጸው ሁሉንም ፍጥረታት የፈጠረበት ጥበቡ ድንቅ ቢሆንም በልዩ ጥበቡ የፈጠራቸው መላእክትና ሰዎች ስሙን ቀድሰው፣ ክብሩን ወርሰው፣ ሕያዋን ሆነው እንዲኖሩ የተፈጠሩ ናቸው፡፡ ሌሎቹ ፍጥረታት መነሻ እንዳላቸው ሁሉ መጨረሻም አላቸው፤ ይህ ማለት የማይኖሩበት ጊዜ አለ ማለት ነው፡፡ ሰውና መላእክት ግን መነሻ እንጂ መጨረሻ የላቸውም፡፡ በዚህ ጊዜ ተፈጠሩ ይባላል እንጂ በዚህ ጊዜ ያልፋሉ የሚባሉ አይደሉም፡፡

ሕያዋን ፍጥረታት በአንድ ዓለም፣ በአንድ ማኅበር ይኖራሉ፡፡ ይህን አንድ ማኅበር በሊቃውንት “ማኅበረ መላእክት ወሰብእ ተአይነ ክርስቶስ ወእሙ፤ ሶበ እከሥት አፉየ ለውዳሴክሙ፣ ፍሬ ማሕሌት እምልሳንየ ትቅስሙ፣ ምስሌየ ሀልዉ ወምስሌየ ቁሙ፤ የሰውና የመላእክት ማኅበር የእናቱ የድንግል ማርያምና የክርስቶስ አንድነት ነው፤ አፌን ለምስጋና በከፈትሁ ጊዜ የምስጋናን ፍሬ ከአንደበቴ ትቀስሙ ዘንድ ከእኔ ጋር ኑሩ፤ ከእኔ ጋርም ቁሙ” በማለት ገልጠውታል(ነግሥ)፡፡ ከዚህም ሰውና መላእክት እግዚአብሔርን በማመስገን አንድ ማኅበር ሆነው በአንድ ዓለም መኖራቸውን እንረዳለን፡፡

በጸሎተ ኪዳን “ዘያፈትዎሙ ለመላእክት ከመ የሐውጽዎ ለዘእምቅድመ ዓለም፤ ከዓለም በፊት የነበረውን ይጎበኙት ዘንድ መላእክትን የሚያስመኛቸው እርሱ ነው” ተብሎ እንደተገለጠው ሊያዩትና ሊያውቁት የሚመኙት እግዚአብሔር የሰውን ልጅ በአርአያውና በአምሳሉ ፈጥሮ ሲያሳያቸው እጅግ ተደሰቱ፡፡ መላእክት በአርአያውና በአምሳሉ ከፈጠረው እግዚአብሔርን ከአዩበት ከሰው ልጅ ጋር በአንድ ማኅበር ጸንተው በአንድ ዓለም የሚኖሩበትን ማኅበር ለአንባብያን ግልጽ ለማድረግ በዘመን ከፋፍለን እንመለከተዋለን፡፡

፩.አዳም በድሎ ከመውደቁ አስቀድሞ፡- መላእክትና የሰው ልጅ ግንኙነት በዚህ ጊዜ ተጀመረ ብሎ ትክክለኛ ሰዓትና ጊዜውን መናገር ቢቸግርም መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርገን ግንኙነታቸው እንዴት እንደ ነበር መግለጽ ይቻላል፡፡ በመጽሐፈ ኩፋሌ “በተፈጠረባትም ምድር ለአዳም አርባ ቀን ከተፈጸመለት በኋላ ያበጃትና ይጠብቃት ዘንድ ወደ ኤዶም ገነት አስገባነው፡፡ ሚስቱንም በሰማንያኛው ቀን አስገባናት” (ኩፋ.፬፥፱) ተብሎ እንደ ተጻፈው ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንም እንደሚያስረዱት አዳም በተፈጠረ በአርባ ቀኑ፣ ሔዋን ደግሞ በተፈጠረች በሰማንያ ቀኗ ብርሃን ለብሰው፣ ብርሃን ተጎናጽፈው በይባቤ መላእክት ወደ ገነት ገብተዋል፡፡ አዳምና ሔዋን ወደ ገነት ሲገቡ ምስጋና የባሕርይ ገንዘቡ ለሆነው እግዚአብሔር ድካም የሌለባቸው መላእክት ምስጋናቸውን እያቀረቡ አስገብተዋቸዋል፡፡ የጸሎትና የሱባኤ ሥርዓትንም አስተምረዋቸዋል፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ አባታችን አዳም መላእክት በአስተማሩት የጸሎት ሥርዓት ማለትም በሃያ ሁለቱ አሌፋት እግዚአብሔርን እያመሰገነ ከገነት እስከ ወጣበት ጊዜ ድረስ ኑሯል፡፡

**፪. ከድቀተ አዳም እስከ ክርስቶስ ልደት፡-** አዳም ከወደቀና ከገነት ከተባረረ በኋላ ክርስቶስ እስከ ተወለድባት ዕለት ሙሉ በሙሉ ተለያይተዋል ባይባልም በገነት ሳለ ከነበራቸው ኅብረት አንጻር ሲታይ አንድነታቸው ፈርሶ፣ ማኅበራቸው ተቋርጦ ኖሯዋል፡፡ ይሁን እንጂ መላእክት ከእግዚአብሔር ዘንድ ለተልእኮና ለጥበቃ እየተላኩ የሰውን ልጅ ሲያገለግሉ ኖረዋል፡፡ ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን የመላእክትንና የሰውን ልጅ ግንኙነት ዘርዝሮ መጨረስ ባይቻልም ለማሳያ ያህል የተወሰኑትን እናቀርባለን፡፡

***ሀ. መላእክት ከአዳምና ከሔዋን ጋር፡-*** አዳምና ሔዋን ከገነት ከተባረሩ በኋላ አትብሉ የተባሉትን ዕፀ በለስን እንዲበሉ የገፋፋቸው ጥንተ ጠላት ዲያብሎስ በየጊዜው መከራ ያጸናባቸው ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ መላእክት ይራዷቸው ነበር፡፡ አዳም ረዳት ትሆነው ዘንድ ከተሰጠችው ከሔዋን ጋር በተጣላ ጊዜ ያስታረቁት መላእክት ናቸው፡፡ አዳምና ሔዋን ከገነት ከተባረሩ በኋላ እግዚአብሔር ይቅር ይላቸው ዘንድ ቅዝቃዜው ሰውነትን ከሚቆራርጥ ባሕር ውስጥ ገብተው ሱባኤ ያዙ፡፡ ሰይጣን በለመደው የማታለያ ንግግሩ “እኔ የብርሃን መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ነኝ” በማለት ይዘውት ከነበረው ሱባኤ አስወጥቶ ለሦስት ቀን በጽኑዕ ጨለማ አቆያቸው፡፡ በዚህ ጊዜ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ደርሶ ከነበሩበት መከራ አውጥቶ በደብር ቅዱስ አስቀመጣቸው፡፡ ምግባቸውንም በገነት የሚኖሩ አዕዋፍ እንዲያደርሱላቸው አዘዛቸው፡፡ እንደዚህ በመሳሰለው ችግራቸው ሁሉ መላእክት ሰዎችን ይረዷቸው ነበር፡፡

***ለ. መላእክት ከኖኅ ጋር፡-*** ኖኅ በዘመኑ ከነበረው የሰው ልጅ ተለይቶ በእግዚአብሔር ፊት ንጹሕና ጻድቅ ነበር፡፡ “ኖኅም በትውልዱ ጻድቅ፣ ፍጹምም ሰው ነበር፤ ኖኅም እግዚአብሔርን ደስ አሰኘው” (ዘፍ.፮፥፱) የተባለው ለዚህ ነው፡፡ ጻድቅ ሆኖ በመገኘቱም እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ሊያጠፋው አልወደደም፡፡ ከሞት የሚተርፍበትን መርከብ እንዲሠራ አዘዘው እንጂ፡፡ ኖኅ ከጥፋት ውኃ የሚድንበትን መርከብ ሲሠራ በኦሪት ዘፍጥረትና በቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ እንደምናነበው መላእክት ይራዱት ነበር፡፡ መርከቢቱን ሠርቶ ሲጨርስም በመርከቡ ገብተው ከጥፋት ውኃ ይድኑ ዘንድ እግዚአብሔር የፈቀደላቸውን እንስሳት፣ አራዊትና አዕዋፍ ሁሉ ወደ መርከቧ ውስጥ በማስገባት ተራድተውታል፡፡

***ሐ. መላእክት ከእስራኤል ጋር፡-*** ነቢዩ ዳዊት “ክፉ ነገር ወደ አንተ አይቀርብም፤ መቅሠፍትም ወደ ቤትህ አይገባም፤ በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለአንተ

ያዝዛቸዋልና" በማለት እንደተናገረው እስራኤል በመጀመሪያ ከግብፅ ወደ ተስፋይቱ ምድር ወደ ከነዓን በሚያደርጉት ጉዞ እግዚአብሔር መግቦቱንና አምላካዊ ጥበቃውን በመላእክቱ አማካይነት ሲያከናውን ኖሯል (መዝ.፺፥፲-፲፩)፡፡ ባሕር ከፍሎ አሻገራቸው፤ መና ከሰማይ አውርዶ መገባቸው፤ ቀን በደመና፣ ሌሊት በብርሃነ እሳት መራቸው፡፡ በዚህ ሁሉ ጉዟቸው መላእክት ከእስራኤል ጋር ነበሩ፡፡ በኋላም ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለሱ ይጠብቋቸው፣ ይመግቧቸው፣ በችግራቸው ሁሉ ይረዷቸው ነበር፡፡

**መ.መላእክት ከነቢያት ጋር፡-** እግዚአብሔር በኋላ ዘመን ሊፈጽመው ያለውን ትንቢት በነቢያት ያናግር የነበረው በመላእክት በኩል ነው፡፡ እግዚአብሔር አስቀድሞ ለአዳም የገባውን የማዳን ተግባር ከዘመኑ ብዛት የተነሣ የቀረ መስሏቸው የሰው ልጆች ሁሉ ተስፋ እንዳይቆርጡ በነቢያቱ እያደረ ትንቢት አናግሯል፡፡ በዚህ ሁሉ መላእክት ትንቢቱን ለነቢያት ይገልጡ ዘንድ እየተላኩ ይነግሯቸው ነበር፡፡

**ፎ.ከክርስቶስ ልደት እስከ ዕለተ ምጽአት፡-** በአዳም መውደቅ ምክንያት የሰውና የመላእክት ማኅበር ተቋረጠ፤ አዳም በመውደቁ እጅግ አዘነ፤ መሐሪው እግዚአብሔር በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ አዳምን ሊያድን ቃል ገባ፤ የትንቢቱን ቃል መላእክት እየገለጹላቸው ነቢያት ትንቢትን ተናገሩ፡፡ ስለዚህ የተቋረጠው ማኅበር ዳግም እንዲመሠረት፣ ለነቢያት የገለጹት ትንቢት እንዲፈጸም፣ ፈጣሪያቸውን በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ እንዲያዩት የእግዚአብሔርን ሰው መሆን ከአዳም እና ከልጆቹ ባልተናነሰ መላእክትም ይሹት ነበር፡፡

በመሆኑም ጥንት አዳም በገነት ሳለ የነበረው የመላእክትና የሰው ልጆች ግንኙነት ዳግመኛ የተመሠረተው ጌታችን በቤተ ልሔም በተወለደ ጊዜ ነው፡፡ ቅዱስ ዳዊት "የመላእክትንም እንጀራ የሰው ልጆች በሉ" (መዝ.፸፯፥፳፭) በማለት እንደተናገረው በቤተ ልሔም እረኞች ከመላእክት ጋር "ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ፤ ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን፤ ሰላምም በምድር ለሰው ልጅም በጎ ፈቃድ ሆነ" ብለው በአንድነት አመሰገኑ (ሉቃ.፪፥፲፬)፡፡ ነቢዩ ዳዊት እንደ ተናገረው የመላእክት እንጀራ የሆነው ምስጋና የእንጀራ ቤት በተባለችዋ በቤተ ልሔም በአንድ መሶብ ቀርቦ እረኞቹ ከመላእክት ጋር ተመገቡት፡፡

ከሦስቱ አካል አንዱ አካል ወልደ እግዚአብሔር በተለየ አካሉ፣ በተወላዲነት ግብሩ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ሰው በመሆኑ ሰባቱ መስተፃርራን ታረቁ፡፡ ሰባቱ መስተፃርራን የተባሉት ሰውና እግዚአብሔር፣ ሰውና መላእክት፣ ሕዝብና አሕዛብ፣ ነፍስና ሥጋ ናቸው፡፡ ከሰባቱ መስተፃርራን መካከል ሁለቱ ሰውና መላእክት ናቸው፡፡ በክርስቶስ ልደት ታርቀው ጥንት የነበራቸው ኅብረት ተመልሶ በአንድ ማኅበር ሆነው እግዚአብሔርን ማመስገን ጀመሩ፡፡

ይህ ግንኙነት በገነት በዐጸደ ነፍስ ላሉት ፍጹም ነው፤ በዚህ ምድር በዐጸደ ሥጋ ላለን ሰዎች ግን እንደ ሰዎች የሃይማኖት ጽናት፣ እንደ ተጋድሏችን ብርታት፣ እንደ ቅድስናችን ይወሰናል፡፡ ሃይማኖታቸውን አጽንተው፣ በበጎ ምግባር ተግተው በተጋድሎ በትሩፋት ሠልጥነው የሚኖሩ ሰዎች መላእክትን ለማየት ይበቃሉ፤ መላእክትን ማየት ብቻ ሳይሆን ለምን አገልግሎት እንደሚላኩም ለማወቅ ይበቃሉ፤ ከዚህ ሲያልፍ ደግሞ እንደ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ ጋር አብረው የሥሉስ ቅዱስን መንበር ለማጠን ይታደላሉ፡፡

ኅዳር ሃያ አራት ቀን የካህናተ ሰማይ ዓመታዊ በዓል መታሰቢያ ነው፡፡ ይህ ዕለት ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከካህናተ ሰማይ ጋር አብረው የሥላሴን ዙፋን ያጠኑበት በመሆኑ የጻድቁ በዓልም ይከበራል፡፡ ይህንንም ገድለ ተክለ ሃይማኖት "ይህቺ ታላቅ ጸጋ ክብር ትሰጠኝ ዘንድ እኔ ምንድን ነኝ? አልሁት፡፡ እግዚአብሔር ለወደደው ባለሟልነትንና ክብርን ይሰጣልና ነው አለኝ፡፡ ከዚህ በኋላ ወደ ሰማይ አውጥቶ ከመጋረጃው ውስጥ አስገብቶ ከሥላሴ ዙፋን ፊት ለፊት አቆመኝና ሰገድኩለት፡፡ ከዚያ አስቀድሞ በማላውቀው አዲስ ምስጋና አመሰገንኩት፡፡ ተክለ ሃይማኖት ክፍልህ ከሃያ አራቱ ካህናቶቹ ጋር ይሁን የሚል ቃል ከዙፋኑ ውስጥ ወጣ፡፡ የወርቅ ጽና አምጥተው ሰጡኝና ከእነርሱ ጋር በአንድነት አጠንሁ፡፡ ምስጋናዬ ከምስጋናቸው ጋር ልብሴም እንደ ልብሳቸው ሆነ፤ ፈጣሪዬንም በሦስትነቱ ተገልጾ አየሁት" በማለት ያስነብበናል(ገድለ ተክለ ሃይማኖት፣ ገጽ ፪፻፲፱)፡፡

**፬. ከትንሣኤ ዘጉባኤ በኋላ፡-** ሕያወ ባሕርይ እግዚአብሔር ሕያው ሆነው እንዲኖሩ ሰውንና መላእክትን ፈጥሯቸዋልና አዳም በገነት በነበረበት ጊዜ ከነበራቸው፣ ከገነት ከተባረረበት ወደ ገነት ተመልሶ እስከሚገባበት ጊዜ ከነበራቸውና ከልደተ ክርስቶስ በኋላ እስከ ትንሣኤ ዘጉባኤ ከሚኖራቸው ግንኙነት በተለየ አንድነት ወይም ማኅበር እስከዚህ ለማይባል ዘመን እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ዘለዓለማዊ በሆነው ምስጋናቸው ይኖራሉ፡፡ ይህ ሕይወት ለመላእክት ሳይቀር አዲስ ልደት ይባላል፡፡

ጉዳዩን አረጋዊ መንፈሳዊ "አኮ ሥጋውያን ባሕቲቶሙ እለ ይጼውዑ ለዝንቱ ልደት መንክር ወምሥጢር ዘኢይተረጐም፤ ዓዲ ጠባይዕ መንፈሳውያን ይፈቅድዎ በጠባይዖሙ ለዝንቱ ልደት ሐዲስ፤ እስመ ይትመከዓብ ፈድፋደ፤ ወይከብር እምነ ህላዌሆሙ ዘይእዜ፤ ወአምሳለ ፈጣሪሆሙ ይነሥኡ፤ እሉሂ ወእልክቱሂ በአሐዱ ጉባዔ፤ ወአልቦ ፍልጠት ማእከሌነ ወማእከሎሙ፤ የማይመረመር ድንቅ የሚሆን ልደትን የሚሹት ሥጋውያን ጻድቃን ብቻ አይደሉም፡፡ ይህን ሐዲስ ልደት መላእክትም በባሕርያቸው ይሹታል እንጂ ፡፡ ይህ ልደት ኋላ በትንሣኤ ዘጉባኤ የሚወለዱት ልደት ነው፡፡ የልጅነት ክብር ዕጽፍ ሆኖ ይሰጣቸዋልና፤ ከዛሬ አነዋወራቸው የኋላ አነዋወራቸው ይከብራልና፡፡ ፈጣሪያቸውን መምሰልን ገንዘብ ያደርጋሉና፡፡ ጻድቃንም መላእክትም በአንድ ዓለም ይኖራሉ፡፡ በመላእክትና በእኛ መካከል መለየት የለም" (አረጋዊ መንፈሳዊ፣ ድርሳን ፲፱)፡፡

ትንሣኤ ሙታን መኖሩን ማመን ተቸግረው የነበሩት ሰዱቃውያን ሙታን ይነሣሉ ከተባለ አንዲት ሴት በምድር ላይ ወንድሙ ሲሞት ወንድሙ እያሉ ሰባቱም ወንድማማቾች አገቧት፡፡ በመንግሥተ ሰማያት ለማንኛው ትሆናለች? በማለት ከፈሪሳውያን ጋር በተከራከሩና ጥያቄውን ይመልስላቸው ዘንድ ወደ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሄዱ ጊዜ "ሙታንስ በሚነሡበት ጊዜ እንደ እግዚአብሔር መላእክት

ሆነው ይኖራሉ እንጂ አያገቡም፤ አይጋቡምም" (ማቴ.፳፪፥፴) ብሎ መለሰላቸው። ይህ ቃል በመንግሥተ ሰማያት ጻድቃን ከመላእክት ጋር አንድ ሆነው እግዚአብሔርን እያመሰገኑ በዘለዓለማዊ ደስታ ጸንተው የሚኖሩ መሆናቸውን የሚያስረዳ ነው።

**አንድነት በምን?**

**፩.በግእዛነ አእምሮ (ለባዊነት፣ ነባቢነት፣ ሕያውነት)፡-** ኦሪት ዘፍጥረትን የተረጐሙ ሊቃውንት "ብርሃን ይሁን" ብሎ በመናገር የፈጠረበትን ምክንያት ሲተረጕሙ ጌታ መላእክትን ሕያዋን፣ ለባውያንና ነባብያን አድርጎ ፈጥሯቸው ነበርና ግእዛነ አእምሮ ያላቸው ሰማዕያን ፍጥረታትን ስለፈጠረ በመናገር ፈጠረው ብለዋል። እንዲሁ በዚሁ ምዕራፍ "እግዚአብሔር ሰውን በአርአያችንና በአምሳላችን እንፍጠር" (ዘፍ.፩፥፳፮) ያለውን ሲተረጕሙ "ሥላሴን በምን እንመስላቸዋለን ቢሉ ሥላሴ ለባውያን፣ ነባብያን፣ ሕያዋን ናቸው፤ እኛም በነፍስ ለባውያን፣ ነባብያን፣ ሕያዋን ነን" ብለው አትተዋል። ከዚህ በመነሣት ሰውና መላእክት በምን ይመሳሰላሉ ከተባለ በለባዊነት፣ በነባቢነትና በሕያውነት መመሳሰላቸውን መረዳት ይገባል። ስለዚህ ሰውም፣ መላእክትም በተሰጣቸው አእምሮ አዋቂዎች፣ አሳቢዎችና ተናጋሪዎች በመሆናቸው ሕያዋን ሆነው ለዘለዓለም ይኖራሉ።

**፪.በምስጋና፡-** ሊቁ ቅዱስ አትናቴዎስ "ወረሰዮ ድልወ ይትቀነይ ሎቱ ወይትለአኮ ከመ መላእክት፡- ያገለግለው ዘንድ እንደ መላእክትም ይላላከው ዘንድ አዘጋጀው" (ሃ.አበው ፳፰፥፴፫) በማለት እንደተናገረው መላእክት ስሙን ቀድሰው፣ ክብሩን ወርሰው ይኖሩ ዘንድ እንደ ተፈጠሩ፣ ያለማቋረጥም ፈጣሪያቸውን ሲያመሰግኑ እንደሚኖሩ የሰው ልጅም እግዚአብሔርን በማመስገን ከመላእክት ጋር ይመሳሰላል። በመጽሐፍ ቅዱስ "ረቂቅ የምትሆን አንተ ከእሳት ነበልባልና ከነፋስ የፈጠረህን ፈጣሪ ነኝ በማለት በታበይህ ጊዜ ፣ አንተም በተመካህ ጊዜ እግዚአብሔር ክፉ ሥራህን ተመለከተ፤ ሳያጓድል ስሙን ያመሰግን ዘንድ በአንተ ፋንታ የሚያመሰግን አዳምን ፈጠረው፤ አንተ ከሠራዊቶችህ ጋራ እግዚአብሔርን ክደሃልና" ተብሎ ተጽፏል (፫ኛ መቃ. ፪፥፲)። ምንም እንኳን እግዚአብሔር የሚያመሰግነው አጥቶ የጎደለበት ነገርም ኖሮ ይሞሉለት ዘንድ የፈጠራቸው ባይሆኑም የተፈጠሩት ግን ስሙን ቀድሰው፣ ክብሩን ይወርሱ ዘንድ ነው።

የሰውንም ሆነ የመላእክትን የመፈጠር ዓላማና መመሳሰል በግልጽ የሚያስረዳ አንድ ተጨማሪ ማስረጃ "እግዚአብሔርን የሚወዱ ግን እንደ ቅዱሳን መላእክት ለእርሱ ወገኖቹ ይሆናሉ፤ የሚያመሰግኑት ሱራፌልና ኪሩቤልም ክንፎቻቸውን ዘርግተው ያለማቋረጥ ያመሰግናሉ። አንተ ግን በመልክህ ከተፈጠሩ ከነገድህና ከሠራዊትህ ጋር ሁል ጊዜ ታመሰግነው ዘንድ ምስጋናህን በትዕቢትህና በስንፍናህ አጠፋህ። እንዳንተ ያለ መፍጠር የማይቻለው መስሎህ አንተ የፈጠረህን የእግዚአብሔርን ምስጋና በዘነጋህ ጊዜ አሥረኛ ነገድ አድርጎ የፈጠረህ የእግዚአብሔር ምስጋናው እንዳይጎድል... ከሠራዊቶችህም ጋር ወደ ገሃነም እንቅጥቅጥ ባጋዘህ ጊዜ በቅዱሳት እጆቹ ከምድር መሬትን ወሰደ፤ ውኃንና እሳትን ነፋስንም ጨመረ፤ አዳምንም በመልኩና በምሳሌው ፈጠረው። ምስጋናው በአንተ ጉድለት ይመላ ዘንድ በእጁ በፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ላይ ሾመው። የመሬታዊውም ምስጋና ከሰማያውያኑ ምስጋና ጋር ተጨመረ፤ ምስጋናቸውም እኩል ሆነ" በማለት ያስነብበናል (፫ኛ መቃ. ፬ ፥፮-፲፩)። ከላይ የተጠቀሰውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ስንመለከተው ሰውና መላእክት እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ዘንድ እንደ ተፈጠሩና በዚህ ተግባራቸውም እንደሚመሳሰሉ እንረዳለን።

**፫.በንጽሕና (በጥንተ ተፈጥሮ)፡-** ሰዎች ከመላእክት ጋር በንጽሕና ይመሳሰላሉ ወይም አንድ ናቸው ሲባል ሰዎች ከውድቀት በኋላ የኖሩትን ሕይወታቸውን በማሰብ አይደለም። የአዳምን ጥንተ ተፈጥሮ ስንመለከት ንጹሐ ባሕርይ እግዚአብሔር ስሙን ቀድሶ፣ ክብሩን ወርሶ የሚኖር ንጹሕ ፍጥረትን ፈጥሯል። ይህንንም ሄኖክ "እንደ መላእክት ጻድቃንና ንጹሓን ሆነው ይኖሩ ዘንድ ነው እንጂ፤ ሰው ለእንደዚህ ያለ ሥራ አልተፈጠረም ነበርና፤ በቀይ ቀለምና በጥቁር ቀለምም ሃይማኖታቸውን ሊያጸኑ ሰው ለእንደዚህ ያለ ሥራ አልተወለደም ነበርና" በማለት ይገልጸዋል (ሄኖ.፲፱፥፳፬)። ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስም ለኤፌሶን ምእመናን በላከው መልእክቱ "ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳን፣ ንጹሓንና ያለ ነውር በፍቅር ያደርገን ዘንድ ለእርሱ መረጠን፤ በኢየሱስ ክርስቶስም እንደ ውድ ፈቃዱ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን" (ኤፌ.፩፥፬-፭) በማለት ከሄኖክ አሳብ ጋር ተመሳሳይ የሆነ መልእክት ጽፎልናል። ስለዚህ ጥንት በንጽሕና በቅድስና በመፈጠር መላእክትን እንመስላቸዋልን። በጥንተ ተፈጥሮ በንጽሕና በቅድስና በአርአያውና በአምሳሉ እንደ ፈጠረው ሁሉ ከትንሣኤ ዘጉባኤ በኋላ እንደ መላእክት ንጹሕ ሆኖ ይኖራል።

ሰዎች በንጽሕና መላእክትን የመሰሉት ከአዳም ውድቀት በፊትና ከትንሣኤ ዘጉባኤ በኋላ ባለው ሕይወታቸው ብቻ አይደለም። ከሦስቱ አካል አንዱ ወልድ በአጭር ቁመት፣ በጠባብ ደረት ተወስኖ፣ በዚህ ዓለም ተገልጦ ሰባቱን መስተፃርራን ካስታረቀና የሰውን ልጅ በሐዲስ ተፈጥሮ በልጅነት ከአከበረ በኋላ እግዚአብሔር እንጂ እኛ ቆጥረን የማንጨርሳቸው ቅዱሳን በንጽሕና፣ በቅድስና በመኖር መላእክትን መስለዋል። በንጽሕናውና በቅድስናው የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ያከበረው ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ (ራእ.፳፪፥፰)፤ "ከመ መላእክት ይመስል ሕይወቱ፤ ሕይወቱ መላእክትን ይመስላል" (ቅዱስ ያሬድ፣ መጽሐፈ ዚቅ) የተባለ እንደ አባ ገሪማ ያለውን፤ "መልአክኑ ሰማያዊ ወብእሲ ምድራዊ፤ ሰማያዊ መልአክ ነውን ወይስ ምድራዊ ሰው" ተብሎ የተደነቀውና ስድስት ክንፍ የታደለው ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት እና ሌሎችም በንጽሕናና በቅድስና መላእክትን መስለዋል።

በአጠቃላይ "ጻድቃንም፣ መላእክትም በአንድ ዓለም ይኖራሉ" በማለት አረጋዊ መንፈሳዊ የተናገረው መላእክት የእግዚአብሔርን ስም ቀድሰው፣ ክብሩን ወርሰው ይኖሩ ዘንድ እንደ ተፈጠሩ ሁሉ የሰው ልጅም ለዚሁ ግብርና ክብር የተፈጠረ እንደ ሆነ ምንም እንኳን ጥንት ባጠፋው ጥፋት ከገነት ቢባረርም፣ ባሕርየ ተፈጥሮው ሞተ ሥጋ የሚስማማው ቢሆንም በዚች ምድር ሲኖር በስመ ሥላሴ አምኖ የተጠመቀ፣ ልጅነቱን ጠብቆ፣ ሃይማኖቱን አጽንቶ፣ በበጎ ምግባር ሲመላለስ የኖረ ክርስቲያን ሁሉ፣ በትንሣኤ ዘጉባኤ እንደ መላእክት ሕያው ሆኖ እግዚአብሔርን እያመሰገነ በመንግሥተ ሰማያት የሚኖር መሆኑን አስረድቶናል። አምላካችን እግዚአብሔር ከመላእክት ጋር አንድ ሆነን ስሙን ለመቀደስ፣ መንግሥቱን ለመውረስ ያብቃን። አሜን!!⌖

# የቤተ ክርስቲያን የዘመን ክሥተቶች

## ክፍል አንድ

ዲ/ን አሻግሬ አምጤ

ዘመን አሳይቶን የሚያርፍባቸው ተወርዋሪ ኮከቦች ለዘለዓለም በትውልድ አእምሮ ውስጥ ታትመው ይኖራሉ፡፡ መልካም ሥራቸው ሲነገረን “ምነው እነርሱን ባደረገን” ብለን ምኞት ያድርብናል፡፡ ከቤተ ክርስቲያን የጎደለ ነገር ባይኖርም የተመልካቾች ዓይን መመልከት ተስኖት የኖረውን በዚህ ዘመን የተነሡ አባቶች ትውልዱ ዕይታውን እንዲያስተካክል አድርገውታል፡፡ በዘመናችን ተፈጽሞ ያየነውና የሰማነው በእኛ ዘመንም እንዲህ ይደረጋል እንዴ የሚያሰኝ ነው፡፡ ከሐምሌ ወር ፳፻፲፫ ዓ.ም ጀምሮ በጦርነት ቀጠና ውስጥ የከረሙት በጥንቱ ወሎ ጠቅላይ ግዛት በሚገኙ አራት አህጉረ ስብከት የሚኖሩ ክርስቲያኖች በስንክሳር መጽሐፍ ገድላቸው ተጽፎ ያነበብነውን ሰማዕትነት የሚተካከል ነው፡፡

በተካሄደው ጦርነት ትውልዱ ቅስሙ ተሰብሮ፣ ሥነ ልቡናው ተሰልቦ እንዳይቀር አባቶቻችን ሃይማኖት ሳይለዩ፣ የቋንቋ ልዩነት ሳያደርጉ ሰውን ሁሉ እኩል ሲያጽናኑና ሲያገለግሉ ከርመዋል፡፡ የአባቶቻችን ተግባር መንግሥት ባይኖር ኢትዮጵያ የምትበተን ለሚመስላቸው የዋሃን ግምታቸው የተሳሳተ መሆኑን እንዲመረምሩ የሚያደርግ ነው፡፡ የሚያስገርምው ነገር በደቡብ ወሎ፣ በሰሜን ወሎ እና በዋግኽምራ የተከናወነው ተግባር መመሳሰል ነው፡፡ በሁሉም ማለት ይቻላል የሰላም ኮሚቴ ተቋቁሞ በአገር ላይ ከደረሰው የከፋ ጉዳት እንዳይደርስ ማድረጋቸው ነው፡፡ በወቅቱ አካባቢውን ተቈጣጥሮ የነበረውን ታጣቂ ወገናችሁን ለምን ትጨፈጭፋላችሁ ብለው ፊት ለፊት እስከ መጋፈጥ መድረሳቸው ሰው ሃይማኖተኛ ከሆነ ከእግዚአብሔር ውጭ የሚፈራው አካል አለመኖሩን ማሳያ ነው፡፡

ከታኅሣሥ ፳፪ እስከ ታኅሣሥ ፳፯ ቀን ፳፻፲፬ ዓ. ም ድረስ የማኅበረ ቅዱሳን ጽሕፈት ቤት ከገቢ አሰባሳቢ ኮሚቴው ጋር ጋዜጠኞችን ያካተተ ድጋፍና ጉብኝት ከደቡብ ወሎ እስከ ዋግ ኽምራ ድረስ አድርጎ ነበር፡፡ በጉብኝቱ ያረጋገጥኩት ነገር ቢኖር ክርስቲያኖች በደረሰው መከራ ተስፋ ከመቁረጥ ይልቅ “ተምረንበታል” ብለው ሲናገሩ መሰማታቸውን ነው፡፡ በዚህ የመከራ ወቅት እንዲህ ዓይነት የሞራል ልዕልና ማግኘት እግዚአብሔርን “ሥራህ ድንቅ ነው” ብለን እንድናመሰግን የሚያደርግ ነው፡፡ ራሱ እየተራበ ያለውን ለወገኑ ሲሰጥ የከረመ ክርስቲያን አይተናል፡፡

ክርስቲያኑና ሙስሊሙ ተደጋግፎ መከራውን ለማቅለል መሥዋዕትነት ሲከፍል መክረሙንም ተመልክተናል፡፡ ከንጋቱ አሥራ አንድ ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ አንድ ሰዓት ድረስ በየቤቱ እያንኳኩ ረሃብ የጸናባቸውንና ወልደው የተኙትን እናቶች እየፈለጉ ድጋፍ ሲያደርጉ የከረሙ አባቶች መኖራቸውን ከክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆን ከሙስሊሞችም ሲነገር ሰምተናል፡፡ ክርስትና የመከራ ጉዞ መሆኑ ይታወቃል፡፡ የአባቶችን አበርክቶ ቀሲስ ይኸነው መልኩ የገለጡት “በመከራ ዘመን ራስን ለሕዝብና ለሀገር አሳልፎ የሚሰጥ አባት ያስፈልጋል፡፡ ‘ያለኝ ይበቃኛል’ የሚለውን የወንጌል ቃልም በሕይወት መተግበር ይገባል፡፡ ይህንንም በወቅቱ በነበረው ችግር በተግባር የገለጡት ክርስቲያኖች ብዙ ናቸው፡፡ ማንም ሰው በረሃብና በመድኃኒት ማጣት መሞት የለበትም በማለት ሰዎች በረሀብና በሕክምና እጥረት እንዳይሞቱ ጥረት አድርገዋል፡፡ የክርስቲያኖች መሪ ወይም የበጎች እረኛ የሆነው ካህን በጎቹ እንዳይበተኑ፣ እንዳይራቡና በችግር እንዳይሞቱ የማድረግ ሃይማኖታዊም፣ ሞራላዊም ኃላፊነት አለበት” ብለዋል፡፡

አያይዘውም “ከተቻለ ጦርነቱ እንዳይካሄድና በሰዎችና በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንዳያደርስ መምከር፣ መገሠጽና ማውገዝ የካህናት ኃላፊነት ነበር፤ ካልሆነ ደግሞ በጦርነቱ የከፋ ችግር እንዳይከሠት መከላከል፣ ከተከሠተም በተቻለ መጠን የፈረሰውን መልሶ ለመጠገን መጣር፣ የተራበውን ማብላት፣ የተጠማውን ማጠጣት፣ የሞተውን መቅበር፣ የታረዘውን ማልበስና የሕክምና እጦት ያለበትን ችግሩ እንዲወገድ መሥራትና ለችግሩ ደራሽ የሚሆኑ ወገኖችን ማነሣሣት የአባቶች ግንባር ቀደም ኃላፊነት መሆን አለበት” ብለዋል፡፡ ጦርነቱ በሀገርና በቤተ ክርስቲያን ላይ ከፍተኛ ውድመትና ውድቀት አስከትሏል፡፡ ውድመቱ ከደረሰ በኋላም ኦርቶዶክሳውያን አባቶች የተጎዱ ወገኖችን በቻሉት ሁሉ ሲደግፉ ቆይተዋል፡፡ ለዚህም የሰሜን ወሎ፣ የደቡብ ወሎና የከሚሴ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ኤርምያስ፣ የዋግኽምራ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ በርናባስና የደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ የእውነተኛ አባትነት ምስክሮች ናቸው፡፡ አባትነትን በተግባር አሳይተዋልና፡፡ ደግነት የአባቶቻችን የዕለት ተዕለት ተግባራቸው ቢሆንም በዚህ ክፉ ዘመን ያሳዩት ቆራጥነት ደግሞ በታሪክ ሲታወስ የሚኖር ታላቅ ተግባር ነው፡፡

በዚያ ክፉ ጊዜ ምእመናን የሚያጽናናቸው ቤተ ክርስቲያንም የሚጠብቃት በሚፈልጉበት ወቅት አባቶቻችን የፈጸሙት አባታዊ ተግባር ለትውልድ መልካምነትንና ከራስ በላይ ለሌሎች መኖርን የሚያሳይ ነው፡፡ በመገናኛ ብዙኃን ሲነገር የሚሰማው ስለክፉ ነገር ነው፡፡ በቅርብ ጊዜ ብቻ ካልሆነ በስተቀር ስለ አባቶቻችን ደግነት፣ አስታራቂነት፣ አስተማሪነት፣ ደጋፊነት፣ የቁርጥ ቀን አለኝታነት እንዲሁም አሻጋሪነት ሲወራ ሰምተን አናውቅም፡፡ አባቶቻችንም መልካም ተግባራቸውን እግዚአብሔር እንዲቀበልላቸው እንጂ የሰው ልጅ ዕውቅና ወይም ሽልማት እንዲሰጣቸው አይሹም፡፡

የአባቶቻችን መልካም ተግባርም በጊዜ ሂደት እየተገለጠና ሥራቸው ምስክር እየሆነ የሚመጣ እንጂ በሚዲያ ወይም በሰው አንደበት የሚነገር ወይም የሚወደስ አይደለም፡፡ በሌሎች ዘንድ ለአባቶቻችንና ለቤተ ክርስቲያናችን የሚሰጠው እይታም ከዚህ ቀደም የተዛባ ነበር፡፡ ይህ ማለት አባቶቻችንም ሆኑ ቤተ ክርስቲያናችን ለወገንና ለሕዝብ የሚጠቅም ሥራ ሳይሠሩ

ቀርተው አይደለም። ነገር ግን ስላልተገለጠ ትውልዱ ሳያየው ቆይቷል። በጦርነት ወቅት አባቶቻችን ያደረጉት ተጋድሎ በሚዲያ መገለጡና በሕዝብ ዘንድ መታወቁ በአማንያንም ሆነ በኢ-አማንያን ዘንድ ለአባቶችም ሆነ ለቤተክርስቲያን ያለው በጎ ያልሆነ አመለካከት እንዲቀየር አድርጓል።

በሦስቱም አህጉረ ስብከት ሊቃነ ጳጳሳት አስተባባሪነት የሰላም ኮሚቴ ተቋቁሞ በየአካባቢው ሊደርስ ይችል የነበረውን መከራ በመጠኑም ቢሆን ለመቀነስ ተችሏል። በመንግሥትና በግል የሕክምና ተቋማት ይሠሩ የነበሩ የሕክምና ባለሙያዎችን አሰባስበው ሕይወት የመታደግ ተግባር እንዲፈጽሙ አድርገዋል። ይህ ተግባር በአንድ በኩል ለቤተ ክርስቲያን አባቶች ክብር ሲሰጥ በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ ተግባር ያለፉ ባለሞያዎች የመንፈስ ርካታ እንዲያገኙ ምክንያት መሆኑን ከደሴ ከተማ ያገኘናቸው የሕክምና ባለሞያዎች ገልጠውልናል። የየአህጉረ ስብከቱን ክራሞትና የክርስቲያኖችን በቃላት ተነግሮ የማይጠቃለል በጎ ምግባር በአጭሩ ያቀረብነው በሚከተለው መንገድ ነው።

### ደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት

የደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት መቀመጫ ከሆነችው ደሴ እንደ ደረስን የሰማነው ነገር ቀጣዩን ለመስማት ጉጉት የሚያሳድር ነበር። ጦርነቱ ወደ አካባቢው መቅረቡን የተረዱት የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ "የሚመጣውን ከበጎቼ ጋር እቀበላለሁ" ብለው ከአዲስ አበባ ወደ ደሴ ሄደው ሲፈጽሙ የከረሙት የእረኝነት ተግባር ቅዱስ አትናቴዎስ በዘመናችን ዳግም መነሣቱን የሚያስገነዝብ ነው። ከየአቅጣጫው ይሰሙት የነበረው የነፍስ ጡሮች ለተጨማሪ ሥቃይ መጋለጥ አባታችንን አንድ ነገር እንድያደርጉ አስገደዳቸው።

በማኅበረ ቅዱሳን ደሴ ማእከል አስተባባሪነት ነፍሰ ጡሮችን ከሞት የመታደግ ክርስቲያናዊ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ በከተማዋ የነበሩ ሐኪሞች በአባታችን ሲጠየቁ የሕክምና ባለሞያዎች መልስ "እርስዎ አዝዘውን የማንፈጽመው ተግባር፣ የማናከናውነው ሥራ የለም" የሚል ነበር። የክርስትና እምነት ተከታይ ሐኪሞች በበኩላቸው በሃይማኖት የማይመስሏቸውን የሌሎች ሃይማኖት ተከታይ የሞያ አጋሮቻቸውን በየቤታቸው ሄደው እያንኳኩ "በዚህ የመከራ ጊዜ ለወገናችን ካልደረስን መቼ ልንደርስለት ነው?" እያሉ አሳብ ሲያቀርቡላቸው የሕክምና ባለሞያዎችም ፈቃደኛ ሆነው ብዙ እናቶችን አዋልደዋል። ጊዜ የማይሰጥ በሽታ የታመሙ ወገኖቻቸውን እየተከታተሉ የመከራውን ዘመን መልካም ተግባር በመፈጸም አሳልፈዋል።

በመንበረ ጵጵስናቸው በተገኘንበት ወቅት ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ የሚገርም ነገር አጫወቱን። ከመካከላችን አንዱ ማኅበረ ቅዱሳን ያደረገውን ድጋፍ ሲነግራቸው ብፁዕነታቸው የመለሱት "ችግሩን ማን ነገራችሁ? ኢትዮጵያውያን የሚሰጡት ያላቸውን ነው። ስጦታቸውም ሕይወት የሚቀጥል ነገር ነው። ፈረንጅ የሚሰጠው ግን ነፍስ የሚያሳድር እንጂ ሕይወት የሚሰጥ አይደለም። እንዳይበቅልና ሕይወት እንዳይቀጥል የተቀቀለ ነው። ሰው የሚያቀርበው ስጦታ ብዙም ይሁን ትንሽ ማለቁ አይቀርም። የማያልቀው በጎ አሳቡ ነው። በመከራችን ጊዜ 'እንዲህ አደረጉልን' የሚለው አስተሳሰብ በሰዎች አእምሮ ታትሞ ይኖራል። ብዙ ጊዜ ግሸን ማርያም ስሔድ የምመለከተው የእናቶቻችን ድርጊት ሲያስገርመኝ ይኖራል። ያላቸውን ሰጥተው ባዶ እጃቸውን የሚመለሱ፣ ነጠላቸውን ከላያቸው አንሥተው ለባለሰበት አልብሰው ቀሚስ ብቻ ለብሰው በዓሉን አክብረው ወደ ቤታቸው የሚመለሱ እናቶችን እመለከት ነበር። እንዲህ ያለውን ከራስ በላይ ወገንን መውደድ ከኢትዮጵያ ውጭ ሲፈጸም አታዩም" ብለዋል።

ብፁዕነታቸው በመቀጠል "በሌሎች አገሮች የምንሰማው በታሪክ ተፈጽሞ የነበረ መሆኑን እንጂ በዘመናችን በተግባር ሲፈጸም አይታይም። ኢትዮጵያውያን ይህን ብቻ ሳይሆን የበለጠም ሲፈጽሙ ይታያሉ። እናቶቻችን በቤታቸው አንድ እንጀራ ቢኖራቸው ግማሹን ለራሳቸው አስቀርተው ግማሹን ቆርሰው ለተራበ ሲመጸውቱ 'ምን እንበላለን? ለልጆቻችንስ ምን እንሰጣለን?' ብለው መጠራጠር አያውቁም። በእምነት የሚሰጡት አምላክ በእምነት እንደሚሰጣቸው አሳምረው ያውቁታል። ዘንድሮ የተፈጸመውም እናቶቻችን ሲፈጽሙት የኖሩትን ገሀድ የሚያወጣ ነው። ብዙ እናቶች ሲያደርጉት የተመለከትነው እንዲህ አይነት ተግባር ነው። ማኅበረ ቅዱሳንም ያደረገው እንደ ጠቀስኳቸው እናቶች ነው። ሲኖረው ከራሱ አውጥቶ ለተቸገሩት ይሰጣል። ሲያጣ ካላቸው ሰዎች ለምኖ በችግር ላይ ለሚገኙ ወገኖቻችን ያቀርባል። እንደምታውቁት እኔ ረጅም የጵጵስና ዘመኔን ያሳለፍኩት ውጭ ሀገር ነበር። ውጭ ሀገር በአገልግሎት ላይ ሳለሁ በጠና ታምሜ ነበር። መታመሜን የሚያውቁ ክርስቲያኖች ስልሳ ስምንት ሺህ ዶላር አዋጥተው 'ታከምበት' ብለው ሰጡኝ። ክርስቲያኖች ለአባታችን ብለው መልካም ሲሠሩ እኔስ ለምን መልካም አልሠራም ብየ አሰብኩ። አዋጥተው በሰጡኝ ገንዘብ ብታከምም ላልድን እችላለሁ። ለጊዜው ሕመሙ ቢተወኝ እንኳ ተመልሶ ሊመጣ ይችላል። ብዙ ዘመን ለማልኖረው ለምን በገንዘቡ የማይሞት ሥራ ሠርቼበት አላልፍም ብዬ አሰብኩ። በገንዘቡ ምን መሥራት እንዳለብኝ አውጥቼ አውርጄ ታሪካዊው የሐይቅ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ቤት ለዘመናት ተዘግቶ መኖሩ ታወሰኝ" ብለዋል።

ብፁዕነታቸው በሚጣፍጥ ትረካቸው "ከስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክ እስጢፋኖስ ገዳም አብነት ትምህርት ቤት መዘጋቱን መስማት ለአንድ ክርስቲያን አሳዛኝ ነገር ነው። አባ ኢየሱስ ሞዐ በደብረ ዳሞ ገዳም ሲማሩ ኖረው ምንኵስና ተቀብለው በጣም ብዙ መጻሕፍትን ይዘው ወደ ሐይቅ እስጢፋኖስ ሔደው ጉባኤ ከፍተው ማስተማር ከጀመሩ በኋላ እስከ ግራኝ አሕመድ መነሣት ድረስ ጉባኤው ሳይቋረጥ ቀጥሎ ኖሯል። በረጅም ዘመን አገልግሎቱም ለቍጥር የሚያታክቱ ሊቃውንትን አፍርቷል። እንዲህ ዓይነት ታሪክ የነበረው ጉባኤ ቤት ተዘግቶ መቅረቱ ዕረፍት ስለነሣኝ ማስከፈት አለብኝ ብዬ አሰብኩ። ራሴም እንጨት እየተሸከምኩ ተሠርቶ ተጠናቆ ጉባኤ ቤቱ አገልግሎት መስጠት ጀመረ። አዳሪ ትምህርት ቤቱ መጀመሪያ ተሠርቶ የነበረው በእንጨት ነበር። ትምህርት ቤቱ አሁን የሚገኝበትን ሁኔታ ራሳችሁ አይታችሁ የምትመሰክሩት

ነው” በማለት አሳባቸውን አጠቃለሉ፡፡ “ዳግሚት ቊስጥንጥንያ” የሚል ቅጽል ተሰጥቶት የነበረው ቦሩ ሜዳ ከወደቀበት ተነሥቶና ከጠፋበት ተመልሶ ወደ ቀደመ ክብሩ እንዲመለስ ያደረጉት ብፁዕነታቸው መሆናቸውን የነገሩን ታሪክ አንድ መንፈሳዊ አባት መሥራት የሚኖርበትን እንድንረዳ ብቻ ሳይሆን አባቶቻችንን ሳናውቃቸው እንዳንተቻቸው ጭምር ትምህርት የሚሰጥ ታሪክን ዳግም የማስቀጠል ተግባር ነው፡፡



ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ

በዚህ የመከራ ዘመንም ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ የተጨነቁትን ከማጽናናት፣ የተራቡትን ከማብላት፣ ተስፋ የቆረጡትን ተስፋ ከማለምለም በተጨማሪ ሐኪሞች በሽተኛ ወገናቸውን እንዲረዱ ያደረጉት አስተዋጽኦ ሲታወስ የሚኖር መልካም ተግባር ነው፡፡ የየአካባቢው ባለሥልጣናት መከራ መምጣቱን አይተው አንጻራዊ ሰላም ወደሚገኝበት ሲሸሹ የእኛ አባቶች ግን ከሕዝባችን ጋር አብረን መከራ እንቀበላለን፣ ሞትም ከመጣ ሰማዕት እንሆናለን ብለው ከሕዝባቸው ጋር መከራ መቀበላቸው የአማናዊ እረኛ ተግባር እንዲህ መሆኑን በተግባር የገለጡበት ነው፡፡

በማኅበረ ቅዱሳን ደሴ ማእከል አስተባባሪነትና በአባታችን መመሪያ ሰጭነት ወገኖቻቸውን ሲታደጉ ከኖሩ የሕክምና ባለሞያዎች መካከል ሲስተር እስከዳር አዝመራው የተባለች ክርስቲያን በደቡብ ወሎ ዞን ከሚገኙ ወረዳዎች ባንዱ ከምትሠራበት ጤና ጣቢያ በመነሣት በቀን ከሃያ አስምት ኪሎ ሜትር ያላነሰ በየገጠሩ በእግሯ እየተጓዘች በመሔድ ስልሳ ስምንት እናቶችን ማዋለዷን ስንሰማ ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን አጋዥ አድርገው ከተነሡ የማይሠሩት ነገር፣የማይቋቋሙት መከራ አለመኖሩን የሚያሳይ እንደሆነ ተረዳን፡፡ በአካል አግኝተን ባነጋገርናት ጊዜ ስለአገልግሎቷ ስትገልጥ “እመቤቴ በእኔ በደካማዋ እጅ መልካም ሥራ ሠራች፡፡ እኔ ይህን ሁሉ ሥራ እንድሠራ ምክንያት የሆነችኝ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት፡፡ ያለምንም መሣሪያ እሊህን ሁሉ እናቶች ያዋለድኩት በእግዚአብሔር ረዳትነት፣ በእመቤታችን ምልጃ እንጂ ካለምንም መሣሪያ ብቻዬን ምን አደርግ ነበር” ብላለች፡፡

ሲስተር እስከዳር አያይዛም “እኔ ይህን ሠራሁ የምለው ነገር የለም፡፡ ዕድሜ ልክ መንፈስን ሲያድስ የሚኖር የአገልግሎት ጥሪ ከቤተ ክርስቲያን ሲደርሰኝ የተቀበልኩት በደስታ ነበር፡፡ በጣም የተደሰትኩበት ነገር ቤተ ክርስቲያናችን በበላይነት እየተከታተለች እንዲህ ዓይነት ወገንን የመታደግ ተግባር መፈጸማችን ነው፡፡ አባቶቻችን በጸሎት እያገዙን እኛ የሕክምና ባለሞያዎች ብዙ ወገኖቻችንን ከሞት የታደግነው እግዚአብሔርን አጋዥ አድርገን ነው፡፡ የአባቶቻችን ጸሎት ባይረዳን ኖሮ ይህን ያህል ሥራ መሥራት ባልቻልንም ነበር” ብላለች፡፡ ሌላዋ የሕክምና ባለሞያ ሲስተር ዘነበች ቆሪቾ በበኩሏ “በአባቶቻችን የአገልግሎት ጥሪ መደረጉ ለክርስቲያኖች ክብር ሲሆን የሌሎች እምነት ተከታዮችም የተሳተፉት በደስታ ነው” በማለት ተናግራለች፡፡

በደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት የተፈጸመው ሌላው ተግባር የአብነት ትምህርት ቤቶችን ለመደገፍ የማእከሉ ልጆችና ሌሎች ክርስቲያኖች ተባብረው የሠሩት አርአያነት ያለው ሥራ ነው፡፡ የደሴ ከተማ ክርስቲያኖች የሐይቅ እስጢፋኖስ የጎባኤ ቤት ተማሪዎች እንዳይበተኑ ያደረጉት ወጣቶቹ በእሳት መካከል እንደሚረማመዱ ቢያውቁም እምነታቸው ግን እሳቱን እንደሚያጠፋው በሙሉ ልብ ያምኑ ነበር፡፡

የአብነት ተማሪዎች አካባቢው በህወሐት ታጣቂዎች ቊጥጥር ሥር ከዋለ በኋላ እያንዳንዷን ዕለት ያሳለፉት በመከራ ነበር፡፡ የአብነት ተማሪዎች “ለረጅም ዘመናት ስንማር ኖረን እንዴት መከራ ገጠመን ብለን እንበታተናለን፤ በቤታችን ያለውን ጥቂት ነገር ለነፍስ ማቆያ እየቀመስን እስከ ኅዳር ፳፯ ቀን የአቡነ ኢየሱስ ሞዐ በዓል እንቆያለን፡፡ ከበዓሉ በኋላ ምንም ለውጥ ካልመጣ የቅዱሱን አባታችንን የኢየሱስ ሞዓን ዓመታዊ በዓል ኅዳር ፳፯ ቀን አክብረን አንድ ላይ ጸሎት አድርሰን እንበታተናለን” ብለው

እስከ ዓመታዊ በዓሉ ድረስ ሲገጥማቸው የሚችለውን መከራ በጸጋ ለመቀበል ቃል ገብተው ፈተናውን ተያያዙት፡፡

የተማሪዎችን ከበዓለ ኢየሱስ ሞዐ በኋላ ሊበታተኑ መወሰን የሰሙት የማእከሉ ልጆች በቅዱሱ አባታችን የበዓል ዕለት የሚችሉትን ነገር አሰባስበው በጠዋት ከገዳሙ ሲደርሱ የተመለከቱት የገዳሙ አበምኔት "በዚህ እሳት ውስጥ ለምን መጣችሁ?" ብለው የተናገሯቸው ለመንፈሳዊ ልጆቻቸው በመሳሳት ነበር፡፡ ከከተማ ለተማሪዎች የሚሆን ነገር ይዘው መሔዳቸው ለአብነት ተማሪዎቹ ተስፋ ቢሆንም ፈተና ሳልለመዱ የከተማ ልጆች እንዳይማረሩ በማለት ነበር አበ ምኔቱ እንዲህ መናገራቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተማሪዎች "ቅዱስ አባታችን ኢየሱስ ሞዐ እስከ ዓመታዊ በዓላቸው አንድ ነገር ካላሰሙን ማሕሌት አድረን፣ በዓላቸውን አክብረን ጸሎት አድርገን እንለያያለን" ብለው መምከራቸው የጻድቁ ጥበቃና በረከት እንደማይለያቸው ጥብዓታቸውን የተመለከተው አምላካችን ከዚያ ለከፋ መከራ አሳልፎ እንደማይሰጣቸው በማመን ነበር፡፡

በዕለቱ የማኅበረ ቅዱሳን አባላት ይዘውላቸው የሄዱትን ነገር ሲያዩ ተማሪዎቹ የተናገሩትን "ከሰማይም ከመሬትም እሳት እየነደደ እያያችሁ በእምነት እኛን ለመርዳት ስትመጡ አይተን እንዴት መከራ ገጠመን ብለን እንበተናለን፡፡ ከእንግዲህ እኛም ያገኘናትን ነገር በቀን አንድ ጊዜ እየቀመስን የሚመጣውን ሁሉ በጸጋ እንቀበላለን፡፡ አሁን ያሳሰበን እናንተ እንዴት ወደ ደሴ እንደምትመለሱ ነው፡፡ እዚህ እንዳትቈዩ ከሰማይ በአየር ቦንብ እየተጣለ በመሆኑ አደጋ ሊደርስባችሁ ይችላል፡፡ እንዳትሄዱ ደግሞ በመንገድ አንድ ነገር ብትሆኑ ጸጸቱን አንችለውም እያልን ነበር፡፡ ያ ቅጽበት ቅሩም ሂዱም ለማለት የማይቻልበት የጭንቅ ቀን ነበር። ድጋፉን ይዘውት የሄዱት የማእከሉ ልጆች ከፊታቸው በአየር ተመትቶ እየተቃጠለ የነበረውን ታንክ ቢመለከቱም በአውሎና በወጀብ ውስጥ መንገድ ያለውን አምላካቸውን ጋሻ አድርገው እየዘመሩ ወደ ፊት ጉዟቸውን መቀጠላቸውንና በሰላምም ደሴ ከተማ መድረሳቸውን" በደሴ ማእከል የገዳማትና የአብነት ትምህርት ቤቶች አስተባባሪ የሆነው ዲ/ን አፈ ወርቅ ነግሮናል፡፡

አበ ምኔቱም ጸሎት አድርገው ጻድቁ "ይከተሏችሁ" ብለው ሲሸኟቸው ወጣቶች በታክሲዋ ዕቃ መጫኛ ላይ ጭምር ተቀምጠው እየዘመሩ መንገድ ሲጀምሩ ከፊታቸው የነበረውን ከባድ መሣሪያ በአየር መትቶ ሲያቃጠለው እያዩም ቢሆን እነርሱ እየዘመሩ ወደ ፊት ይጓዙ ነበር፡፡ ያ ቅፅበት ኮምቦልቻ በመንግሥት ወታደሮች ቊጥጥር ሥር መዋሏን ያረጋገጡት አካባቢውን ይዘውት የነበሩት ታጣቂዎች ደሴን እየለቀቁ ወደ ሐይቅ በጅምላ ይጓዙ የነበረበት ጊዜ ነው፡፡

ፊት ለፊታቸው ደግሞ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሰዎች እየዘመሩ እየመጡ ነው። ድርጊቱ እንግዳ የሆነባቸው ታጣቂዎች አጠገባቸው ሲደርሱ አስቁመው እነማን መሆናቸውን ሲጠይቋቸው ከሐይቅ እስጢፋኖስ ዓመታዊ በዓል አክብረው የሚመለሱ ክርስቲያኖች መሆናቸውን ሲነግሯቸው አንድም አካል ጉዳት ለማድረስ ሳይሞክር እለፉ ብለው እያሻገሯቸው በየቦታው የሚያገኟቸውም በተመሳሳይ እያሳለፏቸው በሰላም ደሴ መግባታቸውን ዲ/ን አፈወርቅ "እግዚአብሔር ከእሳት ካወጣቸው ልጆቹ አንዱ እኔ ነኝ፡፡ ለዚህ ተአምር ከእኔ በላይ ምስክር የለም፡፡ በፊታችን ከባድ መሣሪያ በአየር ተመትቶ ሲነድ አይቻለሁ፡፡ አምላካችን ግን እኛን ከእሳት ውስጥ ነጥቆ አውጥቶ አንጻራዊ ሰላም ከነበረባት ደሴ አደረሰን" በማለት ሲናገር የእግዚአብሔር ሥራ ያስደንቃል፡፡

የሐይቅ እስጢፋኖስ ተማሪዎች ከመምህራቸው ከሊቀ ሊቃውንት ትሕትና ጋር ደሴ መጥተው ከዚያም በደላንታ አድርገው ጎጃም ወይም ጎንደር ሊገቡ የነበረ ቢሆንም አካባቢው በታጣቂዎች በመያዙ ረጅም መንገድ የተጓዙበት እግራቸው ቆሳስሎ መራመድ አቅቷቸው እየተጨነቁ የተመለሱት መምህር ትሕትና ከኮምቦልቻ ዩኒቨርሲቲ ደረቅ እንጀራ ለምነው የተማሪዎቻቸውን ሕይወት ለመታደግ የሚያስችላቸውን ነገር ለማግኘት ወደ ኮምቦልቻ የተጓዙት ዲ/ን አፈ ወርቅን አስከትለው ነበር፡፡ ለምን እንደሄዱ የጠየቃቸው አካባቢውን ተቈጣጥረው የነበሩ ታጣቂዎች አባል ሊያስራቸው ሞክሮ ነበር፡፡

መምህር ትሕትናን ታጣቂዎች ሊያስሯቸው የነበረውም ለአብነት ተማሪዎች የሚሆን ኮቸሮ እንደሚፈልጉ ሲነግሩት ሰላይ መስለውት ነበር፡፡ መምህሩ ኮቸሮ መገኘት አለመገኘቱን ለመጠየቅ መጣሁ ማለታቸው የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እንጀራ አድርቀው ለአብነት ተማሪዎች ይሰጧቸው ስለነበር ነው፡፡ ታጣቂው የተረዳው ግን ለወታደር የሚሰጠውን ደረቅ ራሽን ማለታቸው መስሎት ነው፡፡ እርሳቸው ለማለት የፈለጉት ደረቅ ራሽን ሳይሆን ደረቅ እንጀራ ነው በማለት ዲ/ን አፈ ወርቅ ማብራሪያ ሰጥቶ ሁለቱም ከመታሰር ድነው የፈለጉትን ሳያገኙ ድካም አትርፈው ወደ ደሴ መመለሳቸውንም ዲያቆን አፈ ወርቅ ነግሮኛል፡፡ በደሴ ከተማ በሚገኙ አብያተ ክርስቲያን ከጠዋት እስከ ማታ የሚካሄደው ምሕላና የእናቶች እንባና ሊቃውንትም ሳይታክቱ ማስተማራቸው የመከራውን ሌሊት አሳጥሮላቸው ዛሬ ደሴ በሰላም ውላ ታድራለች፡፡ እንዲህ አይነቱን ታሪክ ሲሰሙት ቀላል ቢመስልም በድርጊቱ አልፈው ትውልድ ሲታደጉበት ግን ይደንቃል። በደሴም ሆነ በሐይቅ የተፈጸመውን ሁሉ ጽፎ መጨረስ ብቻ ሳይሆን ማሰብ አይቻልም፡፡

በቦሩ ሜዳም ተማሪዎች ሁሉ ተበታትነው በጉባኤ ቤቱ የቀሩት አንድ የመጻሕፍተ ሐዲሳት ደቀ መዝሙር መነኵሴ፣ አንድ ዓይነ ሥውርና ሌላ ደቀ መዝሙር ሦስቱ ብቻ ነበሩ፡፡ የችግሩን ጊዜ ያሳለፉትም መነኵሴው ወደ መንደር ወጣ ብለው የሚያስፈልጋቸውን እያመጡ፣ ውኃ ቀድተው እያቀረቡ ዓይነ ሥውሩንና ሌላውን ደቀ መዝሙር እየረዱ ነበር፡፡✢

ይቆየን.....

# መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባልንጀርነት

**ብንያም ወልዱ**

ባልንጀራ ጓደኛ፣ ቢጤ ተብሎ ይፈታል። ሁለቱም ቃላት የሁለት ወይም ከዚያ በላይ ሰዎችን በመውደድ ላይ የተመሠረተ ግንኙት የሚገልጡ ሲሆን በመንፈሳዊ መነጽር ብንመለከተው ደግሞ በሥላሴ አርአያና አምሳል የተፈጠሩ ሁሉ በፍጥረት በመመሳሰላቸው ወገንነታቸውን አንድነታቸውን የሚያሳዩበት ነው። ጓደኝነት መጎዳኘት መጣመድ መተባበር መቀናጀትን አንድ መሆንን ሲያሳይ ቢጤ ደግሞ በኑሮ በዘመን በተግባር መመሳሰልን የሚጠቁም ቃል ነው። የሚታየውንና የማይታየውን የፍጥረቱንና የፈጣሪውን ታሪክ ሁሉ የሚያስረዳን ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚነግረን ቀዳማዊ አባታችን አዳምና ቀዳማዊት እናታችን ሔዋን በተፈጠሩበት ዕለት በተሰጣቸው ቡራኬ ዓለምን መሙላት በጀመሩ ጊዜ፤ የሰው ልጅ እየበዛ፣ የሚኖርበትም እየራቀ ሔዷል። በዚህም ምክንያት በአንድ ቤተሰብ ተወስኖ ይኖር የነበረው የሰው ልጆች ግንኙነት ወደ መንደር አልፎም ወደ ሀገርነት በማደጉ፤ የተፈጠረው የቦታ ርቀት የአንድ አዳም ልጆችን በቀላሉ የመተዋወቅ እድላቸውን ነፍጓቸዋል።

አበው ፍቅር በእግር እንዲሉ ከፊት የራቀ ከልብም ይርቃልና በቦታ ርቀት የተለያዩት ሰዎች ባለመተዋወቅ የልብ ርቀት አጋጥሟቸዋል። ሁሉም ሰው እንደየአቅሙ የራሴ በሚለው ቦታ ብቻ ተወስኖ መኖር ስለጀመረም መራራቅ እና አለመተዋወቅ ሰፍኗል። ባልንጀርነት ተፈጥሯዊ መራራቅን ለመጠገን ግንኙነት ወደ ነበረበት ለመመለስ የሚያስችል ነው። ባልንጀርነት በብዙ ምክንያቶች የሚመሠረት ቢሆንም በዚህ ጽሑፍ የምንመለከተው ግን እግዚአብሔር አምላካችን በቅዱሳት መጻሕፍትና በወዳጆቹ የነገረንን ምንም አስገዳጅ ሰበብ የማይሻውን መንፈሳዊ ባልንጀርነት ነው። በቅዱስ መጽሐፍ አስተምህሮ መሠረት ለባልንጀርነት ብቸኛ መስፈርቱ በአርአያ ሥላሴ መፈጠር ነው። የዳዊትና የዮናታን የባልንጀርነት የሚያስቀና ነው። የእነዚህ ሁለት ባልጀሮች ጓደኝነት ሲጀመር የተመሠረተበት ምንም ዓይነት ሥጋዊ ምክንያት የለም። ዮናታን ማለት እግዚአብሔር ሰጥቷል ማለት ነው። ዮናታን የእስራኤል የመጀመሪያው ንጉሥ የሳኦል ታላቅ ልጅና በጀግንነት ታላቅ ድል ያስመዘገበ በመሆኑም በሕዝቡ ዘንድ የተወደደ የጦር አለቃ ሲሆን ዳዊት ደግሞ በይሁዳ ቤተልሔም አገር እሴይ ከተባለ ሰው የተወለደ ከእሴይም ልጆች መካከል የሁሉም ታናሽ ሆኖ የአባቱን በጎች በመጠበቅ በእረኝነት የልጅነት ዘመኑን ያሳለፈ ብላቴና ነበር። በመካከላቸው የነበረው ሰፊ የዕድሜ የቤተሰብና የአቅም ሁኔታ ልዩነት ከባልንጀርነት አላገዳቸውም(፩ኛ ሳሙ.፲፬÷፵፱፤ ፩ኛ ዜና ፰÷፴፫)።

የሁለቱ ወዳጆች ግንኙነት የተጀመረበትን አጋጣሚ መጽሐፈ ሳሙኤል እንደሚከተለው ከትቦታል። ብላቴናው ዳዊት በእግዚአብሔርና በእስራኤል ፊት ሲገዳደር የነበረውን ፍልስጤማዊውን ግዙፍ ሰው ያለ ጦር መሣሪያ በእግዚአብሔር በመታመን ብቻ በወንጭፉ ገድሎ ነቀፋን ከእስራኤል ባራቀ ጊዜ የጦር ውሎውን ሪፖርት በወቅቱ የእስራኤል ንጉሥ ለነበረው የዮናታን አባት ለሳኦል አቀረበ። ሳኦልም ከየት እንደመጣ አባቱና ቤተሰቦቹ እነማን እንደሆኑ ጠይቆ ከተረዳ በኋላ በቤተ መንግሥቱ ይኖር ዘንድ ወሰደው ወደ አባቱም ቤት ይመልሰው ዘንድ አልተወውም። ይህን ሁሉ ከአባቱ ጋር ሆኖ ሲሰማ የነበረው የእስራኤል የጦር አለቃ ዮናታንም ዳዊት ለሳኦል መናገሩን በፈጸመ ጊዜ ነፍሱ በዳዊት ነፍስ ታሰረች እንደነፍሱም ወደደው። በዚያውም ቀን ስለ መውደዱ ከዳዊት ጋር ቃል ኪዳን አደረገ። የለበሰውንም ካባ አውልቆ እርሱንና ልብሱን ሰይፉንም ቀስቱንም መታጠቂያውንም ለዳዊት ሸለመው።

ዮናታንና ዳዊት የመሠረቱት ባልንጀርነት ዋና መሠረት ከሕያዊት ነፍስ የመነጨ መውደድ ብቻ እንጂ የኑሮ መመሳሰል ወይም የአቅም መመጣጠን አልነበረም። ለዚህም ምስክር ይሆን ዘንድ በሁለቱ ባልንጀሮች መካከል የነበረውን በጦር አለቅነትና በእረኝነት በንጉሥ ልጅነትና በበግ ጠባቂነት መካከል ያለውን ልዩነት ማስተዋል ይበቃል። መጽሐፉ እንደሚነግረን ዮናታን ያለምንም ምክንያት እንደራሱ እንደነፍሱ ወደደው ይህንን ፍቅሩንም ከተረፈው ሳይሆን የለበሰውን የራሱን ልብስና የክብሩ መገለጫ የሆነውን ካባ አውልቆ ለዳዊት በማልበስ ገለጠው፤ የጀግንነቱ ምልክት የጠላቶቹ መከላከያና ማጥቂያ ሰይፉንና ቀስቱን የሚታጠቅበት ዝናሩንም ለዳዊት በመሸለም ባልንጀራውን እንደራሱ/እንደነፍሱ በመውደድ አሳየው። በልጁ በዮናታንና በዳዊት መካከል በተፈጠረው ባልንጀርነት ደስ የተሰኘው ሳኦልም ከእነርሱ ጋር እንዲኖር ፈለገ፤ ዳዊትንም ወደቤቱ እንዳይሰደው እምቢ አለ።

ዳዊትም በምላሹ የባልንጀራውን አባት አባቱ ቤቱን ቤቱ አድርጎ ስለታመነ አባቱ ሳኦል ወደ ሰደደው ሁሉ በደስታ ይሔድ ነበር። በልጆቹ ምክንያት የተፈጠረው ባልንጀርነት ደርጅቶም ወደቤተሰብነት ስላደገ ዳዊት በጦረኞች ላይ ተሾመ። ይህም በጎ ነገር በሕዝብ ሁሉ ዓይንና በሳኦል ባሪያዎች ዓይን መልካም ነበር (፩ኛ ሳሙ. ፲፰÷፩፬)። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባልንጀርነት በሥጋ ከመወለድ ከቤተሰብነትም በላይ ነው። ይህንን እውነት ከነዳዊት ባልነጀርነት አንዱን ሰበዝ መዘን በማየት ልንረዳው እንችላለን። ዳዊት በንጉሡ በሳኦል እና በባልንጀራው በዮናታን እንዲሁም በሰው ሁሉ ፊት በዝና ከሳኦል ልቆ በታየ ጊዜ ሳኦል የመልካም ባልንጀርነት ክፉ ደዌ የሆነው ቅናት አደረበት። ለልጁ ለዮናታንና ለባሪያዎቹ ሁሉ ዳዊትን ይገድሉት ዘንድ ነገራቸው።

ሳኦል ንጉሥ ነውና ሁሉም እንደየትእዛዙ ሲሰማራ ዮናታን ግን የሚወደው ጓደኛው ሲገደል ዝም ብሎ ያይ ዘንድ

የባልንጀርነት ፍቅሩ አልፈቀደለትም፡፡ ምንም እንኳ የንጉሡን ትእዛዝ መተላለፍ ሕይወትን እስከማሳጣት መሥዋዕትነት እንደሚያስከትል ባይጠፋውም የአባቱ ትእዛዝ ከባልንጀራው መውደድ አልበለጠበትም፡፡ ስለዚህም በድብቅ ወደ ዳዊት ሔዶ ከአባቱ ጋር ተነጋግሮ መፍትሔ እስኪያመጣለት ድረስና የአባቱ ቁጣ እስኪበርድ ድረስ እንዲሸሸግ ነገረው፡፡ እውነተኛ ባልንጀርነት ሐሰትና ድብብቆሽ አይነካካውምና በግልጥ "አባቱ ሳኦል ሊገድልህ ፈልጓል አሁን እንግዲህ ለነገው ተጠንቀቅ በስውርም ተቀመጥ እኔም እወጣለሁ አሁን አንተም ባለህበት እርሻ በአባቴ እርሻ አጠገብ እቆማለሁ ስለ አንተም ከአባቴ ጋር እነጋገራለሁ የሚሆነውን አይቼ እነግርሃለሁ" በማለት አሰናበተው፡፡ ይህ ተግባር የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ባልንጀርነት አንዱ መገለጫ ጠባይ ነው፡፡ ለባልንጀራ ምሥጢርን አለመደበቅ ለሞቱ/ለጉዳቱ የሚሆን ምክንያትን ማራቅ ነው፡፡ በሀገራዊ አባባላችን "ተማክረው የበሉት ሽንኩርት አይሸትም" የሚባለው ለዚህ ነው፡፡

ዳዊትም ከዮናታን ጋር የነበረው የባልንጀርነቱ ልክ ነቅ በሌለበት እምነት የተሸለመ ነበርና አባቱ ነው ሳይልና ቃሉን ሳይጠራጠር ባልንጀራው እንደነገረው አደረገ፡፡ ባልንጀራ መልካም ምክር ከሞት ያድናልና ከፊቱም ገለል ብሎ ወደ ነገረው ቦታ ሔደ፡፡ ዮናታንም ሁኔታው ሲመቻችለት ባልንጀራውን ለማዳን በሚያስፈራው በባለግርማ ሞገሱ ንጉሥ ዙፋን ፊት ቆመ፡፡ ወደ አባቱ ፊት ቀርቦም ስለባልንጀራው ስለዳዊት ለአባቱ ሳያደላ እውነቱን መሰከረ፡፡ ‹‹እርሱ አልበደለህምና ሥራውም ለአንተ እጅግ መልካም ሆኖአልና ንጉሡ ባሪያውን ዳዊትን አይበድለው ነፍሱንም በእጁ ጥሎ ፍልስጥኤማዊውን ገደለ እግዚአብሔርም ለእስራኤል ሁሉ ታላቅ መድኃኒት አደረገ አንተም አይተህ ደስ አለህ በከንቱ ዳዊትን በመግደልህ ስለ ምን በንጹሕ ደም ላይ ትበድላለህ›› ሲል የባልንጀራውን እውነት ይዞ ሞገተው፡፡

ይህ ምስክርነት በገዛ ልጁ በባለግርማው ንጉሥ ፊት የተነገረ ስለሆነ የዳዊትን ጥብዓትና እውነት የሚመሰክር ለስላሳ ቃል መሰለ እንጂ በግልባጩ ቢታይ "አስቀድሞም ጠላትህን ድል የነሳልህ እርሱ ባልንጀራዬ ነው፡፡ አሁንም ልትገድለው የምትፈልገው ሕዝቡ ስለወደደው ቀንተህ ተመቅኝተህ ነው እንጂ እርሱ በደል ኖሮበት አይደለም፡፡ እግዚአብሔርም ለእስራኤል ምሕረት ያደረገው በእርሱ በኩል እንጂ በእኛ ቤት በኩል አይደለም›› የሚል የልጅ ተግሣጽ ነው፡፡ በልዝብ አንደበት የቀረበች የልጁን ተግሣጽ የሰማው ሳኦልም ስለ ልጁ ምክርና ስለሚያስከትልበት መዘዝ ሲል የዮናታንን ቃል ሰማ፡፡ "ሕያው እግዚአብሔርን ዳዊት አይገደልም" በማለት ማለ፡፡ ዮናታንም ዳዊትን ጠርቶ ይህን ሁሉ ነገረው፡፡ ዮናታንም ዳዊትን ወደ ሳኦል አመጣው እንደ ቀድሞውም በፊቱ ነበረ" (፩ኛ ሳሙ. ፲፱÷፩-፯)፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊው ባልንጀርነት ከቤተሰብነት ይልቃል፡፡ አልፎ ተርፎም ከሞት ያድናል፡፡

በአንዲት ለነጻነቷ በምትታገል ሀገር ውስጥ ሁለት እንደነፍሳቸው የሚዋደዱ በአንድ ዐውደ ውጊያ የዋሉ ጓደኛሞች ነበሩ ይባላል፡፡ በአጋጣሚ በጦርነቱ ጠላት አይሎ ስለተሸነፉ ተግቶ ሲዋጋ በነበረው ከሁለቱ ባልንጀሮች በአንዱ ላይ የሞት ፍርድ ይፈረድበታል፡፡ በሀገሪቱ ልማድም አንድ የሞት ፍርድ የተፈደበት ፍርደኛ ከመሞቱ በፊት አንድ የፈለገው ነገር እንዲደረግለት ፈቃድ ስላለው እድሉን ተጠቅሞ የሚወዳቸው ቤተሰቦቹን ተሰናብቶ እንዲመጣ ይጠይቃል፡፡ ይሁን እንጂ በልማዳቸው የሚፈልገው እስኪደረግለት ነጻ የሚሆነው ፍርደኛ ከሔደበት ተመልሶ ፍርዱን እስከመቀበል ድረስ የሚታመን ዋስ ያስፈልገው ነበርና ሁለተኛው ባልንጀራው ዋስትናውን ተቀብሎ ባልንጀራውን ወደ ቤተሰቦቹ ሰደደው፡፡ በተለያዩ ምክንያቶችም በታዘዘው ቀን ለመምጣት ስለዘገየ እንደቃሉ የባልንጀራውን የሞት ጽዋ ይጠጣ ዘንድ ታማኙ/ዋስ የሆነው ባልንጀራው ወደ ፍርዱ አደባባይ ቀረበ፡፡

በአሸናፊው ንጉሥ ፊት በፍርደኛው ፈንታ የቀረበውን ሰው አንገት መቀላት የምታስፈጽመው የመጨረሻይቱ ደወል ከመደወሏ በፊት ግን የተፈረደበት ሰው እያለከለከ ወደ ዐደባባዩ ደረሰ፡፡ ወዳጄ ጉድ ሠርቼህ ነበር፤ በል ውረድ ጽዋዬን ልጠጣበት እያለም ወደ ወዳጁ በተጠጋ ጊዜ ባልንጀራው አንተ የሚናፍቁህ፣ የምትናፍቃቸው፣ የሚጠብቁህ፣ የምትጠብቃቸው ሚስትና ልጅ አሉህ፡፡ እኔ ግን ብቸኛ ነኝና ይህች ጽዋ ለኔ ትሁን ሲል ተማጸነው፡፡ በሁለቱ ጓደኛሞች ፍቅርና መተማመን የተደነቀው ንጉሥ አተኩሮ ሲመለከታቸው ከቆየ በኋላ አገልጋዮቹን ጠርቶ ሁለቱንም ወደ ፊቴ አቅርቡልኝ አላቸው፡፡ ወደ እነርሱም ዞሮ "እስከ ሞት ለሚታመን ወዳጅነታችሁ ስል እኔም ምሬያችኋለሁ ፍቅር ከሞት ያድናል" በማለት አሰናበታቸው፡፡

ወደ ቀደመ ነገራችን ስንመለስ ከጥቂት ጊዜ በኋም ጦርነት ተካሔዶ ዳዊት ከፍልስጥኤማውያን ጋር ተዋግቶ ታላቅ ግዳይ በጣለላቸው ጊዜ ሳኦል ክፉ መንፈስ ይዞት ከነጦሩ ከቤት ውሎ ነበር፡፡ ዳዊትም በገና በመደርደር ተጠናውቶት የነበረውን እርኩስ መንፈስ ያርቅለት ዘንድ ሲሔድ ሳኦል ሊገድለው ጦር ወርውሮ ሲስተው ጦሩ በቅጥሩ ግንብ ላይ ተሰክቶ ቀረ፡፡ ዳዊትም ሸሽቶ ወደ አርማቴም ወደ ሳሙኤል ሔደ፡፡ ከዚያም ተያይዘው ወደ ነዋትዘራማ ሔዱ፡፡ በዚያ መኖራቸውን የሰማው ሳኦል ግን ዳዊት ሳይገደል ላለማረፍ ቆርጦ ሲያሳድደው ነገሩን ሰምቶ እንዲሸሽ ለባልንጀራው እንዲሸሽ ያመለከተው ከንጉሥ የቁጣ በትር ያዳነው ባልንጀራው ዮናታን ነበር (፩ኛ ሳሙ፣፲፱÷፳-፳፩)፡፡

ዳዊትም እርሱን ሳልገድል አላርፍ ያለው ሳኦልን ሸሽቶ በጫካ ውስጥ ተደብቆ ሲኖር የጎበኘው "የአባቴ የሳኦል እጅ አታገኝህምና አትፍራ፤ አንተም በእስራኤል ላይ ንጉሥ ትሆናለህ፤ እኔም ከአንተ በታች ሁለተኛ እሆናለሁ፤ ይህን ደግሞ አባቴ ሳኦል ያውቃል" በማለት ያጽናናውና በእግዚአብሔር ፊት ቃል የገባለት ዮናታን ነው (፩ኛ ሳሙ፣ ፳፫÷፲፮-፲፰)፡፡ በመጨረሻም ከባልንጀራው ዳዊት ሥር ሁለተኛ ሰው ሆኖ ለመኖር ተስፋ ያደረገው ዮናታን ከአባቱ ከሳኦል ጋር ተሰልፎ ከጠላት ሲዋጋ በሞተ ጊዜ ዳዊት ጀግንነቱንና ፍቅሩን አስታውሶ አለቀሰለት፤

‹‹የእስራኤል ክብር በኮረብቶች ላይ ተዋግቶ ሞተ፣ኃያላን እንዴት ወደቁ፣

የፍልስጥኤማውያን ቆነጃጅት ደስ እንዳይላቸው፣

የቆላፋንም ቆነጃጅት እልል እንዳይሉ፣

በጌት ውስጥ አታውሩ፣.....

ከሞቱት ደምና ከኃያላን ስብ የዮናታን ቀስት አልተመለሰችም፣

ሳኦልና ዮናታን የተዋደዱና የተስማሙ ነበሩ፣

በሕይወታቸውና በሞታቸው አልተለያዩም፣

ከንስር ይልቅ ፈጣኖች ነበሩ፣

ከአንበሳም ይልቅ ብርቱዎች ነበሩ፣

የእስራኤል ቆነጃጅት ሆይ፣

ቀይ ሐርና ጥሩ ግምጃ ያለብሳችሁ ለነበረ፣

በወርቀ ዘቦም ላስጌጣችሁ ለሳኦል አልቅሱለት፣

ኃያላንም በሰልፍ ውስጥ እንዴት ወደቁ፣

ዮናታንም በኮረብቶችህ ላይ ወድቋል፣

ወንድሜ ዮናታን ሆይ እኔ ስለአንተ እጨነቃለሁ፣

በእኔ ዘንድ ውድህ እጅግ የተለየ ነበር፤

ከሴት ፍቅር ይልቅ ፍቅርህ ለእኔ ግሩም ነበረ፣

ኃያላን እንዴት ወደቁ፣ የሰልፍም ዕቃ እንዴት ጠፉ” ሲል (፪ኛ ሳሙ. ፩÷፳፬-፳፯):: በየመጽሐፍ ቅዱሳዊ ባልንጀርነት ፍቅር እስከ መቃብር ብቻ ሳይሆን ከመቃብርም ያልፋል:: ዳዊት ስለባልንጀራው ዮናታን የተቀኘው ቅኔ የሚነግረን ይህንን እውነት ነው:: ቀድሞም እግዚአብሔር በወዳጁ በሙሴ በኩል ለሰው ሁሉ ከሰጣቸው ትእዛዛትም ሰባቱ ከባልንጀራችን ጋር በሚኖረን መስተጋብር ልንጠብቃቸው የሚገቡ ናቸው:: እነዚህም አባትህን እና እናትህን አክብር ባልንጀራህን ውደድ፣ አትግደል፣ አታመንዝር፣ አትስረቅ፣ በሐሰት አትመስክር፣ አትመኝ የሚሉ ናቸው:: ከአሥሩ ቃላተ ኦሪት ሦስቱ በቀጥታ የሰውና የእግዚአብሔር ግንኙነት ላይ የሚያተኩሩ ሲሆኑ ቀሪዎቹ ሰባቱ የማናየውን እግዚአብሔርን ማመናችንን በምናየው ባልንጀራችን በኩል የምንገልጽባቸው ናቸው:: ሁሉም ትእዛዛት በፍቅረ እግዚአብሔርና በፍቅረ ቢጽ እንደሚፈጸሙ ጌታችን ያስተማረው ለዚህ ነው:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አንድ ሕግ አዋቂ ወደ እርሱ ቀርቦ እድን ዘንድ ምን ላድርግ? ብሎ በጠየቀው ጊዜ የሰጠው መልስ ለመጽሐፍ ቅዱሳዊው ባልንጀርነት ማሳያው ነው::

በዚህም መሠረት የምወደው ባልንጀራ በሥጋ ሳልዋለደው በፍጹም ልቤ በፍጹም አሳቤ፣ በፍጹም ነፍሴ የምወደው፣ ሰው የመሆን ፍቅሬ መገለጫ ነው:: ኦሪትና ነቢያት የሚጸኑበት አንዱ የሕይወት ሚዛን አካል ነው:: ባልንጀራዬ እሱን በመውደዴ የማላየውን አምላኬን መውደዴን የማረጋግጥበት ምሳሌ ራሴን በእግዚአብሔር ዘንድ የማይበት መስታወቴ ነው:: ባልንጀራዬን መውደዴ በአእምሮ በመመለስ ከእግዚአብሔር መንግሥት አለመራቄን የምለካበት ነው::

ደጉ ሳምራዊ ምሳሌነቱ በወንበዴዎች ተደብደቦ ለሞት ተቃርቦ ሳየው የማላልፈው፣ ቀርቤም ቁስሉን በወይን የማደርቅለት፣ በዘይትም የማለሰልስለት፣ ለቀሪው ሕክምናም አስታማሚ የምቀጥርለት፣ ክፍያውንም የምከፍልለት፣ እኔ እስክመለስም አደራ የምሰጠው፣ እርሱም ያደረኩለትን ለሌሎች ሲያደርግ የማየው መስተዋቴ ነው:: ይልቁንም በዕለተ ምጽአት እናንተ የአባቴ ቡሩካን ኑ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ በሚባልበት ጊዜ ተርቤ አብልተኸኛል፤ ተጠምቼ አጠጥተኸኛል፤ ታርዤ አልብሰኸኛል፤ ታምሜ ጠይቀኸኛል፤ እንግዳ ሆኜ ተቀብለኸኛል፤ ታስሬ ወደ እኔ መጥተኻል ተብዬ የምጠየቅበት መፈተኛዬ ነው(ማቴ. ፳፭÷፴፭)::

ከቊሳዊ ፍላጎት ርቆ በአምሳለ እግዚአብሔር በመፈጠር ብቻ የሚመሠረት መልካም ባልንጀርነት የማኅበራዊ ኑሮ መሠረት ነው:: ቤተሰብም ሆነ ዝምድና በባልንጀርነት መሠረት ላይ ይታነጻል:: የዘመኑ ሥልጣኔ የሰውን ኑሮ በማቅለል ስም የነጠቀን ትልቁ ዕሴት ባልንጀርነት ነው:: “ልጄ ለራስህ አዋቂ ብትሆን ለባልንጀራህም አዋቂ ትሆናለህ”(ምሳ. ፱÷፲፪) የተባለው ለዚህ ነው:: መንፈሳዊው ባልነጀርነት ሆነን የምንፈጽመው እንጂ ከሌሎች የምንጠብቀው አይደለም:: ለወዳጃችን የምናደርገው እንጂ የሚደረግልን ብቻ አይደለም:: ባልንጀርነታችንን ለማደርጀት የምንሰጠው እንጂ ውለታ በመሥራት ወረታ የምንቀበልበት አይደለም:: ይህ ባልንጀርነት በምልአት በሚሰጥ ፍቅር ስለሚመሠረት ሲያካፍሉት እጥፍ ይሆናል እንጂ አይጎድልም:: እንደ ሻማ ልቡናችን ውስጥ የበራውን እውነተኛ ፍቅር ለሌላው ባልንጀራችን ስንለኩስለት የሚበራው የወዳጅነት ብርሃን ለሌሎችም እያበራ እየደመቀ ይሔዳል እንጂ ቀልጦ አይጠፋም::

በጎ ወዳጅ እንደ ተገራ ፈረስ ነው፤ የተገራ ፈረስ ጋልቦ ከፈለጉት ቦታ በፍጥነት ያደርሳል:: “አብረው ሲሔዱ መንገዱም አይገድ” እንዲሉ በጎ ወዳጅም የልብን የሚያውቅ በመሆኑ ያሰቡትን ቀድሞ አስቦ ይፈጽማል፤እያጫወተም መንገድን ያሳልጣል (ሲራ. ፴፯÷፯):: “ልጄ ለራስህ አዋቂ ብትሆን ለባልንጀራህም አዋቂ ትሆናለህ” (ምሳ.፱÷፲፪):: “በባልንጀራህ ሐሰትን ተግባር አታድርግ በወዳጅህና በባልንጀራህም ላይ እንዲህ አታድርግ” (ሲራ. ፯ ÷፲፪) የተባለው ከእያንዳንዳችን ታማኝነት የሚጠበቅ መሆኑን ያስገነዝባል:: “የባልንጀራውን ምሥጢር ያወጣ ሰው መታመኑን አጠፋ ከዚያም በኋላ ወዳጅ አያገኝም” (ሲራ. ፳፯÷፳፮) ተብሎ የተነገረውን አስበን የባልንጀራችንን ምሥጢር መጠበቅ ይኖርብናል:: መልካም ባልንጀርነት የሚገኘው ከሌላ በመጠበቅ ሳይሆን ታማኝ ሆኖ መገኘት ነው:: እንዲህ ስናደርግ እግዚአብሔር ሞገስ ይሰጠናል::✠

***ወስብሐት ለእግዚአብሔር***

# ገነተ ቅዱሳን ፈንድቃ መድኃኔዓለም አንድነት ገዳም

**ድረስ እንዳላማው**

*ሀገራችን ኢትዮጵያ “በኃጥአን ድንኳኖች ከመቀመጥ ይልቅ በእግዚአብሔር ቤት እጣል ዘንድ መረጥሁ” (መዝ.፹፫÷፲) በማለት ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት እንደ ተናገረው በእግዚአብሔር ቤት መኖርን መርጠው፣ ምድራዊውን በሰማያዊው ለውጠው፣ መላ ሕይወታቸውን የእግዚአብሔርን ስም እያመሰገኑ የሚኖሩባቸው፣ የቅዱሳን ከተማ የሆኑ በርካታ ቅዱሳት መካናት አሏት። በዚህ ዕትም የምናስነብባችሁም የቅዱሳን ከተማ ከሆኑ መካናት አንዱን ነው። ይህም በምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት የሚገኘው ገነተ ቅዱሳን ፈንድቃ መድኃኔዓለም የተባለው ቅዱስ ቦታ ነው። መልካም ንባብ።*

ገነተ ቅዱሳን ፈንድቃ መድኃኔዓለም አንድነት ገዳም በምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት በጎዛምን ወረዳ ቤተ ክህነት በቅርብ ጊዜ ቢመሠረትም ረጅም ዘመን እንዳስቆጠሩ ገዳማት ለምእመናን ተገቢውን አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝ ገዳም ነው። ገዳሙ ከአዲስ አበባ በ፫፻ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ከምትገኘውና የምሥራቅ ጎጃም ዞን ዋና ከተማ ከሆነችው ከደብረ ማርቆስ ከተማ በስተምዕራብ ፲፰ ኪ.ሜ ርቀት ላይ ከምትገኘው ፈንድቃ ከምትባለው የገጠር ከተማ ፬ ሜትር ወጣ ብሎ ይገኛል።

ገዳሙ በፍልፍል ዋሻ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ዋሻው ተፈልፍሎ የተዘጋጀው በጣም ረጅም ከሆነው ተራራ ላይ የተራራው መሠረት ከሆነው ደልዳላ መሬት ፭፻ ሜትር ከፍ ብሎ ነው። በ፲፱፻፹፯ ዓ.ም ተራራው መፈልፈል ተጀምሮ ከሁለት ዓመት በኋላ ቤተ መቅደስ፣ ቅድስትና ቅኔ ማሕሌት የሚል ቅርጽ ባይዝም በ፲፱፻፹፱ ዓ.ም በሰንሰለታማ ተራራ ሥር በዋሻ ውስጥ የመድኃኔዓለምን ጽላት በማስገባት በወቅቱ ሊቀ ጳጳስ በብፁዕ አቡነ ዘካርያስ ተገድሟል። ገዳሙ እንዲ ገደም ያደረጉት አባት ባሕታዊ ወልደ ሚካኤል ይባላሉ። ጥር ፳፯ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ገዳሙን በማስተዳደር ላይ የሚገኙት አበምኔት አባ ገብረ ሥላሴ ይባላሉ።

ይህ ፍልፍል ቤተ መቅደስ አሁን ያለው መቅደስ፣ ቅድስትና ቅኔ ማሕሌት የሚለውን ቅርጽ እንዲይዝ ለመፈልፈል ፲ ዓመት የፈጀ ሲሆን አስቀድሞ እንደተገለጸው ዋሻው አሁን ያለበትን ሙሉ ቅርጽ ባይዝም ከጥር ፳፯ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም ጀምሮ ሥራው እስከ ተጠናቀቀበት ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ድረስ ሥራው ከተጠናቀቀ በኋላም እስከ ፳፻፲፪ ዓ.ም ድረስ የገዳሙ ቤተ መቅደስ በመሆን አገልግሏል። ይህ ቤተ መቅደስ ከ፳፻፲፪ ዓ.ም በኋላ ግን አዲስ በተሠራው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመድኃኔዓለም ጽላት በመግባቱ በዋሻው ውስጥ ደግሞ የቅዱስ ሩፋኤል ጽላት እንዲገባ ተደርጓል። በአሁኑ ጊዜ በሳምንት አንድ ጊዜ በዋሻ ውስጥ ኪዳን ይደርሳል፤ እንዲሁም በወር አንድ ጊዜ ይቀደሳል።

በአሁኑ ወቅት የገዳሙ አገልግሎት የሚፈጸመው አዲስ በተሠራው የመድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው። የመድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን የተሠራው ዋሻው ከሚገኝበት ተራራ ሥር ከደልዳላው መሬት ላይ ነው። የገነተ ቅዱሳን ፈንድቃ መድኃኔ ዓለም አንድነት ገዳም አሁን ከሚገኝበት ደረጃ እስከሚደርስ ልዩ ልዩ ፈተናዎችን አልፏል። አንዳንዶቹም ፈተናዎች እስከ አሁን ድረስ እንደዘለቁ የገዳሙ አበምኔት አባ ገብረ ሥላሴ ይገልጻሉ። ገዳሙ ከተተከለ ጀምሮ ባለፉት ፳፰ ዓመታት ከተከሠቱ ፈተናዎች መካከል የመጀመሪያ ተደርጎ የሚጠቀሰው ከተራራው ላይ የሚወርደው ጎርፍ ነው። ጎርፉ በገዳሙ ምሥረታ ወቅት የነበረ ችግር ሲሆን በዚያን ጊዜ ገዳሙ ዋሻው ከተራራ ሥር በመመሥረቱ ከላይ የሚፈሰው ጎርፍ አገልግሎቱን ሲያደናቅፍ እና መንገዱን በመዝጋት መተላለፊያ በማሳጣት ገዳማውያንን ሲያስቸግር እንደነበር አባ ገብረ ሥላሴ ገልጸውልናል።

ሌላው በምሥረታ ወቅት እንደችግር ሆኖ የነበረው የልማት መሬት ማጣት ነበር። ገዳሙ ለገዳማውያኑ ሰርከ ኅብስት (የዕለት ምግብ) በማጣቱ ምክንያት መነኮሳቱ ልመናው ሲያሰቅቃቸውና ኑሮ ሲከብዳቸው ብዙዎቹ ወደሌሎች ገዳማት ይፈልሱ እንደነበር ይነገራል። ከዚህም በተጨማሪ ገዳሙ በገበሬዎች መኖሪያ አካባቢ ስለሚገኝ በጥቂት ግለሰቦች አስተባባሪነት በገዳሙ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ደርሶበታል። ይህም ገዳሙን ለማስፋፋት በሚደረገው ዘርፈ ብዙ ጥረት አንዳንድ የአካባቢው ኗሪዎች ቦታ ለመስጠት ፈቃደኛ ካለመሆናቸው በተጨማሪ ገዳሙ እንዲዘጋ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል። የገዳሙን በአካባቢው መመሥረት የማይፈልጉ ግለሰቦች ባይሳካላቸውም ማንም ስለገዳሙ እንዳይናገር እና እንዳይመሰክር ለማድረግ ሞክረው ነበር።

ይሁን እንጂ በቦታው ስሙ እንዲጠራ የፈቀደው አምላካችን እግዚአብሔር ገዳሙ እንዲፈርስና ገዳማውያኑ እንዲበተኑ ነውጥ ሲፈጥሩ በነበሩ ጥቂት ግለሰቦች ላይ ገቢረ ተአምሩን ገለጠ። እግዚአብሔር እንዲህ ያለውን ተአምር የሚገልጠው በአካባቢው የሚገኘው ሕዝበ ክርስቲያንም ሆነ የተደረገውን የሚሰማው ሩቅ ያለው ሰምቶ እንዲማርበት ነው። የገዳሙን መስፋፋት የሚቃወሙ ጥቂት ግለሰቦች ቢሆኑም ብዙ የአካባቢው ሕዝበ ክርስቲያን ግን ለገዳሙ በጎ አመለካከት ስለነበረው ሊስፋፋ ችሏል። በክፉ ግለሰቦች ላይ እግዚአብሔር የፈጸመውን ድንቅ ተአምር በማየት ገዳሙን ስለሚንከባከብ እና ስለሚጠብቅ ገዳሙ አሁን አለበት ላይ ደርሷል። ዋናው ገዳማውያንን እየፈተነ ያለው ችግር በአካባቢው የመጠጥ ውኃ አለመገኘት መሆኑን አበምኔቱ ገልጠዋል።

ገዳሙ በየዘመናቱ ያጋጠሙትን ችግሮች ለመፍታት የወሰዳቸው መፍትሔዎች ነበሩት። ከነዚህም መካከል የውኃ ችግርን ለመፍታት የውኃን ጉዳይ ከሚመለከተው የወረዳው ጽ/ቤት ጋር በመተባበር ምንጮችን በማጎልበት ችግሩን ለመፍታት ተሞክሯል። እንዲሁም የማኅበረሰቡን አስተሳሰብ ለመቀየር

ገዳሙ፣ ከወረዳ ቤተ ክህነት እና ከሀገረ ስብከት ጋር በመተባበር ማስተማር፤ መምከር፤ ገዳሙ የእነሱ መሆኑን ማስገንዘብ እንዲሁም በገዳሙ መመሥረት ደስተኛ ያልሆኑትን ግለሰቦች በእርቅና ይቅርታ በመጠየቅ ከማኅበረሰቡ ጋር በመግባባት ችግሩን ለማስወገድ ተችሏል፡፡

መሬት በመከራየት በአካቢው የሚበቅሉ ሰብሎችን በማምረት ከፍተኛ ልማት እያለማ እንደ ሆነ አበምኔቱ ገልጸውልናል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ከ፳፻፯ ዓ.ም ጀምሮ የወተት ላም በመግዛትና ለአካባቢው ማኅበረሰብ ወተት በማቅረብ ገቢ ማግኘት ተችሏል፡፡ የወተት ላም ፕሮጀክቱን ማኅበረ ቅዱሳን ዋናው ማእከል



የቅዱስ ሩፋኤል ጽላት ያለበት ፍልፍል ዋሻ ቤተ ክርስቲያን

በገነተ ቅዱሳን ፈንድቃ መድኃኔዓለም አንድነት ገዳም የተከናወኑ የልማት ተግባራትን በተመለከተ ከአባ ገብረ ሥስላሴ ጋር ባደረግነው ቆይታ ገዳሙ ሲገደም መነኰሳቱ የዕለት መቁንናቸውን ያገኙ የነበረው ከሰፈር ቁራሽ እንዲሁም በርሐ ድረስ ሄደው ጥራጥሬና ሌላም ነገር በመለመን እንደ ተጀመረ ገልጸውልናል፡፡ አሁን ገዳሙ ሰብል እያመረተ ደኅና ገቢ ያገኛል፡፡ ገዳሙ ይህን ተግባር የሚፈጽመው ከአካባቢው ሕዝበ ክርስቲያን

በማጥናት ከ፳፻፲ ዓ.ም ጀምሮ የወተት ልማቱ እንዲጠናከር ፕሮጀክት በመተግበር በ፳፻፲፩ ዓ.ም አምስት ላሞችን፣ ፳፰ ቆርቆሮ ያለው የላሞች መጠለያ ቤት፣ ዕቃ ቤት እና ወተት ማስቀመጫ በመሥራት ልማቱ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ሆኗል፡፡ ይህ የወተት ልማት ፕሮጀክት በገዳሙ ላሉት አብነት ተማሪዎች ድጎማ እና መነኰሳት መተዳደሪያ እንደ ተጨማሪ ገቢ በመሆን እያገለገለ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ሰዓት ገዳሙ ፲፰ የወተት



ከተራራው ሥር የተሠራውና የመድኃኔ ዓለም ጽላት የሚገኝበት ቤተ ክርስቲያን



የቅዱስ ሩፋኤል ጽላት ያለበት ፍልፍል ዋሻ ቤተ ክርስቲያን

ላሞች ያሉት ሲሆን ለአካባቢው ማኅበረሰብ እና ለደብረ ማርቆስ ከተማ ነዋሪ ወተት በተመጣጣኝ ዋጋ እያቀረበ ይገኛል፡፡ በሦስተኛ ደረጃ በገዳሙ ከሚከናወኑ የልማት ሥራዎች መካከል አንዱ የሸማ ሥራ አንዱ ነው፡፡ ይህም ሥራ በመጀመሪያ በባህላዊ መንገድ የተጀመረ ሲሆን በወረዳው ጥቃቅን እና አነስተኛ መሥሪያ ቤት አራት ዘመናዊ ማሽኖችን ማግኘት በመቻሉ አሁን በተጠናከረ መልኩ በመተግበር ተጨማሪ ገቢ እንዲገኝ ከሚከወኑት የልማት እንቅስቃሴዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህን የሸማ ሥራ መነኰሳቱ በትጋት በመሥራት ለአካባቢው ማኅበረሰብ ኢትዮጵያዊ አልባሳትን በማዘጋጀት ማቅረብ ተችሏል፡፡

በገነተ ቅዱሳን ፈንድቃ መድኃኔ ዓለም አንድነት ገዳም በትኩረት ከሚታዩ አገልገሎቶች መካከል አብነት ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ ገዳሙ ከ፲፱፻፺ ዓ.ም ጀምሮ የቅዳሴ እና የቅኔ ጉባኤ ቤቶችን ከፍቶ ተማሪዎችን በመቀበል እያስተማረ ይገኛል፡፡ በወቅቱ ጉባኤ ቤቶች ሲጀምሩ መምህራኑ በ፺ ብር ደመወዝ ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ ነበር፡፡ ነገር ግን በደመወዙ አነስተኛነት ምክንያት የመምህራን መቀያየር መሠረታዊ ችግር ሆኖ ነበር፡፡ በአሁኑ ሰዓት ጉባኤ ቤቶች በቅኔ ቤት ፻፸ ተማሪዎችን እንዲሁም በቅዳሴ ቤት ፶ ተማሪዎችን እያስተማሩ ይገኛሉ፡፡ ገዳሙ በዚህ ወቅት ለመምህራኑ የመኖሪያ ቤት እና ወርኃዊ ደሞዝ ለእያንዳንዳቸው ሦስት ሺህ ብር እና ለተማሪዎች የመኖሪያ ቤት በከፊልም ቢሆን ማሟላት ችሏል፡፡ ነገር ግን ከተማሪዎች ብዛት አንጻር ብዙ ተጨማሪ መኖሪያ ቤት እና የመጠጥ ውኃ አቅርቦት እጥረት ከፍተኛ ተግዳሮት ነው፡፡ ተማሪዎቹ በአሁኑ ሰዓት ለገዳሙ የውስጥ (ቅዳሴ፣ ማሕሌት፣ ሰዓታት…) እና የውጭ (ስብከት፣ ማኅበራዊ አገልግሎት) አገልግሎት መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ፡፡

ገዳሙ ከሚያከናውነው የውስጥ እና የውጭ አገልግሎት በተያያዘ በውስጡ ባሉት መነኰሳት እና መምህራን እንዲሁም ተማሪዎች ውስጣዊ አገልግሎቶችን በመፈጸም እንዲሁም የገዳሙን ልማታዊ እንቅስቃሴዎች በትጋት በመፈጸም ላይ ሲሆን በአካባቢው ካሉት አጥቢያዎች ጋርም በስብከተ ወንጌል፣ በቅዳሴ፣ በፍትሓት፣ በገንዘብ ድጋፍ፣ወዘተ. በትብብር እያገለገለ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም ለአካባቢው ማኅበረሰብ ልዩ ልዩ የገዳሙ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ያቀርባል፡፡ የገነተ ቅዱሳን ፈንድቃ መድኃኔ ዓለም አንድነት ገዳም የወደ ፊት ዕቅዱን በተመለከተ አባ ገብረ ሥላሴ "ገዳሙ ሁለት ዓይነት ዕቅድ አውጥቶ እየተንቀሳቀሰ ሲሆን በአጭር ጊዜ ለመከወን ከያዛቸው ዕቅዶች መካከል ተጨማሪ ገቢ እዲያገኝ መሥራት እና የአብነት ትምህርት ቤቶች ያለባቸውን የመኖሪያ ቤት እና የውኃ ችግር መቅረፍ ነው፡፡ ይህን ለማሳካት የተጀመረውን የዶሮ እርባታ በተሻለ መልኩ አደራጅቶ መሥራት አንዱ የትኩረት ነጥብ ነው፡፡ በረጅም ጊዜ ገዳሙ ለመሥራት ዓላማው አድርጎ ከያዛቸው ዕቅዶች መካከል አንዱ እና ዋነኛው ለአብነት ተማሪዎች አዳሪ ትምህርት ቤት መሥራት ነው፡፡ ይህን አሁን ገዳሙ ካለበት ችግር አኳያ ተግባራዊ ማድረግ ስለማይቻል እግዚአብሔር የፈቀደለት እዲሠራው አሳቡን የመንገር እና የማስተዋወቅ ተግባር እናከናውናለን፡፡ ሌላኛው ገዳሙ በረጅም ጊዜ ዕቅዱ ያሰበው ተግባር የኤሌክትሪክ መብራት ማስገባት ነው" ብለዋል፡፡

በአሁኑ ጊዜ በገዳሙ ያለው ምቹ ሁኔታ ለገዳማዊ ሕይወት እና ለአብነት ትምህርት በሰጠው ልዩ ትኩረት መሠረት መንፈሳዊ ሕይወትን እና ዕውቀትን ለማዳበር ከፍተኛ ተነሣሽነት መኖሩ ነው፡፡ ከደብረ ማርቆስ ከተማ ቅርብ በመሆኑ ብዙ ክርስቲያኖች መንፈሳዊ በረከት ለማግኘት ስለሚመጡ ወንጌልን በቀላሉ ለማስተማር ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቦታው ፈዋሽ ጸበል ስለሚገኝበት ብዙዎቹ ከልዩ ልዩ ደዌና ከርኵስ መንፈስ መላቀቃቸውን የሰሙ ተጠማቅያን ወደ ገዳሙ እየሄዱ ነው፡፡ እስከአሁን ድረስም በሽዎች የሚቈጠሩ ምእመናን ከደዌ ተፈውሰዋል፡፡

በመጨረሻም ገዳሙ የበረከት ቦታ እንደመሆኑ መጠን ምእመናን ጎብኝተው በረከት እንዲያገኙ፣ ገዳሙ በአጭር ጊዜም ሆነ በረጅም ጊዜ ዕቅዱ ሊተገብራቸው ላሰባቸው ተግባራት ክርስቲያናዊ ግዴታቸውን እንዲወጡ ገዳሙ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡ እግዚአብሔር ሀገራችንን ኢትዮጵያን እና ሕዝቦቿን ይጠብቅልን፡፡ አሜን!!✠

***ወስብሐት ለእግዚአብሔር***

# የኢንተርኔት ዘመን ስብከተ ወንጌል

ዲ/ን ማለደ ዋሲሁን

የያዝነው ፳፩ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ለዓለም ካበረከታቸው አስደናቂ ቴክኖሎጂዎች ኢንተርኔትን ያህል ፈጣን የዕድገት ለውጥ እና የአገልግሎት ስፋት አልታየም። ኢንተርኔት ቴክኖሎጂን በምርምር አሁን ላለበት ደረጃ ያደረሱ መሐንዲሶች አሁን ባለበት ደረጃ ስለመስፋቱም ግምቱ የነበራቸው አይመስልም። ኢንተርኔት ለተግባቦት ሁነኛ መሣሪያ ሆኖ ማገልገሉ ከምንም በላይ ዋጋውን ከፍ አድርጎታል። በመሆኑም ፳፩ኛው ምዕት ዓመት ትክክለኛና ተከታታይ መረጃዎችን ለመስጠት አመቺ ሆኖ ተገኝቷል። መረጃዎችን በዓለም ላይ በአንድ ጊዜ በብዙ መጠን ለሚፈለገው ቡድን፣ ግለሰብ ወይም ተቋም ለማድረስ መቻሉ የሚደነቅ አድርጎታል።

የሰው ልጅ በተሰጠው የፈጠራ ጸጋ ተጠቅሞ ያገኘውን ይህን ፈጣን ቴክኖሎጂ፣ ሊያስደስት በሚችል መንገድ ጥቅም እንዲሰጥ ማድረግ ደግሞ የሃይማኖት መምህራን ተግባር ይሆናል። በተለይ "ወንጌልን በዓለም ስበኩ"፤ ተብለው ለታዘዙ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና ምእመናንን ልዩ ትርጉም አለው። ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ የምታደርገውን የምስክርነት /የተጋድሎ/ አገልግሎት በማፋጠን ትርጉም ያለው ተግባር ልታከናውንበት ትችላለች። በየትኛውም ቅርጽ ቢሆን ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮዋን ልታስፋፋበት፣ ሥርዓቷን ልታስተዋውቅበት፣ የሰዎችን ጥያቄዎች ልትመልስበት ትችላለችና። ኢንተርኔት በዓለም ሁሉም አካባቢዎች በአንድ ጊዜ ተደራሽ መሆኑ የክርስቶስን ወንጌለ መንግሥት በዓለም ላይ እንዲሰበክ ከፍተኛ እገዛ ለማድረግ የሚያስችል ሆኗል።

በዚህም ኢአማንያንን ወደ አማኒነት፣ ያመኑትን በምግባር ትሩፋት ከአንዱ ምዕራፍ ወደ ሌላው እንዲያድጉ በማድረግ ለማጽናት ልትጠቀምበት ትችላለች። "እንግዲህ ሂዱና በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ። ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው፤ እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ በዘመኑ ሁሉ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ" /ማቴ. ፳፰፥፲፱-፳/ ያለው የጌታችንን የአደራ ቃልም ለመወጣት ያበቃል።

በኢንተርኔት የሚሰጥ የሰብከተ ወንጌል አገልግሎት ሲባልም ኢንተርኔትን መሠረት አድርገው የተፈለሰፉ የማኅበራዊ ብዙኃን መገናኛ አማራጮችን መጠቀም ማለታችን ነው። በዚህ ዘመን በአብዛኛው በዓለም ላይ ሃይማኖታዊ አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙት የማኅበራዊ ሚዲያ አማራጮች Facebook፣ Twitter፣ Whats App፣ LinkedIn፣ YouTube፣ Instagram፣ chat rooms ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

መጻሕፍት፣ ጋዜጦች፣ መጽሔቶች፣ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ቢልቦርዶች፣ በራሪ ወረቀቶች የሚሰጡት አገልግሎት እንዳለ ሆኖ የማኅበራዊ ሚዲያ የኢንተርኔት አማራጩ ግን እነዚህን ከማገዝ አልፎ በተለያዩ የማኅበራዊ ብዙኃን መገናኛ መተግበሪያ መንገዶች/ፕላት ፎርሞች የበለጠ ተደራሽ የመሆን ዕድልን አስፋፍቷል።

## ልዩ ባሕርይ

ኢንተርኔትን መሠረት ያደረገ አገልግሎት ከሌሎች የስብከተ ወንጌል አገልግሎት መንገዶች ለየት የሚልበት የራሱ ባሕርይ አለው። የኢንተርኔት ግንኙነት ዘመኑ እጅግ ፈጣን፣ አዋጪ፣ ተስማሚ የግንኙነት/ተግባቦት መሣሪያ ሆኗል፤ በጊዜ፣ በቦታ፣ በርቀት የሚፈጠርን ተጽዕኖ ይቀርፋል፤ በኢንተርኔት የመገልገል ጥቅሙ በዝቅተኛ ዋጋ፣ በዝቅተኛ ስጋት፣ በመላው ዓለም መድረስ፣ ልዩ ልዩ የሚዲያ ቅርጾችን የመጠቀም ዕድል፣ ልዩ ልዩ ቋንቋዎችን የመጠቀም ዕድል፣ ተደራሽነትና ተስማሚነት፣ በተገልጋዮች ፍላጎት የሚኀበኙ መሆናቸው ነው፤ አንድን የተለየ አካባቢም ዒላማ ማድረግ ይችላል፤ ወጣቱን ለማግኘት የሚያስችል መሆኑም ትልቅ ዕድል ነው። ቴሌቪዥን በሽፋን ውስንነት አለበት፤ ይህንን ግን አጣምሮ መጠቀም ይቻላል።

## የማኅበረሰብ አኗኗር ለውጥ

በዓለም ላይ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰ የመረጃ ልውውጥ አብዮት እየተካሄደ ነው። ያንን ተከትሎ ብዙኃኑ ማኅበረሰብ የአኗኗር ሥርዓታቸውን ከሁኔታዎች ጋር ለማስማማት እየተጣደፉ ነው። ይህ በክርስቲያኖች አኗኗርና በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያስከተለው ግፊትም ከፍተኛ ነው። በመሆኑም በአንድ በኩል የኢንተርኔት ግንኙነት መልካም ነገሮችን ይዞ መጥቷል። በሌላ በኩል ደግሞ መጠነ ሰፊ ፈተናን ደቅኗል። ይህ የቴክኖሎጂ ውጤት ይዞት ከመጣው ፈተና ለመዳን ግን ያለው አማራጭ ኢንተርኔትን ለመርገም ሳይሆን ለበረከት ማዋል መሆኑ ግልጽ የሆነ ይመስላል። ምእመናንን ጨምሮ የዓለም ሕዝብ ከዚህ የሳይበር ዓለም ጋር ተሳስሯል። የዓለም ሕዝብ ይህን የሚያደርገው ወዶ ብቻ ሳይሆን ተገዶም ነው።

ስለዚህ የቤተ ክርስቲያንን አግልግሎት፣ ልጆቿንም ሌላውንም ሕዝብ ከእሳት ነጥቆ ለማውጣት፣ ርካታ በሌለው መዝናናት እያበደ የሚገኘውን ማኅበረሰብ ለእውነተኛ ዜና ትኩረት በመስጠት፣ ጊዜ መድቦ በመሥራት ለእግዚአብሔር ቃል ተገዢ ለማድረግ የነገዋ ቤተ ክርስቲያን ወሳኝ ተጋድሎ ይጠይቃታል። የዓለማችን ሕዝብ ባልተጣራ የመረጃ ሸክም አእምሮው ተጨናንቋል፤ የመረጃ ጎርፍ እያናወጠው በመሆኑ ከአቅሙ በላይ እየሆነበት ነው። አያያዙን ማወቅ ያልቻሉና በሸክሙ ወገባቸው የተሰበሩ በርካቶች ሲሆኑ የተጠቀሙበትም የትየለሌ ናቸው።

በመሆኑም ቤተ ክርስቲያን ለአገልግሎቷ በሚፈለገው ደረጃ የኢንተርኔቱን ዓለም መቀላቀል የሚኖርባት ኢንተርኔትን

መሠረት ባደረጉ ማኅበራዊ ሚዲያዎች በዓለም ላይ እየተቀላጠፈ ያለውን የባህልና የርዕዮተ ዓለም መለዋወጥ የሚያስከትለውን የምእመናን ፈተና ለማቅለል ስለሚያግዝ ነው። ምክንያቱም አዲሱ የመገናኛ ብዙኃን አማራጭ የአሳብ ልውውጥ ከባቢ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች በማኅብረሰቡ ውስጥ የሚያደርጉትን መስተጋብር በፍጥነት በአብዮት መንገድ እያካሄዱ ነው፤ የኢንተርኔቱን ዓለም ማኅበራዊ ግንኙነቶቻችንንም እየበየነ ይገኛል። ለዚህም እጅግ የዘመኑ ተንቀሳቃሽ ስልኮች፣ ላፕቶፖች እና ልዩ ልዩ ተያያዥ የኤሌክትሮኒክስ ቴክኖሎጂዎች ለሰዎች በጣም አስፈላጊ ሆነዋል። በመሆኑም ምእመናንን በራሳቸው ተነሣሽነት በዚህ የኢንተርኔት ዓለም ውስጥ አግልግሎት ለመስጠትና ለመቀበል የሚፈጥሩት አደረጃጀት እየጠነከረ መጥቷል።

የኢንተርኔትን መፈልሰፍ እና በእርሱ ውስጥ የሚሠራባቸውን ማኅቀፎች መብዛት ተከትሎ ቀድሞ በጽዋ ማኅበር እንደ ነበረው ግንኙነት እርሱን ባይተካም በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ በሚደረግ የገጽ ለገጽ ወይም የምስልና የድምፅ ግንኙነት ይህን አገልግሎት ለማቀላጠፍ ሲመቻቹ እየታየ ነው። የቅዱስ ገብርኤል፣ የቅዱስ ሚካኤል… ወዳጆች ማኅበር እየተባሉ የሚፈጠሩ ቡድኖች እና ወዳጅነቶች የዚህ ማሳያ ናቸው። ይህ የሚያመለክተን ምእመናን በዓለም ላይ በእጅጉ እየተንሰራፋ ላለውና ኢንተርኔትን መሠረት ላደረገው የወንጌል አገልግሎት ራሳቸውን እያዘጋጁ መሆናቸውን ነው። የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ደግሞ አገልግሎቱን የሚመራ በመሆኑ ለዚህ የወንጌል አገልግሎት አለመዳረስ በዚሁ መንገድ ምላሽ ለመስጠት መነሣት ይኖርበታል።

### በተለይ ለስብከተ ወንጌል

ቴክኖሎጂው ዘርፈ ብዙ ጥቅም ቢኖረውም የስብከተ ወንጌል አገልግሎትን ግን የበለጠ ያስፋፋዋል። ማኅብራዊ መገናኛ ብዙኃን ለስብከተ ወንጌል ያላቸውን ሚና ስናይ ወሳኙ ቁም ነገር በመልክአ ምድር ያልተገደበ፣ በመዋቅር ያልታሰረ ፈጣን አገልግሎት መስጠት መቻሉ ነው። በዚህም በዓለም ላይ የሚገኙ ክርስቲያኖችን እንደ አንድ ቤተሰብ በአንድ ጊዜ ማቅረብ ተችሏል። በመሆኑም በዚህ በክፋትና በከንቱ ስብከት በተጨናነቀና አስተሳሰቡን በአጨለመ ዓለም ውስጥ በብዙ ቋንቋ የወንጌልን ብርሃን ማብራት ቢቻል ጨለማው እየተገፈፈ የተቀደሱ የመረጃ መረብ መስመሮችን እየዘረጉ ሰይጣንን ድል ማድረግ ይቻላል።

በተለይ ከአገር ውጭ የሚኖሩ ምእመናንን በሀገር ውስጥ ከሚኖሩ ከሚናፍቋቸው ሊቃውንት ጋር ማስተሳሰር፣ የረጋ፣ የሰከነና የበረታ አእምሮ ካላቸው መምህራን አንደበት የሚወጣውን ቃል ለማድረስ ምቹ ይሆናል። በውጪ ሀገር ለሚገኙ አገልግሎታችንን ለሚናፍቁ አፍሪካውያንንና የዓለም ጥቁር ሕዝቦችም በቶሎ ለመድረስ ያመቻል፤ ሌሎችንም የዓለም ማኅብረሰብ አባላት ከጥፋት ወደ ምሕረት መንገድ ለማምጣት ይበጃል። ለዚህ ከኢንተርኔት ቴክኖሎጂው በተጨማሪ የልዩ ልዩ ቋንቋዎች ችሎታ ያላቸውን አገልጋዮች ማሰማራት ከተቻለ የቤተ ክርስቲያናችን ወርቃማ የሕይወት ትምህርት በቀላሉ ይዳረሳል።

የአጥቢያና የሀገረስብከት… ድረገጾች፣ የመገናኛ አውታሮች (የፌስቡክ ገጾች)፣ … ያስፈልጋሉ። በእነዚያም ላይ የምስል

**በአንድ በኩል የኢንተርኔት ግንኙነት መልካም ነገሮችን ይዞ መጥቷል። በሌላ በኩል ደግሞ መጠነ ሰፊ ፈተናን ደቅኗል። ይህ የቴክኖሎጂ ውጤት ይዞት ከመጣው ፈተና ለመዳን ግን ያለው አማራጭ ኢንተርኔትን ለመርገም ሳይሆን ለበረከት ማዋል መሆኑ ግልጽ የሆነ ይመስላል። ምእመናንን ጨምሮ የዓለም ሕዝብ ከዚህ የሳይበር ዓለም ጋር ተሳስሯል። የዓለም ሕዝብ ይህን የሚያደርገው ወዶ ብቻ ሳይሆን ተገዶም ነው።**

ወድምፅ) የቪዲዮ፣ የኦዲዮ፣ መልእክቶች፣ መጻሕፍት ከተቻለ ያለዋጋ ከዐቅም በላይ ከሆነና ገቢው ለአገልግሎቱ ከተፈለገ በተወሰነ ተመጣጣኝ ዋጋ ለሚፈልጉ ሁሉ ማቅረብ ይገባል። በተጨማሪም የድረገጽ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ያስፈልጋል። ዓለምና መናፍቃን የኢንተርኔቱን መስመር ፈጥነው በተቈጣጠሩት መጠን እኛ ኦርቶደክሳውያን ግን ይህን መልካም ዕድል ለአገልግሎት

የሚገባውን ያህል አላዋልነውም። ሰይጣን የሳይበሩን ዓለም ለመውረስ በጉዳይ አስፈጻሚዎቹ አማካኝነት ጥድፊያ ላይ በመሆኑ ክርስቲያኖች መቀደም መቻል አለብን።

### በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ምቹ ሁኔታዎች

ቤተ ክርስቲያናችን ኢንተርኔትን መሠረት ላደረጉ መገናኛ ብዙኃን ሰፊ ግብዓት እንዳላት መታወቅ አለበት። በርካታ አገልግሎቶቿ ሳቢ በሆኑ ክዋኔዎች በሚደነቁ ሥርዓቶች የተሞሉ ናቸው። የበዓላቱ ትዕይንት፣ ከመቅደስ እስከ ቅኔ ማሕሌት ያሉ አስደማሚ አገልግሎቶች፣ የበርካታ ማራኪ የሊቃውንት አንደበት፣ ሊዘገቡ የሚችሉ፣ ዶክመንተሪ ሊሠራባቸው የሚችሉ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ታሪካዊ ቅርሶች፣ የክርስቶስን ወንጌል መሠረት ያደረገ አኗኗር በዘርፉ በዕውቀትና በልምድ እጅግ የተካኑ ልጆች ያሏት ለማኅበራዊ መገናኛ ብዙኃን ሰፊ ግብዓት የሚሆኑ ናቸው። እነዚህ ሁሉ እየተተነተኑ በልዩ ልዩ ቋንቋዎች እየተተረጐ ሙ ቢቀርቡ በየዕለቱ ዓለም ሊደመምባቸው የሚችሉ ለስብከተ ወንጌል አገልግሎት አጋዥ ግብዓቶች ይሆናሉ።

### ለአስተዳደራዊ ሥራዎች

ለአስተዳደራዊ ሥራዎች ኢንተርኔትን ጥቅም ላይ ማዋል ብልህነት በመሆኑ ለስብከተ ወንጌል ክትትልና ማበረታታት በዚሁ ቴክኖሎጂ ማከናወን ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪም ሌሎች የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶችን ለማቀላጠፍና ከማኅበረሰቡ አካሔድ ለማስማማት ከዚህ በተጨማሪም ለምጣኔ ሀብት አገልግሎት አጥቢያን ከአጥቢያ፣ መሪዎችን ከምእመናን፣ ምእመናናን ከምእመናን በማስተሳሰር ዘርፈ ብዙ አገልግሎቶችን እንዲሰጥ ማድረግ ይቻላል። በዚህም የበረቱትን የበለጠ ማበርታቱ ብቻ ሳይሆን በተለይ አጥቢያ ባልተቋቋመባቸው የውጪ ሀገራትና በቍጥር አነስተኛ ሆነው በጠረፋማ አካባቢ በርቀት ለሚገኙ ምእመናን ትልቅ መጽናኛ እየሆነ በመምጣቱ ወዲያውኑም ግብረ መልስ የሚታይበት ዕድል ስላለው ስብከተ ወንጌል በሰዎች ላይ የፈጠረውን በጎ ተጽዕኖና ያስገኘውን ፍሬ ለመመዘን አመቺ ይሆናል።

### ዝግጅት

ኢንተርኔት ልናደርግ የሚገባውን አገልግሎት ውጤታማ በማድረግ ለትምህርት፣ ለአስተዳዳር፣ ለመረጃ ልውውጥ፣ ለማኅበራዊ ትስስርና ለአንድነታችን በእጅጉ ይጠቅማል። ነገር ግን ማእከላዊነት ባለውና ከቁጥጥር ባልወጣ መልኩ ምክርና ተግሣጽ ባለተለየው ሁኔታ መመራት አለበት። በቂ በጀት መመደብም ያስፈልጋል። ለባለሙያዎችና ለአገልግሎቱ ለሚያስፈልገው የሰው ኃይል በቂ ሥልጠና መስጠት ይገባል። ጠንካራ የመገናኛ ብዙኃን በማቋቋም ማስተሳሰርና ማናበብም ተገቢ ነው። ይህ ካልሆነ ፈተናዎች ይኖሩታል።

### ፈተናዎች

በዚህ ፈጣን የመረጃ ልውውጥ ዘመን ውስጥ ክርክሮች፣ አደገኛ የጥፋት ምክሮችና ሰይጣናዊ አሳቦች የሚረጩበት አጋጣሚ ሰፊ ሆኗል። በቴክኖሎጂው በሚሠራው የሳይበር ጥቃት፣ ስም ማጥፋት፣ ሕገ ወጥ ግብይት፣ ዝሙትን የሚቀሰቅሱ መልእክቶች፣ የሐሰት ማስታወቂያዎች፣ ዜናዎች፣ ጊዜ ማባከኛ ጽሑፎች፣ ድምፅና ምስል ቅንብሮች የኢንተርኔት ዓለም ተጠቃሚ አካላት ፈተናዎች ናቸው። ይህ ሁሉ ሲሆን አገልግሎታችንን በኢንተርኔት እናቀላጥፍ ማለት የኢንተርኔት አገልግሎት ችግር አይኖረውም፣ ጥንቃቄ አያስፈልገውም ማለት አለመሆኑን መረዳት ይገባል። ችግሩን ኢንተርኔት በባሕርዩ ያስከተለው ሳይሆን የቴክኖሎጂው ተጠቃሚዎች ልዩ ልዩ ፍላጎት፣ አመለካከትና እምነት ያላቸው ከመሆናቸው የሚመነጭ በመሆኑ አሁን ኢንተርኔትን ገፍተን የማናስወግደው ለስብከተ ወንጌል አማራጭ ሆኗል። በተለይ ወጣቶችን ያቀፈች ቤተ ክርስቲያን መንጋዋ ከዚህ ቴክኖሎጂ ጋር ተጣብቆ የሚኖር መሆኑን መዘንጋት የለባትም። ስለዚህ በአዲሱ የሚዲያ ዘመን አገልግሎቱን እንዴት ላደራጅ ብሎ ማሰብ የዛሬዋና ነገዋ ቤተ ክርስቲያን ወሳኝ የቤት ሥራ ነው።

ኢንተርኔትን በጥርጣሬ ለሚያዩ ሰዎች በሙከራ ሥራዎች ጥቅምና ጉዳቱን ለይተው እንዲያዩ ማስገንዘብ ያስፈልጋል። እንዳንጠቀምበት ሳይሆን ጉዳቱን እንዴት እንቀንስ? ጥቅሙን እንዴት እንጨምር ለማለት ነው፤ ሆኖም ኢንተርኔት የማይተካውንና የሚተካውን አገልግሎት ለይቶ ሕግና ሥርዓት እስከ መደንገግ ለጉዳዩ ትኩረት መስጠት ይጠይቃል። በአጠቃቀሙም ላይ ሥርዓት ማበጀት፣ ኃጢአትና ጽድቁን ማሳወቅ፣ ካህናት ልጆቻቸውን ለንስሓ ሲያበቁ ለሚሰጡት ቀኖናም በሚበጅ መንገድ መልካሙና ክፉው መለየት አለበት።

ከዚህ ባሻገር ፈተና የሚሆነው ወደ ፊት የኢንተርኔት ሚዲያ አገልግሎት አቅራቢዎች ማንነት በአገልግሎቱ ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ነው። ይህንን ከግምት ውስጥ ባስገባ መንገድ እንቅስቃሴ ማድረግ ይጠይቃል። ሌላው ደግሞ ማእከላዊነትን ያልጠበቁ አገልግሎቶች የሚያስከትሉት ፈተና ነው። በቤተ ክርስቲያን ደረጃ ተቋማዊ የማይሆኑ አገልግሎቶች ፈተና የማይሆኑበት አሠራር መዘርጋት ይገባል። ለኦርቶዶክሳዊ ማኅበረሰቡ አገልግሎት ለመስጠት የቆሙ የሚመስሉ ነገር ግን ለራሳቸው ግላዊ ዓላማ የተሰለፉና የራሳቸውን የማኅበራዊ ገጸ ድር ከፍተው በመደበኛነት የሚጽፉ ጸሐፊዎችን እንቅስቃሴ የመግራትና የማስተካከል ተግባር መፈጸም ያስፈልጋል።

ኢንተርኔትን መሠረት ያደረገውን ይህን አገልግሎትም በማእከላዊነት የሚቈጣጠርና ቤተ ክርስቲያናዊ መልኩን የሚያስጠብቅ ቦርድም ሊኖረው ይገባል። የማኅበራትንና የሰንበት ትምህርት ቤቶችንም ተሳትፎ በዚህ መልኩ ቅርጽ ማስያዝ ያስፈልጋል። ይህ ከሆነ ሰፊውን የስብከተ ወንጌል አገልግሎታችንን በኢንተርኔት የበለጠ ማስፋት እንችላለን።✚

***ወስብሐት ለእግዚአብሔር።***

# ካሳ

እንዳለ ደምስስ

ጥር ፳፩ ቀን የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የዕረፍቷ መታሰቢያ ዓመታዊ ክብረ በዓል ነው፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ ዓለም ባንክ በምትገኘው የቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ገና ከሌሊቱ ጀምሮ በምእመናን ተጨናንቃለች፡፡ ካህናቱ ዕለቱን አስመልክቶ ከሚቀርቡ ቀለሞች መካከል "ሞትሰ ለመዋቲ ይደሉ ሞታ ለማርያም የአጽብ ለኵሉ፤ ሞትማ ለሚሞት ሰው ይገባል፤ የማርያም ሞት ግን እጅግ ያስደንቃል" እያሉ በድምፅ ሲያዜሙ የድምፃቸው ጣዕመ ዜማ ነፍስን ነጥቆ ሰማየ ሰማያት አድርሶ ይመልሳል፡፡

ከቤተ ክርስቲያኑ በስተጀርባ የሚገኘው የጀሞ ተራራ በኩራት ራሱን ቀልሎ ከቤተ ክርስቲያኑ በሚፈሰው ጣዕመ ዝማሬ ከዕለት ወደ ዕለት ቁመቱ እየረዘመ ከምድር የሚበቅል አስመስሎታል፡፡ የጥር ወር ነፋስ አዘል ቀዝቃዛ አየር በቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያ በበቀሉ ዕድሜ ጠገብ ዛፎች ታግዞ ከተራራው ቁልቁል እየተምዘገዘገ ፊትን ይለበልባል፤ ቆፈኑ መላ አካልን ያደነዝዛል፡፡ ከተራራው ግርጌ እስከ ጫፍ መኖሪያ ቤቶች እዚህም እዚያም በአንድ ምሽት በቅለው ያድራሉ፡፡ ይህም የሰው ልጆችን ጥንካሬ ያበሥራል፡፡ "ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃል" እንዲሉ በቤት እጥረት ምክንያት የተቸገሩ አዲስ አበቤዎች ከተማዋ ከአፍ እስከ ገደፏ ሞልታ ካፈሰሰቻቸው ሰፈሮች አንዱ ሆኗል፡፡ በቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ለበዓሉ የሄዱ ምእመናንና በደዌ ዳኛ ተይዘው በሰንሰለት የታሰሩ ጠበልተኞች ከአራቱም አቅጣጫ ተሰብስበውበታል፡፡

የአባቶች የምስጋና ዝማሬ ቀጥሏል፣ "ለዛቲ ብእሲት ሠረቀ ላዕሌሃ ብዕለ ጸጋሁ ለአብ፤ ወአግዐዛ እምእኵይ ውስተ ሠናይ እሞት ውስተ ሕይወት፤ ወረሰየ ይዝክሩ ስማ ውስተ ኵሉ ምድር፤ ለዚች ሴት የአብ ፍጹም ጸጋው በላይዋ ተገለጠ፤ ከክፉ ወደ በጎ፣ ከሞት ወደ ሕይወት ነፃ አወጣት፤ ስሟንም በምድር ሁሉ ይጠሩ ዘንድ አደረገ " (ድጓ ዘአስተርእዮ) በማለት በቅዱስ ያሬድ የምስጋና ዝማሬ እየመላለሱ እንደ መላእክት ያመሰግናሉ፡፡ ከቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ቆም ብሎ ቁልቁል ለተመለከተ ምእመናን ከዓለም ባንክ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ዳገቱን ተቋቁመው በነጭ የሀገር ባህል ልብስ አሸብርቀው፣ ነጠላቸውን መስቀለኛ ደርበው፣ የማይቋረጥ ሰንሰለት ሠርተው ሲተሙ ቅዱሳን መላእክት ከምድር እስከ ሰማይ በተዘረጋ መሰላል ሲወጡ ሲወርዱ የሚታዩ ይመስላሉ፡፡

ወጣቱ ከልካይ ቪ-፰ የተሰኘች ጥቁር ዘመናዊ መኪናውን ወደ ዓለም ባንክ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ያጠድፋታል፡፡ እርሷም እንደ ውኃ ትፈስሳለች፡፡ ከልጅነቱ ጀምሮ ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም ልዩ ፍቅር አለው፡፡ የገጠር ተወላጅ በመሆኑ ከቤታቸው ከፍ ብላ ከምትገኘው ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ክርስትና ተነሥቶ፣ ወላጆቹን ተከትሎ፣ በኋላም ከሰፈሩ ሕፃናት ጓደኞቹ ጋር ተመላልሶ ቊርቧል፤ በልጅነቱ የተቀረጸው የፍቅሩ እርሾ አልጠፋም፡፡ ዛሬ ራሱን ችሎ በሀብት ማማ ላይ ቢቀመጥም የልጅነት ትዝታው ከፊቱ ላይ ድቅን እያለበት ሊረሳት አልቻለም፡፡

ከልካይ ሊያስወግደው ያልተቻለው አንድ ችግር አለበት፡፡ መስጠትን እንደ ብክነት ይቆጥረዋል፣ ሞልቶ በፈሰሰው ሀብቱ ለተቸገረ መመጽወትን ይጠላል፡፡ ገንዘብ ባገኘና ኪሱ በደለበ ቊጥር "እንዴት ሆኜ ይህንን ሀብት እንዳፈራሁት እኔ ነኝ የማውቀው" በሚል ፈሊጥ ተተብትቦ እጁን ይሰበስባል፡፡ በሆነ አጋጣሚ እንኳን ለተቸገረ ወይም ለቤተ ክርስቲያን ቢሰጥ ሀብቱን ለነፋስ እንደበተነ ይቈጥረዋል፡፡ ቢሰጥም ስለሚቆጭ ለተቸገረ አይሰጥም፡፡ በዚህ ምክንያት "ቋጣሪው" ይሉታል፡፡ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ የሚጐርፉትን ምእመናን በመኪናው ጡሩምባ እያስበረገገ አልፎ ጀሞ ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ሲደርስ ከዚያ በላይ በመኪና መጓዝ እንደማይችል በመረዳቱ ለመኪናው ምቹ ቦታ ፈልጎ በማቆም በእግሩ ዳገቱን ተያያዘው፡፡ የመንገዱን ግራና ቀኝ ይዘው "ስለ እመቤታችን፣ ስለ ጭንቅ አማላጇ" እያሉ የሚለምኑ ነዳያን ጨኸት፣ ጧፍ፣ ዕጣን፣ ዘቢብ፣ ሻማ፣ ጃንጥላ አለ የሚሉ ምእመናንን የሚያዋክቡ ሻጮች ድምፅ ጆሮን ያደነቁራል፡፡ ምእመናንም የሚሹትንና አቅማቸው የቻለውን እየገዙ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ይገሰግሳሉ፡፡ ከልካይ "ወደ ቤተ ክርስቲያን ስትሄድ ባዶ እጅህን አትሂድ›› የሚለውን ቃል ሽሮ ባዶ እጁን ወደ እመቤታችን ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ገባ፡፡ አንድ እግሩ ከጉልበቱ በታች የተቆረጠ የኔ ቢጤ ምርኩዙን ተደግፎ በአንድ እግሩ እንጣጥ እንጣጥ እያለ ወደ ከልካይ በመቅረብ "ስለ እመቤታችን" በማለት እጁን ዘረጋ፡፡

ከልካይ የኔ ቢጤውን በመጠየፍ ሰውነቱን እያሽማቀቀ በእግዚአብሔር ይስጥልኝ ስሜት አንገቱን ዝቅና ከፍ አደረገ፡፡ "የኔ ጌታ አይጨክኑ፤ ለሀገር ድንበር ከተዋደቁት ጀግኖች አንዱ ነኝ፡፡ አንድ እግሬን ያጣሁትም ለሀገሬ ስል ነው፣ ይኸው አልባሽ አጉራሽ አጥቼ እንከራተታለሁ፡፡ ስለ እመቤታችን!" አለ እጁን ዘርግቶ እየተከተለው፡፡ ከልካይ ተበሳጨ፡፡ "እግዚአብሔር ይስጥልኝ!" አለ ኮስተር ብሎ፡፡ "ሞኝህን ፈልግ ገንዘብ እንዲሁ ይበተናል እንዴ? እንዴት እንዳፈራሁት እኔ ነኝ የማውቀው" ይላል በልቡ፡፡ ቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ከገባ በኋላ በወንዶች መግቢያ በኩል ተሳልሞ ከዐውደ ምሕረቱ ፊት ለፊት ጥቅጥቅ ካለው ባሕር ዛፍ ውስጥ አንዱን ተደግፎ በመቆም ጸሎት ለመጸለይ ሞከረ፤ ነገር ግን ምን እንደሚጸልይ አልመጣልህ አለው፡፡ -"መገኘቴ በራሱ በረከት ነው" በማለት ራሱን ሸንግሎ ወዲህ ወዲያ የሚንቀሳቀሱትን ምእመናን ይታዘባል፡፡

ቅዳሴው ተፈጽሞ ታቦት ከመውጣቱ በፊት አንድ በዕድሜ የበለጸጉ ባለ ረጅም ነጭ ሪዝ ካህን የተአምረ ማርያም መጽሐፍ በቀይ ግምጃ እንደተሸፈነ በደረታቸው ታቅፈው በመውጣት በዐውደ ምሕረት ከተዘረጋው አትሮንስ ላይ መጽሐፉን አኖሩት፡፡ የድምፅ ማጉያውን ከዕለቱ መርሐ ግብር መሪ ተቀብለው ለማንበብ ሲዘጋጁ ወፈር፣ አጠር ያሉና ጋቢ የለበሱ አባት

ቀርበው በጆሯቸው አንድ ነገር ሹክ ብለዋቸው ሦስት የታሠሩ ባለ አሥር ሺህ ብሮችን አስረከቧቸው፡፡ ካህኑ የድምፅ ማጉያውን አስተካክለው በመያዝ "እግዚአብሔር ይስጥልኝ አባታችን፡፡ በእውነት እኚህ አባት የተባረኩ ናቸው፡፡ ባለፈው ወር አንድ ችግር ገጥሞኝ ለእመቤታችን አልቅሼ ነግሬያት ነበር፣ አልዋለ አላደረ በዕለተ ቀኗ ፈጽማ ካጋጠመኝ ችግር አድናኛለችና ለክብሯ መግለጫ ፴ ሺህ ብር አምጥቻለሁ ብለዋል" በማለት ብሩን ለምእመናን እያሳዩ "እልል ብላችሁ አመስግኑላቸው" አሉ፡፡ የምእመናን እልልታና ጭብጨባ ከዳር እስከ ዳር አስተጋባ፡፡

ከልካይ ዛፉን በመደገፍ እጁን አጣምሮ እንደቆመ "ይቀልዳል እንዴ? ሠላሳ ሺህ ብርን እንዴት እንደማመጣው እኔ ነኝ የማውቀው፡፡ እግዚአብሔር ይሰጣል እንጂ ይቀበላል እንዴ? ጽድቅስ እግዚአብሔር የሰጠንን ሀብት ሳናጕድል አትርፈን መገኘታችን ነው እንጂ ገንዘብ ለእግዚአብሔር ምን ያደርግለታል?" አለ በልቡ ስዕለት ሰጪውን ሰው እየታዘበ፡፡ ከልካይ በካህኑ ንግግር ተበሳጨ፡፡ "እኔ እኮ የሚገርመኝ በየሄድኩበት ሁሉ ስጡ፣ አምጡ የሚል ብቻ ነው እንዴ? ለምን ያስጨንቁናል? መስጠት ካለብን ልቡናችን ሲፈቅድ፣ ከራሳችን ሲተርፍ ነው እንጂ ዝም ብሎ ይሰጣል እንዴ? እኔስ ብሆን መቼ ተረፈኝ፣ ያሰብኩት ተሳክቶ ሦስቱን ድርጅቶቼን ወደ አራት ወይም ወደ አምስት ከፍ አድርጌ ብሰጥ እኮ ምንም አይደለም" አለ ራሱን ለመሸንገል፡፡ ከልካይ በካህኑ ማሳሰቢያ መነሻነት ከጎሊናው ጋር መሟገቱን ቀጠለ፡፡ "ደግሞስ 'ምጽዋትህ በሥውር ይሁን' አይደል የሚባለው? በዐደባባይ ምን አስነገረኝ? ከተረፈኝ በሥውር እሰጣለሁ፡፡ በዐደባባይ የሚሰጡ እኮ ከንቱ ውዳሴ ፈላጊዎች ናቸው፡፡ ነገር ግን አንድ ሰው ለራሱ ሳይበቃው እንዴት ለሌላ ይሰጣል?" አለ ከኅሊናው ጋር እየተሟገተ፡፡

"ተሳስተሃል፡፡ መስጠት እኮ ያጸድቃል፡፡ ካለህ ላይ ነው እንጂ ከተረፈህ ላይ ስጥ አይልም እግዚአብሔር፡፡ ግድ የለህም ስጥ ይሰጥሃል" በማለት ኅሊናው ይሞግተዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያን አልፎ አልፎ ሲሄድ በእነዚህ አሳቦች እንደተፈተነ ነው፡፡ እንደ ሀብታም ግን እጁ ተፈትቶ አያውቅም፡፡ ከኅሊናው ጋር ለመታረቅ ሲፈልግ ከአሥር ብር ያልበለጠ ገንዘብ እየተንቀጠቀጠም ቢሆን ጃንጥላ ላይ ጣል ያደርጋል፤ ወይም ሙዳየ ምጽዋት ውስጥ ሰው አየኝ አላየኝ እያለ ይጨምራል፡፡ "ይቀልዳሉ እንዴ? አፈር ልሼ የምለብሰው ጨርቅ፣ የማጠልቀው ጫማ ሳይኖረኝ ሊስትሮ እየጠረግሁ ያጠራቀምኩትንና ለዚህ ክብር የበቃሁበትን ገንዘብ እንዴት እበትናለሁ፡፡ ዛሬ ብበትነው ነገ መሰብሰብ እንዴት ይቻለኛል? የለም አልሞኝም" አለ እጁን አጣምሮ እንደ ቆመ፡፡ ካህኑ ዕለቱን አስመልክቶ ከተአምረ ማርያም አንዱን አንብበው በአቡነ ዘበሰማያት ዘግተው ወደ ቤተ መቅደስ ገቡ፡፡

ታቦቱ እስከሚ ወጣ ድረስ ከዐውደ ምሕረቱ ዝማሬው ቀጥሏል፡፡ ረዘም፣ ቀጠን ያሉ ሽበት ጣል ጣል ያደረገባቸው አንድ አባት ነጠላቸውን አደግድገው የስዕለት ጃንጥላቸውን ዘቅዝቀው "ስለ እመቤታችን ስለቅድስት ድንግል ማርያም" እያሉ ይለምናሉ፡፡ አባቶች፣ እናቶች፣ ወጣቶች፣ ሕፃናቱ ሳይቀር ያላቸውን ወደ ጃንጥላው ወርወር ያደርጋሉ፡፡ ከልካይ ዘንድ ሲደርሱ ቆመው ዓይን ዓይኑን ተመለከቱት፡፡ ደንግጦ ያጣመረውን እጁን በይሉኝታ ፈትቶ ኪሱን ሲዳብስ ድፍን ዐሥር ብር አገኘ፡፡ በይሉኝታ እያሳዘነውም ቢሆን ጃንጥላው ላይ አኖረው፡፡ "እመቤቴ ትስጥልን፡፡ ለአጥሩ ማሠሪያ ነው፡፡ እኛ ካልሠራነው ማን ይመጣል? ምእመናን የእመቤታችንን ቅጥር እንሥራ" እያሉ አለፉ፡፡

አንዲት ዐይነ ሥውር እናት የተቀዳደደ አዳፋ ነጠላ ደርባ ከስድስት ዓመት በማይበልጥ ወንድ ልጇ እየተመራች ልብ በሚሰብር ቅላጼ "ስለ ጭንቅ አማላጇ! በርዶኛል አልብሱኝ፣ ርቦኛል አብሉኝ! ጠምቶኛል አጠጡኝ" በማለት ትለምናለች፡፡ ከልካይ የየኔ ቢጤዋ የልመና ቅላጼ ሊረዳው ያልቻለው ስሜት ፈጠረበት፡፡ ሳይፈልግ ድምፅ ወደሰማበት አቅጣጫ ተመለከተ፡፡ አንዳንዶች ከንፈራቸውን ከመምጠጥ አልፈው ያላቸውን ጣል፣ ጣል ያደርጉላታል፡፡

የየኔ ቢጤዋ ልመና አንጀት የሚበላ ቢሆንም ከልካይ ራሱን አሸንፎ ኪሱን መዳበስ አቃተው፡፡ ከዚያ ይልቅ "አሁን አንድ ብር፣ ሁለት ብር ብሰጣት ምን ይጠቅማታል? ከድህነቷ አያስጥላት፤ ነገም ከመለመን አትወጣ፡፡ ይባስ ስንፍናን ማበረታታት ነው" ‹ብሎ ልቡን አጨከነ፡፡ የኔ ብጤዋም በልጇ እየተመራች፣ እጇን ለመቀበል እንደ ዘረጋች አለፈች፡፡ ታቦቱ ወደ ዐውደ ምሕረቱ ከመውጣቱ በፊት ዝማሬው አልቆ አንድ ሰባኬ ወንጌል ለማስተማር ድምፅ ማጉያውን ተቀበለ፡፡ ሰባኬ ወንጌሉ በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም ካማተበ በኋላ ምእመናን የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን ዕረፍት ምክንያት በማድረግ በቦታው በመገኘታቸው አመስግኖ "ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው" በሚል ርእስ ማስተማር ጀመረ፡፡

መምህሩ ስብከቱን በመቀጠል "በልግሥና በፍጹም እምነት ጸንቶ የሚሰጥ ሰው እግዚአብሔር አሳፍሮት አያውቅም፡፡ ስንሰጥ እግዚአብሔር የበለጠውን አበርክቶ፣ ባርኮና ቀድሶ ይሰጠናል፡፡ እግዚአብሔር የለመኑትን የማይነሳ አምላክ ባሔ በእግዚአብሔር ፊት ቀርበን ከምንወደስባቸውም ሆነ ከምንወቀስባቸው ቃላት መካከል ብራብ፣ አብልታችሁኛል፣ ብጠማ አጠጥታችሁኛል፣ ብታረዝ አልብሳችሁኛል፣... የሚሉት መሠረታዊ የርኅራኄ ቃላት ናቸው፡፡ ለመሆኑ ከየትኛው ወገን ነን? ከሞላን ከተረፈን ሳይሆን ካለን ለሌላቸው መስጠት ታላቅ የጽድቅ ተግባር ነው፡፡ አጠገባችን ያሉትን የተራቡትን፣ የተጠሙትን፣ የተቸገሩትን መርዳት በረከት ያስገኛል ..." በማለት ይሰብካል፡፡

ሰባኪው የመረጠው ርእስና የትምህርት አሰጣጥ የከልካይን ልብ እያራደው ፍርሃት ለቀቀበት፡፡ የዓይነ ሥውሯ የልመና ቅላጼ ከውስጡ አልጠፋ አለው፡፡ ሰባኪው ደግሞ ባልጠበቀው መንገድ ስብከቱን ቀጥሏል፡፡ "ምን ማለቱ ነው? ከሰጠሁ እኮ ካለኝ ላይ አጕደልኩ ማለት ነው፡፡ አጉድሎ መገኘት ደግሞ ያስጠይቃል፡፡ ለእግዚአብሔር አለመታመንም ነው፡፡ የሰጠኝን እንዴት የትም እበትናለሁ? ይኼ ሰባኪ አብዷል እንዴ?" በማለት እየፈራም ቢሆን ራሱን ለማረጋጋት ሞከረ፡፡ ሰባኪው ስብከቱን ቀጠለ፡፡ ስለባለጸጋው ነዌ እና ከደጁ ተጥሎ ስለነበረው አልዓዛር ታሪክ

እንሥቶ ስብከቱን አጠናከረ (ሉቃ. ፲፮÷፳-፳፮)፡፡ ከልካይ በፍርሃት የተዋጠው ልቡ በፍጥነት ሲመታ ታወቀው፡፡ ከቤተ ክርስቲያኑ መውጣት ፈለገ፤ ግን ደፍሮ እግሩን ማንቀሳቀስ ተሳነው፡፡

"ነዌ የሚባል ባለጸጋ ነበር፤ መላው አካሉ በቁስል ተመትቶ የሚሰቃይ አልዓዛር የሚባል ድሃ ከደጁ ወድቆ ወጪ ወራጁን ይማጸን ነበር፡፡ አልዓዛር ከሕመሙ በተጨማሪ ከረኀቡ ጽናት የተነሣ ለውሾች የተጣለ ምግብ ለመብላት ይመኝ ነበር፡፡ ውሾቹም ቁስሉን ይሉስለት ነበር፡፡ ነገር ግን ነዌ ሲወጣ ሲገባ ተጠይፎት ሊረዳው አልወደደም፡፡ ሞት አይቀርምና ሁለቱም ዐረፉ፡፡ ነዌ በሲዖል ሲሠቃይ፣ አልዓዛር በገነት እግዚአብሔርን ያመሰግን ነበር፡፡ ባዕለጸጋው ነዌ ወደ አብርሃም ያማልደው ዘንድ ጮኸ፡፡ አልዓዛርን ይልክለት ዘንድ….''፡፡ ከልካይ ከእመቤታችን ቅጥር ለመውጣት አቅም አጣ፡፡ ሰውነቱ በላብ ተዘፈቀ፡፡ ከኪሱ መሐረብ አውጥቶ ፊቱን መጠራረግ ጀመረ፡፡ የደረቀውን ከንፈሩን ማርጠብ አማረው፡፡ ሰባኪው ግን ትምህርቱን ቀጠለ፡ "አብርሃም ግን ልጄ ሆይ አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደ ተቀበልህ አስብ፤ አልዓዛርም በሥቃይ በምድር ላይ ኖረ፡፡ አንተ ግን ዞር ብለህ አላየኸውም፣ ተጠየፍከው፡፡ ዛሬ እርሱ በዚህ ይጽናናል፡፡ በእግዚአብሔር ፊት ከመላእክቱ ጋር ያመሰግናል፡፡ አንተ ግን በሲዖል ትቃጠላለህ ….አለ፡፡ "

ከልካይ ቃሉን ዛሬ ብቻ የሰማው ይመስል አብረከረከው፤ መቆም አቅቶት ባለበት ተቀመጠ፡፡ ከዘመናዊ ባለ ሁለት ወለል ቤቱ ፊት ለፊት ላስቲክ ወጥራ አንዲት ጨቅላ ሕፃን ይዛ ስለምትኖረው ሴት አሰበ፡፡ አንድም ቀን ዞር ብሎ አይቷት፤ ለችግሯ መፍትሔ ሰጥቷት አያውቅም፡፡ እንዲያውም ሲወጣ ሲገባ ከመጠየፉ የተነሣ አካባቢውን ታቆሽሻለች ብሎ ከዚያ ቦታ እንድትነሣ ለበርካታ ጊዜ አስቦ ነበር፡፡ ከልካይ ከዚህ በኋላ የሰባኪውን ስብከት መስማት አልቻለም፡፡ አንድ ዓይኑ የፈረጠ፣ እግር የሌለው የኔ ቢጤ በመንፏቀቅ ቀጭን ገመድ በወገቡ ላይ ታስሮ በመሪ "ዓይን የሌለኝ፣ እግር የሌለኝ አትለፉኝ ምሳዬን አጉርሱኝ፤ ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ እመቤታችን" እያለ ወደ ከልካይ ቀረበ፡፡ ከልካይ ደነገጠ፤ ከቤቱ ፊት ለፊት ወድቀው ያሉት እናትና ልጅ ለነፍሱ ያደረ የሚያቀርብላቸውን ምጽዋት እየተጠባበቁ ታዩት፡፡ የነዌና አልዓዛር ታሪክ ደግሞ ዕረፍት ነሣው፡፡ በሲዖል የነዌን ሥቃይ፣ በገነት የአልዛዓርን ደስታ እያሰበ ኅሊናው በሓሳብ ተወጠረ፡፡

የኔ ቢጤው እየተንፏቀቀ "ስለእመቤታችን! እግር የሌለኝ፣ ዓይን የሌለኝ፣ ወገኖቼ ሰጥታችሁ ጽደቁብኝ! ርቦኛል አጉርሱኝ፣ ጠምቶኛል አጠጡኝ" ይላል፡፡ "ሰጥታችሁ ጽደቁብኝ!" የምትለዋ የየኔብጤው ልመና ከልካይን ከሄደበት መለሰችው፡፡ ኪሱን ዳበሰ፡፡ ገንዘቡን መኪናው ውስጥ አድርጐ በመምጣቱ የሚሰጠው አጣ፡፡ እጆቹ ተንቀጠቀጡ፡፡ እየፈራም ቢሆን "እመቤቴ ትስጥልኝ" አለ፡፡ የኔ ቢጤው በመሪው እየተመራ አለፈ፡፡ ሌላዋ ደግሞ ተተካች፡፡ አንዲት ሴት ጨቅላ ሕፃን እንደታቀፈች "ስለ እመቤታችን!" በማለት ቀረበች፡፡ ከከልካይ ጋር ዓይን ለዓይን ተጋጩ፡፡ እርሱ ንቆ የረሳት ከቤቱ ፊት ለፊት ላስቲክ ወጥራ በልመና የምትተዳደረው ከዚያች ቦታ ለበርካታ ጊዜያት ሊያባርራት የዛተባት ሴት ነበረች፡፡ ሁለቱም ተፋጠጡ፡፡ ነገር ግን ዓይኑን ሞልቶ እርሷን ማየት አቃተው፡፡ ዓይኑን ከዓይኗ አሸሸ፡፡ እሷም ተስፋ የቆረጠች በሚመስል ገረፍ አድርጋው አለፈች፡፡ ከከልካይ ይልቅ ከፊት ለፊቷ ዓይነ ሥውሩ እና እግር አልባው የሚንፏቀቀውን የኔ ቢጤ ዓይታ አዘነችለት፡፡ ልጇን እንደ ታቀፈች ወገቧ ላይ የታጠቀችውን መቀነት ፈትታ ድፍን አሥር ብር ለምና ካገኘችው ሰጠችው፡፡ ለምኖ ለለማኝ መሆኑ ነው፡፡

ከልካይ ያየውን ማመን አቃተው፡፡ ሰማይ ምድሩ ዞረበት፡፡ ሳያስበው ዕንባው በሁለት ጉንጮቹ መውረድ ጀመረ፤ ሳያስበው ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ፡፡ የሰባኪው ስብከት፣ የየኔ ቢጤዎቹ መተዛዘን፣ የናቃት የኔ ቢጤ ድርጊት ብቻ መሄጃው ጠፋው፡፡ ታቦቱ እስኪ ወጣ በዚያ ቦታ መቆየት አስፈራው፡፡ ኃይሉን አሰባስቦ ከእመቤታችን ቅጥር በመውጣት መኪናውን ወደ አቆመበት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ቁልቁል ሮጠ፡፡ ከመኪናው ውስጥ ቁጭ ብሎ የቁጭት፣ የጥፋተኝነት፣ የጸጸት ዕንባ ማንባቱን ቀጠለ፡፡ ከሁሉም በላይ እየለመነች የእርሷንና የልጇን ጉሮሮ የምትደፍነው ምስኪን ሴት ድርጊት ዕረፍት ነሣው፡፡

"ለካ እግዚአብሔር እኔን ለማስተማር እኔን ለጽድቅ ያዘጋጀኝ ዘንድ የላካት ነበረች ለካ፡፡ እኔ ግን ከንቱ፣ የከንቱ ከንቱ ነኝ፡፡ እንዴት ይህንን ማሰብ ያቅተኛል?" እያለ መረጋጋት እስኪሳነው ድረስ አለቀሰ፡፡ ከልካይ ታቦት ወጥቶ መርሐ ግብሩ እስኪጠናቀቅ መኪናው ውስጥ ሆኖ ጠበቀ፡፡ ምእመናን ወደየቤታቸው ሲሄዱ ዓይኖቹ ተንከራተቱ፡፡ የፈለገውን ማግኘት ግን አልቻለም፡፡ ቢሆንም ተስፋ አልቆረጠም፡፡ አምስት፣ ዐሥር፣ ሃያ፣ ሠላሳ ደቂቃዎች አለፉ፡፡ ወደ ኋላ የቀሩ ምእመናን ብቻ አልፎ አልፎ ቁልቁለቱን ተያይዘውታል፡፡ ከልካይ ልሂድ አልሂድ እያለ ሲያመነታ ዓይኖቹም ልቡናውም ሲጠባበቁት የነበረውን ነገር ከርቀት ተመለከተ፡፡

ከመኖሪያ ቤቱ ፊት ለፊት ላስቲክ ወጥራ የምትኖረዋ ሴት ልጇን አዝላ ብቻዋን እየመጣች ነው፡፡ ጸጸት ያደቀቀው ልቡ በተስፋ እና በደስታ ተሞላ፡ ከትምህርቶች ሁሉ በላይ ጽድቅ ያስተማረችውን ሴት ሊንከባከብ፣ በሀብቱ ደካሞቹን ሊረዳ ለራሱ ቃል ገባ፡፡ ወደ እርሱ መቅረቧን ሲመለከት ከመኪናው ወርዶ የኋላውን በር ከፍቶ ጠበቃት፡፡ ስትደርስ "ይቅርታ ወደ ቤት ላድርስሽ ግቢ" አላት፡፡ የኔ ቢጤዋ አላመነችም፡፡ ከዛሬ ነገ ይጉበኘኛል፤ እኔን እንኳን ባይሆን ልጄን ያሳድግልኛል ብላ ተስፋ ስታደርገው የነበረው ሰው ጠዋት ማታ ሊያባርራት ዕረፍት አልነበረውም፡፡ ዛሬ ግን አጠገቧ ቆሞ፣ የመኪና በር ከፍቶ ትገባ ዘንድ ሲጋብዛት ማመን አቅቷት አመነታች፡፡

ከልካይ እስከ አሁን የፈጸመውን በደል ለመካስ ቆርጧል፤ ይህንን ዕድል ማጣት አልፈለገም፡፡ እስከ አሁን ብበድልሽም "እባክሽ ከመኪናው ግቢና አብረን እንሂድ" አለ በትሕትና፡፡ የኔ ቢጤዋ እያመነታችም ቢሆን ልጇን ከጀርባዋ አውርዳ በመታቀፍ ከመኪናው ገባች፡፡ ከልካይ የገባውን ቃል ለመፈጸም መኪናውን አስነሥቶ በረረ፡፡፨

***ወስብሐት ለእግዚአብሔር***

# ለሰው ይናገርብኛል ብዬ ስለምሰጋ ኃጢአቴን ለካህን ባልናገርስ?

**ክፍል ሁለት**

**ቀሲስ ዐቢይ ሙሉቀን**

ባለፈው ዕትም የዚህን ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ማስነበባችን ይታወቃል፤ ቀጣዩን ደግሞ እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

አንድ በሽተኛ ሐኪም እየቀያየረ በታየ ቍጥር መፍትሔ የማግኘት ዕድሉ የጠበበ ነው። ከመጀመሪያ ጀምሮ ክትትል የሚያደርገውና በአግባቡ የበሽታውን ሥር መሠረት የሚያውቀው ሐኪም ቢሆን የተሻለ ይሆንለታል። ተነሳሕያንም ንስሓ አባቶቻቸው ለነፍሳቸው የሚጠቅም ትምህርት እንዲሰጧቸው ቀርበው በግልጽ መነጋገር ይኖርባቸዋል።



*መጋቤ ሐዲስ ምሥጢረ ሥላሴ ማናየ*

**ሐመር መጽሔት፡- ንስሓ አባት ለመቀየር የሚያስገድዱ ሁኔታዎች ካሉ ቢገልጹልን?**

**መጋቤ ሐዲስ ምሥጢረ** ያት ሲኖር ነው። የመጀመሪያው ምክንያት ንስሓ አባት ወጥቶ ወርዶ መምከር፣ ማስተማር የማይችል ቢሆን በአልጋ ቁራኛ፣ በደዌ ዳኛ ተይዞ አስፈላጊውን አገልግሎት መስጠት የማይችል ቢሆን ወይም በእርጅና ምክንያት ማገልገል ባይችል የንስሓ ልጆች አገልግሎቱን ማግኘት ስላለባቸው ከአባታቸው ጋር ተመካክረው መቀየር ይችላሉ። ካህን ወጥቶ ወርዶ አስተምሮ መንጋዎችን ከተኵላ የሚታደግ እረኛ በመሆኑ የእረኝነት ተግባሩን መወጣት ካልቻለ መንጋዎች እንዳይበተኑና ተኵላ እንዳይነጥቃቸው በእርሱ ፈንታ ትጉህና መልካም እረኛ ሊይዙ ይገባል።

ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ በካህኑ የሃይማኖት ሕፀፅ ከተገኘበት ነው። ንስሓ አባት የምንይዘው በሃይማኖቱ ጥርጥር የሌለበት ሆኖ ከእግዚአብሔር ጋር ሊያገናኘን እንጂ ከእግዚአብሔር እንዲያለያየን ባለሆኑ የሃይማኖት ሕፀፅ ከተገኘበት ይቀየራል። ቅዱስ ጳውሎስ "የእግዚአብሔርን ቃል የነገሯችሁን መምህሮቻችሁን ዐስቡ፤ መልካም ጠበያቸውን አይታችሁ በእምነት ምሰሏቸው" (ዕብ. ፲፫፥፯) በማለት ያስተማረን መምህረ ንስሓዎቻችን በእምነት የምንመስላቸው ከእግዚአብሔር ጋርም የሚያገናኙን በመሆናቸው ነው። ስለዚህ ካህኑ የሃይማኖት ሕፀፅ ከተገኘበት ክርስቲያኖችን ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርባቸው ስለማይችል ሌላ አባት መያዝ የግድ ይሆናል።

እንደዚህ ያለውን ጉዳይ ልንጠነቀቀው እንደሚገባን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "የበግ ለምድ ለብሰው ወደ እናንተ ከሚመጡ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ፤ በውስጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኵላዎች ናቸው። ከፍሬአቸው ታውቋቸዋላችሁ፤ ከእሾህ ወይን ከአሜከላም በለስ ይለቀማልን? እንዲሁ መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬን ያፈራል፤ ክፉ ዛፍም ክፉ ፍሬን ያፈራል፤ መልካምም ዛፍ ክፉ ፍሬን ማፍራት፣ ክፉ ዛፍም መልካም ፍሬን ማፍራት አይችልም። መልካም ፍሬ የማያፈራ ሁሉ ይቆረጣል፤ ወደ እሳትም ይጣላል። እንግዲህ ከፍሬአቸው ታውቃቸዋላችሁ" (ማቴ. ፯፥፲፭-፳) በማለት ያስተማረው ንስሓ አባት ስንይዝ እንድንጠነቀቅ ጭምር ነው።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዕወቋቸው፤ ተጠንቀቁ፤ እያለ ያስተማረን ሃይማኖት ሳይኖራቸው ሃይማኖት እንዳላቸው፣ ክህነቱ ሳይኖራቸው ክህነት እንዳላቸው ሆነው ምእመናንን የሚያስናክሉ በመኖራቸው ነው። "መልካም ፍሬ የማያፈራ ሁሉ ይቆረጣል" የሚለው ቃል እግዚአብሔር ከመምህርነት፣ ከካህንነት ይሽራቸዋል እኛም መጀመሪያ መስለውን በአባትነት ብንይዛቸውም ካወቅናቸው በኋላ ግን ልንቀይራቸው ብቻ ሳይሆን ከአገልግሎታቸው እንዲታገዱ የሚጠበቅብንን ማከናወን ይኖርብናል።

ሦስተኛው ምክንያት የቦታ ርቀት ነው። ለምሳሌ ካህኑ ወደ ሩቅ ቦታ ቢሄድ ያ ካህን እየመጣ ሊያገለግል ስለማይችል ምእመናኑም አገልግሎቱን ማግኘት ስላለባቸው ሌላ አባት መያዝ ይኖርባቸዋል። ሐዋርያት አስተምረውና አሳምነው ያጠመቋቸውን ምእመናን ከእነርሱ ጋር ባሉበት ወቅት ራሳቸው ያገለግሏቸው ነበር። እነርሱ ለአገልግሎት ከቦታ ወደ ቦታ በሚንቀሳቀሱበት ወቅት ግን ከምእመናን ጋር አብረው የሚኖሩ እነርሱን ዕለት ዕለት የሚያገለግሏቸው ካህናትን እየሾሙላቸው ይሄዱ ነበር። ለምን ከተባለ የንስሓ አባትና የንስሓ ልጅ ሁልጊዜ መገናኘት ስላለባቸው ነው። አሁንም ካህናት በልዩ ልዩ ምክንያት ከነበሩበት ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ከሄዱ ምእመናን የመጀመሪያቸውን አባት ተሰናብተው በአካባቢያቸው የሚኖር ሌላ አባት መያዝ ይችላሉ።

**ሐመር መጽሔት፡-** አንዳንድ ክርስቲያኖች ንስሓ ግቡ ሲባሉ እንፈራለን የሚል ምላሽ ይሰጣሉ፤ ለእንደነዚህ ያሉ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን የተለየ መፍትሔ ይኖራት ይሆን? ለምሳሌ

በደላቸውን በጽሑፍ፣ ወይም ለቅርብ ጓደኛቸው በመናገር እና በመሳሰሉት?

**መጋቤ ሐዲስ ምሥጢረ ሥላሴ ማናየ፦** እንፈራለን የሚለው ምክንያት አሳማኝ አይደለም። ቀድሞ መፍራት የሚገባ ኀጢአቱን ሲሠሩ ነው። ኀጢአቱን ሲሠሩ ያልፈሩ ለንስሐ እንዴት ይፈራሉ? ፍሩት የተባልነው ኃጢአትን ነው እንጂ ንስሐ መግባትን አይደለም። ሊቁ ቅዱስ ያሬድ "ኢትፍርሕዎ ለሞት ፍርሕዋ ለኃጢአት፤ ሞትን አትፍሩት ኃጢአትን ፍሩት" (ጾመ ድጓ) በማለት እንደ ተናጋረው መፍራት የሚገባ ኃጢአትን ነው።

ምን አልባትም እኛ ለንስሓ አባት ለመናገር ፈራን እንል ካልሆነ በቀር ዓለም የሠራነውን ኀጢአት ያወራዋል። ይልቁንም ዓለም በግልጥ የሚያወራውን ኀጢአታችንን ምንም ሳንፈራና ሳናፍር ደፍረን መናገር ያስፈልጋል። ሌላ አካል በትምህርት፣ በምክር፣ ወደ ንስሓ ለማደፋፈር ሊያግዝ ይችላል እንጂ የእርሱን ኀጢአት መቀበል አይችልም። ለጓደኛው ሲናገር ካላፈረ ለንስሓ አባቱ መናገር እንዴት ሊያፍር ይችላል? በጽሑፍም ምን አልባት ኃጢአቱ እንዳይረሳው ቀርቦ ንስሓ በሚገባበት ጊዜ እያስታወሰ ለመናገር እንዲያመቸው ሊያደርግ ይችላል እንጂ እርሱ በአካል ሳይገኝ ጽሑፉን ብቻ ሰጥቶ ንስሓ መግባት የሚባል ነገር የለም።

ይልቁንም ‹‹ራስህን ለካህን አሳይ›› የሚለውን አምላካዊ ቃል አክብሮ ራሱን ዝቅ አድርጎ በመቅረብ ለንስሓ አባቱ መናገር ይጠበቅበታል። ከምንም በላይ ሰው ወደ ንስሓ ሲቀርብ ማወቅ ያለበት የሚቀርበው ወደ እግዚአብሔር መሆኑን ነው። ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሰው ይሰቀል፣ ይፈለጥ፣ ይቆረጥ፣ ይታሰር አይባልም። በዚህ ፈንታ ምሕረትን፣ ይቅርታን፣ ሥርየተ ኀጢአትን ያገኛል እንጂ። እግዚአብሔር በነቢዩ በሚልክያስ አድሮ "ወደ እኔ ተመለሱ፤ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ" (ሚል. ፫፥፯) በማለት ወደ እርሱ በንስሓ ለሚመለሱት እርሱም በምሕረት እንደሚመለስ ተናግሯል። ስለዚህ እግዚአብሔር በምሕረቱ እንዲመለስ የሚያስችለውን የንስሓ መንገድ ይዞ መጓዝ እንጂ መፍራት አይገባም።

ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም "አማን መነኑ ሰማዕት ጣዕማ ለዛ ዓለም፤ ወከዓዉ ደሞሙ በእንተ እግዚአብሔር፤ ወተዐገሡ ሞተ መሪረ በእንተ መንግሥተ ሰማያት፤ ሰማዕታት የዚችን ዓለም ጣዕም በእውነት ናቁ፣ ስለ እግዚአብሔር ብለው ደማቸውን አፈሰሱ፤ ስለ መንግሥተ ሰማያትም መራራ ሞትን ታገሡ" (ውዳሴ ማርያም ዘሐሙስ) በማለት እንደተናገረው የዚህን ዓለም ሐሜትና ደስታ ትተው ወደ ነደደ እሳት፣ ወደ ተሳለ ስለት ለመግባት ጨክነዋል። ንስሓ ኀጢአትን ለንስሓ አባት ተናግሮ ሥርየተ ኀጢአትን ማግኘት፣ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ እንጂ አንገትን ለስለት፣ ለእሳት መስጠት አይደለም። ስለዚህ በንስሓ የሚገኘውን ጸጋ ርስት መንግሥተ ሰማያት ተስፋ በማድረግ የሚያስፈራ፣ የሚያሳፍር ስላልሆነ በመንፈሳዊ ድፍረት መቅረብ ይገባል።

**ሐመር መጽሔት፦** ከንስሓ አባታቸው ጋር በርቀት ቦታ ያሉ አካላት በስልክ ንስሓ መግባት ይችላሉን?

**መጋቤ ሐዲስ ምሥጢረ ሥላሴ ማናየ፦** የምሥጢረ ክህነትና የምሥጢረ ንስሓ ጉዳይ በመቅረብ፣ በአካል በመገናኘት የሚፈጸም እንጂ በርቀት የሚሆን አይደለም። ካህኑ መንፈሳዊ መጋቢ ነውና ከሥጋዊ አባት በተሻለ መልኩ ተቀራርበው ሊኖሩ ይገባል። የንስሓ አባቱ በሩቁ ያለ ምእመን ቢታመምና ለሞት ለሚያበቃ ሕመም ቢገጥማቸው ማን ይናዝዛቸዋል። ምቹ በሆነ ጊዜ በጤንነት ሳለን ዘመኑ ባፈራው መሣሪያ ማከናወን ይቻላል ልንል እንችላለን። ጭንቅ የሆነ ነገር ቢመጣስ እንዴት ይደርስለታል? ስለዚህ ቢታመሙ በቅርብ ሆኖ ሥርዐተ ቀንዲል የሚፈጽም አባት ያስፈልጋል። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባለህበት ሆነህ ተናገር አላለውም። በዚህ ፈንታ "ሑር ወአፍትን ርእሰከ ለካህን፤ ሂድና ራስህን ለካህን አሳይ" ያለውን ልብ ማለት ያስፈልጋል። "ሂድና" የሚለው ትእዛዝ የአካል ግንኙነትን ያመለክታል።

በንስሓ አባትና በንስሓ ልጅ መካከል ፊት ለፊት መገናኘት ሲኖር ካህኑም የተነሳሒውን ፍጹም መመለስ ተነሳሒው በፊቱ ከሚያሳየው ሁኔታ በመነሣት የሚመለከተው ነገር ይኖራል። በስልክ ቢሆን ግን መረዳት አይቻልም። እንዲህ ያለውን ተግባር ቤተ ክርስቲያን አላስተማረችንም። የጠፋው ልጅ ታሪክ የሚያስረዳንም "ወደ አባቱ መጣ" በማለት ነው። ስለዚህ ተነሳሒው ወዲያውኑ በፍጥነት ወደ አባቱ መሄድ አለበት። የንስሓ አባትም ንስሓውን ከመቀበልና ቀኖና ከመስጠት በተጨማሪ ቀድሶ ማቊረብ አለበት። ቀድሶ ለማቊረብ ሲሆን በቅርብ እንዲያውም ምእመኑ በሚሳለምበት፣ በሚያስቀድስበት አጥቢያ መሆን ያስፈልጋል። ይህ ከሆነ የሚያስፈልገውን ሙሉ አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ።

የምሥጢረ ንስሓ ዋና ዓላማ ተነሳሕያንን ወደ ምሥጢረ ቊርባን ማቅረብ ነው። ስለዚህ በዚያ ቦታ ካህን የለም ማለት ቅዱስ ቊርባን የለም ማለት ነው። እንዲህ ከሆነ ካህን ወዳለበት መሄድ የግድ ነው። የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት ሁሉ በምሥጢረ ጥምቀት መግቢያ በርነት ተጀምረው የሚጠናቀቁት በምሥጢረ ቊርባን ነው። እነዚህ ሁሉ ያለ ካህኑ አይፈጸሙም፤ የሚደመደመው በምሥጢረ ቊርባን ነው ከተባለ ንስሓውን በስልክ ተቀብሎ ቀኖናውም በስልክ ቢሰጠው ሥጋ ወደሙን ግን በስልክ ሊሰጠው አይችልም። ንስሓውም ቢሆን ከላይ እንደተገለጸው በአካል መገናኘትን፣ የተነሳሒውን ሁኔታ መረዳትን፣ የልብ መሰበሩን መገንዘብን የሚጠይቁ ጉዳዮችን ሁሉ በአግባቡ ማወቅ የሚቻለው በአካል ሲገናኙ ነው። ስለዚህ በአጭር አነጋገር በአካል እንጂ በስልክም ሆነ በጽሑፍ ንስሓ መግባት አይቻልም።

በርካታ ምእመናን ካህንም ቤተ ክርስቲያንም በሌለበት ቦታ ሊኖሩ ይችላሉ። ቤተ ክርስቲያን ምርጫ የሌላት የምታስጨንቅ አይደለችም። ጉዳዮችን እንደ ጊዜውና እንደ ቦታው ሁኔታ ታስተናግዳለች። ስለዚህ ከቤተ ክርስቲያንና ከካህን ርቀው

የሚኖሩ ክርስቲያኖች በተስፋ ቢስነት እንዳይጨነቁ በርቀት ከሚኖር አባታቸው ጋር በስልክ እየተደዋወሉ የሚያጽናና ምክር መቀበል ይችላሉ:: በአካል ሲገናኙ ደግሞ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን በጠበቀ መልኩ ንስሓውን ሊያከናውኑ ይችላሉ:: ይህ ማለት ግን የችግሩን ክብደት ከእኛ በላይ እግዚአብሔር ያውቀዋልና በአካል ማግኘት የማይቻልበት ሁኔታ ሲከሠት ጊዜአዊ መፍትሔ ይሆን ዘንድ ነው እንጂ ይህን መግቢያ ይዞ ንስሓ በስልክ መግባት ይቻላል ወደ ሚል ማጠቃለያ መድረስ አይቻልም:: የእግዚአብሔር መንግሥት በየዋህነት እንጂ በብልጠት የምትወረስ አይደለችምና::

**ሐመር መጽሔት፡-** በቅዱስ ወንጌል "በሰው ልጅ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ሁሉ ይሰረይለታል፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ግን በዚህ ዓለምም ሆነ በሚመጣው ዓለም አይሰረይለትም" (ሉቃ. ፲፪፥፲) የሚል ቃል አለ:: ይህ ማለት በንስሓ ይቅር የማይባል ኃጢአት አለ ማለት ነውን?

**መጋቤ ሐዲስ ምሥጢረ ሥላሴ ማናየ፡-** ይቅር የማይባለው ኀጢአት በክህደት መጥናት ነው:: ክዶ የማይመለስ ከሆነ ለማለት ነው:: መንፈስ ቅዱስን የሰደበ ማለት የካደ ማለት ነው:: ለእንዲህ ያለ ሰው ካልተመለሰ ሥርየት የለውም:: ልጅነቱን፣ የታተመበትን ቅዱስ መንፈስ ክዷል:: ስለዚህ መበደሉን አምኖ፣ ከበደሉም ተመልሶ ንስሓ እስካልገባ ድረስ ሥርየት ሊያገኝ አይችልም:: አይሠረይለትም ማለት በክህደቱ ጸንቶ የቀጠለ ከሆነ እንጂ ከተመለሰ ይቅር አይባልም ማለት አይደለም:: ይህን የሠራ ሥርየት የለውም የሚል ገጸ ንባብ ከአንዳንድ መጻሕፍት ቢገኝም የኀጢአቱን ክብደት የሚገልጽ መሆኑን መረዳት ይገባል:: አንድ ሰው የበደለውን ሰው ይቅር አልልህም ቢለው የበደሉን ክብደት ለመግለጽ እንጂ ሽማግሌዎች ተሰብስበው ቢማልዱት ይቅር የማይልበት ምክንያት አይኖርም:: ራሱ እግዚአብሔር ‹‹ለዘመጽአ ኀቤየ ኢይሰድዶ ወኢያወጽኦ አፍአ፣ ወደ እኔ የመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም›› ብሎ ተናግሯል:: ስለዚህ ኀጢአቱ የፈለገውን ያህል ከባድ ቢሆንም ንስሓ ካልገቡበት እንጂ ንስሓ ከገቡበት ይቅር አይባልም ማለት አይደለም:: የእኛ ኀጢአት የትኛውንም ያህል ቢከብድ የእግዚአብሔር ቸርነት ደግሞ ከዚህ በላይ ብዙ ነው:: ሲጀመር ከእግዚአብሔር ምሕረትና ቸርነት በላይ የሆነ ኀጢአት ልንሠራ አንችልም::

ቅዱስ ጴጥሮስ "አላውቀውም" ብሎ ክዶት ነበር:: ግን "ወወጽአ አፍአ ወበከየ፣ ወደ ውጭም ወጥቶ መራር ልቅሶን አለቀሰ" (ማቴ. ፳፮፥፸፭) ተብሎ በቅዱስ ወንጌል እንደ ተጻፈው ከክህደቱ ተመለሰ፤ ኀዘነ፣ እጅግም ተጸጸተ:: ቅዱስ ጴጥሮስ መሪር ዕንባ በማንባቱ ምክንያት "በጐቼን ጠብቅ፤ ጠቦቶቼን አሰማራ፤ ግልገሎቼን ጠብቅ›› (ዮሐ.፳፩፥፲፭-፲፯) የሚለውን ትልቅ ኃላፊነት ለመቀበል በቅቷል:: ይህ ኃላፊነት እጅግ ከባድ ነው:: ሰው እምነት ካልጣለበት ገንዘብ አስቀምጥልኝ ብሎ ለማንም አደራ አይሰጠውም:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ክዶት የነበረውን ቅዱስ ጴጥሮስን ተቀብሎ እንዲህ ያለውን ኃላፊነት መስጠቱ ኃጢአቱን ይቅር ማለቱን ያመለክታል:: ስለዚህ ክዶ የቀረ እንጂ የተመለሰ ሰው ንስሓ የለውም አይባልም::

**ሐመር መጽሔት፡-** በመጨረሻም ንስሓን በተመለከተ ቀረ የሚሉት ጉዳይ ካለ ቢገልጹልን?

**መጋቤ ሐዲስ ምሥጢረ ሥላሴ ማናየ፡-** ንስሓ መሠረታዊ ትምህርት ነው:: ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከእርሱ ስድስት ወር ቀድሞ ስለእሱ የሰበከው መንገድ ጠራጊው መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ ማስተማር ሲጀምሩ ያስተማሩት የንስሓ ትምህርት ነው:: "መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ" የሚለው ትምህርት ዕለት ዕለት የሚሰበክ ነው:: የቅዱስ ወንጌል ዋና ዓላማም ከእግዚአብሔር ቤት ወጥተው የተበታተኑትን መመለስና ወደ እግዚአብሔር ቤት ማቅረብ ነው:: ንስሓ ለዓለም ሁሉ የተነገረ የምሕረት ጥሪ ነውና ሁሉም በሕይወታቸው ተግባራዊ ሊያደርጉት የሚገባ ነው:: ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱሱ ክርስቶስ "ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን እመርጣለሁ ያለው ምን እንደ ሆነ ዕወቁ፤ ኀጥአንን እንጂ ጻድቃንን ወደ ንስሓ ልጠራ አልመጣሁምና" ብሎ እንዳስተማረው በኀጢአት የወደቁ ሰዎች ንስሓን ገንዘብ ሊያደርጉት ይገባል::

በቅዱስ ወንጌል "ከኀጢአተኞች ጋር አብሮ ተቀመጠ" (ማቴ.፱፥፱-፲፩) ተብሎ ተጽፏል:: ከኀጢአተኞች ጋር የተቀመጠበት ዋና ዓላማ ለመብላት አይደለም:: ይህንም "አንሰ ብየ መብልዕ ዘኢተአምርዎ አንትሙ፤ እኔ የምበላው እናንተ የማታውቁት ምግብ አለኝ" (ዮሐ.፬፥፴፪) በማለት ለደቀ መዛሙርቱ ነግሯቸዋል:: ዋናው የመጣለት ዓላማ ኃጢአተኞችን ለማግኘት፣ ወደ ንስሓ ለመጥራትና ይቅርታን ለማደል ስለሆነ ከእነርሱ ጋር ተቀመጠ:: በዚህ ሂደት ፈሪሳውያን እና የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ሐዋርያትን "ለምንት ይበልዕ ሊቅሙሙ ምስለ መጸብሐን ወኀጥአን፣ መምህራችሁ ከኀጢአተኞችና ከቀራጮች ጋር ለምን ይበላል?" ብለው ጠይቀው ነበር:: ጌታችንም "ኢመጻእኩ እጸውእ ጻድቃነ አላ ለንስሓ ኀጥአነ፤ ኃጥአንን ወደ ንስሓ ልጠራ እንጂ ለጻድቃን አልመጣሁም" አላቸው:: ስለዚህ የክርስቶስ ሰው የመሆን ዓላማ ሰዎችን ወደ ንስሓ መጥራት ከዚያም ሰማያዊውን ርስት ማውረስ ነው:: በቅዱስ ወንጌልም "ንስሓ ስለሚገባ ስለ አንድ ኀጢአተኛ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት በሰማያት ደስታ ይሆናል" (ሉቃ. ፲፭፥፲) ተብሎ ተጽፎ እናገኛለን::

በአንድ ኀጢአተኛ ወደ ንስሓ መመለስ በመላእክት ከተማ ደስታ የሚሆን ከሆነ፣ የጠፋ ሰው ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብበት፣ ኀጢአት ርኵሰት የሚወገድበት፣ ፍጹም ይቅርታን የምናገኝበት ንስሓ ስለሆነ በአግባቡ ልንጠቀምበት ይገባል:: ንስሓ ለሰዎች ውድ የሆነ ስጦታ ነውና:: ንስሓ ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት ስለሆነ ሁላችንም በአግባቡ ልንጠቀምበት ይገባል::

**ሐመር መጽሔት፡-** ጥሪያችንን አክብረው ላነሣናቸው ጥያቄዎች ተገቢውን ማብራሪያ ስለሰጡን እናመሰግናለን::

**መጋቤ ሐዲስ ምሥጢረ ሥላሴ ማናየ፡-** እኔም ለዚህ አገልግሎት ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ::✥